# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስ እና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል


# አፋን ኦሮሞን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ረገድ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች ትንተና

## (በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በማና ወረዳ በተመረጡ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)


**በ**

**ሳቢታ ሸውሞሎ ሀሚድ**


አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የድህረ-ምረቃ ትምህርት መርሃ-ግብር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


ሚያዚያ 2013 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# አፋን ኦሮሞን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ረገድ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች

(በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በማና ወረዳ በተመረጡ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)


**በ**

**ሳቢታ ሸውሞሎ ሀሚድ**

**አማካሪ**

**ምህረት ሳዳም (ዶ/ር)**


ሚያዚያ 2013 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ምስጋና

በቅድሚያ ይህን ጥናት በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ እንድችል ላገዘኝ ፈጣሪዬ አልሀምዱሊላሂ ረቢልአለሚን፡፡ በመቀጠል አማካሪዬና መምህሬ ዶ/ር ምህረት ሳዳም ስላደረጉልኝ ድጋፍና ክትትል ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለው፡፡

የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት የመማር ፍላጎቴን እንዳሳካ ላገዙኝ የስራ ባልደረቦቼ፣ ጓደኞቼ ጥናቱ በተካሄደባቸው አንደኛ  ደረጃ ትምህርት ቤቶች የየትምህርት ቤቱ አስተዳደሮች፣ የየትምህርት ቤቱ መምህራን የስድስቱም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ በመሆንና በመረጃ አሰጣጥ ስላሳዩኝ ቀና ትብብር ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡ ትምህርቴን በምከታተልበት ወቅት ብዙ ድጋፍ ያደረጋችሁ፣ አይዞሽ በርቺ በማለት ላበረታታችሁኝ ውድ ባለቤቴ አቶ አለምሁሉ ታዬ፣ ልጆቼ፣ ወንድሜ ጀማል ሸውሞሎ መላው ቤተሰቦቼ በጥናቱ ወቅትና ከዚያም በፊት በነበሩት የድህረ-ምረቃ የመማር ጊዜያቶች ስላሳያችሁኝ ፍቅር፣ አይዞሽ ባይነትና በገንዘብ የማይተመን የሞራል ማበረታቻ የምንጊዜም ባለውለታዎቼ ናችሁና በጣም አመሰግናለው፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ያተኮረው በኦሮምያ ክልል በጅማ ዞን በማና ወረዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ የሚታዩ ተግዳሮቶችን ፍተሻና ትንተና ላይ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ረገድ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን ፍተሻ እና ትንተና ነው፡፡ ጥናቱ የተከናወነው በአመቺ ናሙና ዘዴ በተመረጠው በኦሮምያ ክልል በጅማ ዞን በማና ወረዳ ከሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በስድስት የገጠር ትምህርት ቤቶች መካከል ገሩኬ ጅማቴ፣ ሳረዶ፣ ሶሞዶ፣ ቢሊዳ፣ ቡሩ እና ቡጡሬ በአመቺ ንሞና በመምረጥ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥም በ2013 ዓ.ም በ26 የመማርያ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ከወላጅ መምህራን ህብረት /ወመሀ/፣ ከትምህርት ቤት ሀላፊዎች በጽሁፍ፣ በቃለ መጠይቅና በክፍል ምልከታ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ዓላማውን ለማሳካትም የተከተለው ዘዴ ገላጭ ጥናታዊ ዘዴን የተከተለ ሲሆን በዚህ ዘዴ በመታገዝ ትምህርታዊ ችግሮችን በቀረቡበት ሁኔታ በገለፃ አስደገፎ በመተንተንና መፍትሄዎቻቸውን ለማቅረብ ምቹ በመሆኑ ተመርጦ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ለጥናቱ አስተማማኝ መረጃዎችን ለማግኘትም ቅይጣዊ የምርምር ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የተገኙ መረጃዎችም ለጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች አመላለስ እንዲረዳ በሶስት ደረጃዎች በመክፈል ከተማሪዎች የተሰበሰቡትን መጠናዊ መረጃዎችን በሰታቲክሳዊ ስሌቶች /በፐርሰንት/ በአጠቃላይ አማካይና መደበኛ ልይይት መስፈርያዎች በመለካት በገለፃና ከክፍል ምልከታና ከቃለ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች አይነታዊ የአተናተን ስልትን በመከተል በበቂ ትንተናና ማብራርያ ቀርቧል፡፡ የጥናቱ ግኝቶች እንዳመለከቱትም አብዛኞቹ የጥናቱ ተተኳሪዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትምህርቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ በመሰጠቱ ደስተኞች እንደሆኑና እንደሚደግፉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ በማስተማር ሂደት ላይ አብይ ተግዳሮት እና የተግዳሮቶቹ መንስኤዎችም በአብዛኛው ከትግበራ አውድ ጋር የተያያዙ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነትምህርታዊ፣ ቁሳቁሳዊ፣ ማህበራዊ ድጋፎች ጋር የተያያዙ ሲሆን ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ሁሉንም በአፍ መፍቻ ቋንቋ አውድ ያሉ ተግዳሮቶች ለመቀነስ /ለማስወገድ ቁልፍ ሚና መሆኑን ጥናቱ ረጋግጧል፡፡ በመጨረሻም ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳት አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡ የወደፊት የምርምር አቅጣጫዎችም ተጠቁመዋል፡፡

## ማረጋገጫና የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ መስጫ

**የጥናቱ ርዕስ፡- አፋን ኦሮሞን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ረገድ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች ትንተና (በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በማና ወረዳ በተመረጡ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት**

**ማረጋገጫ፡-**

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩ ይህ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የድህረ-ምረቃ ትምህርት መርሃ-ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት የራሴ የጥናት ውጤት የሆነ፣ ከዚህ ቀደም በየትኛውም ዩኒቨርሲቲ ለመመረቂያ ጽሁፍነት ያልቀረበ፣ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ምንጮች ሁሉ በተገቢው መንገድ ‹‹አክኖውሌጅ›› ተደርገው የቀረቡ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ፡፡

ሳቢታ ሸውሞሎ ____________________ ____________________

### የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ

**የጥናቱ ዋና አማካሪ፡-**

ምህረት ሳዳም (ዶ.ር) ____________________ ____________________

**ተባባሪ አማካሪ፡-**

____________________ ____________________ ____________________

ስም ፊርማ ቀን

**የጥናቱ ፈታኞች**

**የውስጥ ፈታኝ**

____________________ ____________________ ____________________

ስም ፊርማ ቀን

**የውጭ ፈታኝ** ___________ ________________ ________________

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


መግቢያ………………………………………………………………………………i
ምስጋና………………………………………………………………………………iv
አጠቃሎ………………………………………………………………………………v
ማረጋገጫና የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ መስጫ……………………………………………vi
የሰንጠረዥ ማውጫ…………………………………………………………………x
**ምዕራፍ አንድ**………………………………………………………………………1
1.1. የጥናቱ ዳራ………………………………………………………………………1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት…………………………………………………………2
1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች………………………………………………………4
1.4. የጥናቱ አላማዎች…………………………………………………………………4
1.4.1. የጥናቱ አቢይ አላማ……………………………………………………………4
1.4.2. የጥናቱ ንኡሳን አላማዎች………………………………………………………4
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ…………………………………………………………………4
1.6. የጥናቱ ወሰን………………………………………………………………………4
1.7. የቁልፍ ቃላት አውዳዊ ፍቺ………………………………………………………6
**ምዕራፍ ሁለት**………………………………………………………………………7
2. ክለሳ ድርሳናትና ተዛማጅ ጥናቶች ፍተሻ………………………………………7
2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት………………………………………………………………7
2.1.1. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ምንነት………………………………………………………7
2.1.2. የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለመጠቀም አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች…………………………8
2.1.3. የአፍ መፍቻ ቋንቋን የመማሪያ ቋንቋ የማድረግ ጠቀሜታ…………………………9
2.1.3.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስነ-ትምህርታዊ (Pedagogical) ጠቀሜታዎች…………10
2.1.3.2 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስነልቦናዊ (Psychological) ጠቀሜታዎች……………11
2.1.3.3 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማህበራዊ (Sociological) ጠቀሜታዎች………………12
2.1.4. የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለመጠቀም ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች…………………13
2.1.5. በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መማር የሚያስገኘው ጥቅም………………………14
2.1.6 በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ዙሪያ የሚቀርቡ ሙግቶች……………………………14

2.1.7 የአፍ መፍቻ ቋንቋን በመጠቀም ዙሪያ ያሉ ተግዳሮቶች……………………..…....15
2.1.7.1 ስነትምህርታዊ ተግዳሮቶች……………………………………………..…...…15
2.1.7.2. ስነልቦናዊ ተግዳሮቶች……………………………………………………..16
2.1.7.3. ፖለቲካዊ ተግዳሮቶች…………………………………………..…………18
2.1.7.4. ስነልሳናዊ ተግዳሮቶች………………………………………………...…19
2.1.7.5. ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች……………………………………………........19
2.1.7.6 የቁሳቁሳዊ ግብዓቶችና የሰው ኃይል ተግዳሮቶች………………………………21
2.1.7.7 ከትምህርት መስጫ አካባቢ ጋር የሚያያዙ ተግዳሮቶች…………………..…...22
2.1.7.8 ከተማሪዎች ዝግጁነቶች ጋር የሚያያዙ ተግዳሮቶች……………………..…23
2.1.8 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ንድፈ-ሀሳባዊ መሰረቶች……………………..…24
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት………………………………………………………26
**ምዕራፍ ሦስት**…………………………………...…………………..........28
3 የጥናቱ ዘዴና አካሄድ…………………………………………………………...28
3.1 የጥናቱ ስልት…………………………………………………………..….28
3.2 የጥናቱ አካላዮች……………………………………………………………28
3.3 የተጠኚዎች አመራረጥና የናሙና መጠን……………………………………28
3.3.1 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ……………………………………………..28
3.3.2 የመምህራን፣ ርእሰመምህራንና የወላጅ ተወካዮች አመራረጥ……..……..…29
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች…………………………………………………29
3.4.1 የጽሑፍ መጠይቅ………………………………………………………...29
3.4.2 ቃለመጠይቅ………………………………………………………………30
3.4.3 የክፍል ምልከታ……………………………………………………….…30
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ…………………………………………………….…31
**ምዕራፍ አራት**………………………………....……………………......…32
4 የጥናቱ መረጃዎች ትንተና ………………………………………………………32
4.1 የጥናቱ መረጃ አቀባዮች ግላዊ መረጃዎች ትንተና……………………………33
4.1.1 የመረጃ አቀባይ ተማሪዎች እድሜና ጾታ……………………………………..33
4.1.2 የመረጃ አቀባይ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ችሎታ………………..………33
4.1.3 የመረጃ አቀባይ ተማሪዎች ወላጆች የትምህርት ዳራ……………………………34

4.1.4 የመረጃ አቀባይ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጋልጦ.............................35
4.1.5 ተጠኚዎች በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መጻፊያ (ቁቤ) ያላቸው ተነሳሽነት..................36
4.2 አፋን ኦሮሞን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በትምህርት መስጫነት በመጠቀም
ረገድ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮች.......................................................................36
4.2.1 ከትምህርት የይዘት አቀራረብ ጋር የተያያዙ ችግሮች..............................37
4.2.2 ከመማሪያ አውድ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ድጋፍ አሰጣጥ ጋር የተገናኙ ችግሮች...40
4.2.3 ከመምህራን ስልጠና ጋር የተያያዙ ችግሮች..........................................42
4.2.4 ቁስ አካላውያን የትምህርት ግብአቶች ስልጠና ጋር የተያያዙ ችግሮች...........46
4.2.5 ከወላጆች የትምህርት ድጋፍ ጋር የተያያዙ ችግሮች.................................49
4.2.6 ከፖለቲካዊ እሳቤ ጋር የተያያዙ ችግሮች...............................................50
4.2.7 ከክፍል ምልከታዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና.....................................51
4.2.7.1 የክፍል ምልከታ ውጤቶች ማብራሪያና ማጠቃለያ...................................55
4.3 በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ የሚታዩ የመማር ማስተማር
ሂደት ችግሮች መንስኤ ምክንያቶች...............................................................57
4.3.1 ከመምህራን አሰራር ጋር የተገናኙ ተግዳሮቶች መንስኤዎች........................57
4.3.2 ከተማሪዎች ባህሪ ጋር የተገናኙ ችግሮች መንስኤዎች...............................58
4.3.3 ከሌሎች የትምህርት ባለድርሻዎች ጋር የተገናኙ ችግሮች መንስኤዎች...........59
4.3.4 ኢኮኖሚያዊ መንስኤ ምክንያቶች.......................................................61
4.4 ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ወላጆች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት.62
4.5 የጥናቱ ውጤቶች ማብራሪያ..............................................................67
**ምዕራፍ አምስት**.................................................................................76
5 የጥናቱ ግኝቶች፣ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች ጥቆማ...............................76
5.1 የጥናቱ ግኝቶችና ማጠቃለያ..............................................................76
5.2 የመፍትሄ ሃሳቦች ጥቆማ...................................................................79
ዋቢ መጻህፍትና ጽሁፎች..........................................................................82
አባሪዎች............................................................................................85

# የሰንጠረዥ ማውጫ

**ርእስ** **ገጽ**

ሰንጠረዥ 1፡-የተጠኚዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ዳራ…………………………….……….33
ሰንጠረዥ 2፡-የተጠኚዎቹ ወላጆች የትምህርት ዳራ………………………..…………..34
ሰንጠረዥ 3፡-የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ይዘት አቀራረብ
ዙሪያ ስላሉ ተግዳሮቶች የሰጧቸው ምላሾች…………………………………………..37
ሰንጠረዥ 4፡-የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ ስለሚያገኙት
ድጋፍ የሰጧቸው ምላሾች……………………………………………………40
ሰንጠረዥ 5፡-የጥናቱ ተሳታፊዎች ከመምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር
ተበረታችነት ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች የሰጧቸው ምላሾች…………………………………42
ሰንጠረዥ 6፡-የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ስላሉ የሰው ሃይልና
ቁሳቁሳዊ ተግዳሮቶች የሰጧቸው ምላሾች……………………………………………46
ሰንጠረዥ 7፡-የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ዙሪያ የወላጆችን ድጋፍ
በተመለከተ የሰጧቸው ምላሾች………………………………………………………49
ሰንጠረዥ 8፡-የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ሰላላቸው አመለካከት
የሰጧቸው ምላሾች…………………………………………………………………62

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ተማሪዎች ስለሚማሩት የቋንቋ ትምህርት የተሻለ አስተማማኝ መረዳት እንዲኖራቸው እንዲሁም የሚማሩበትን ተገንዝበው ሌሎች የትምህርት አይነቶችን በውጤታማነት እንዲማሩ፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊ በመሆን ራሳቸውንም በራስ መተማመን እንዲገልጹ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት አውድ በአፍ መፍቻ ቋንቋ በበርካታ ምሁራን የተደገፈ ጽንሰ ሃሳብ ሲሰራበት ቆይቷል (Khejeri፣ 2014፣ Young, 2009 Altaye, 2001)፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎቹ የሚማሩበት ታላሚ ቋንቋ ለተማሪዎቹ የትምህርት ውጤታማነት በጣም ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት የአፍ ቋንቋ የመማሪያ ቋንቋ አድርጎ ማቅረብ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ከመሆኑ አኳያ ተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን አሃዶች ግንዛቤ በማዳበር ለሁለተኛ እና የውጭ ቋንቋ ትምህርት መልካም የልምድ መነሻ ይፈጥርላቸዋል፡፡ ስለሚማሩት ትምህርት በግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ተነሳሽነትና በራስ መተማመን ኖሯቸው በመማር ሂደት ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያግዛቸዋል፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ቋንቋ ከመማራቸው በፊት የአፍ መፍቻ ቋንቋ የዳበረ ግንዛቤ ሁለተኛ ቋንቋን በተሻለ ለመማርም ሆነ ሌሎች የትምህርት አይነቶችን በጥሩ ሁኔታ ለመረዳት ሁነኛ አስተዋጽኦ እንዳለው Coombs (1984)ን ጠቅሰው Altaye (2001)፣ UNESCO (2005) ይገልጻሉ፡፡

Young (2009)፣ Altaye (2001)፣ በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት እርከን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማር ጠቀሜታ እንዳቀረቡት ገለጻ አፍ መፍቻ ቋንቋን በመማሪያ ቋንቋነት የመወሰን ምርጫ በበርካታ የቋንቋ ምሁራን የተደገፈ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በበርካታ ምሁራን የሚቀርበው መከራከሪያ ነጥብ አጽንኦት ያደረገው የተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት እርከን የመማሪያ ቋንቋ ተደርጎ በሚቀርብበት አውድ አቀላጥፎ የመማርና የሚማሩትን ነገር በሚገባ የመረዳት ችሎታቸው ከፍ ይላል፡፡ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማርን በሚገባ ሳያዳብሩ በሁለተኛ ቋንቋቸው

በመማር ያን ያህል ስኬታማ ሊሆኑ እንደማይችሉ፣በሌላ ቋንቋ የማንበብም ሆነ ትምህርቱን የመገንዘብ ብቃታቸው አስተማማኝ እንደማይሆን ይጠቁማሉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ Khejeri (2014)፣ UNESCO (2005) በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መስጠት እያንዳንዱ ተማሪ የራሱን ባህልና እሴቶች ለይቶ እንዲያውቅና ማንነቱን በተሻለ ሁኔታ በመቅረጽ ሌሎች ባህሎችን ለማወቅ ምቹ እድሎችን እንደሚፈጥርለት ይገልጻሉ ፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በህጻኑ ቀዳሚ የትምህርት እድሜ ማቅረብ እውቀትን በተገቢ ሁኔታ ለመቅሰም ያለው ጠቀሜታ ከፍ ያለ ነው (Elliot, 2003፣ Cook & Cook, 2005)፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በመማሪያነት ማቅረብ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማነትም ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ ተማሪዎች አፍ በፈቱበት ቋንቋ መማር መጀመራቸው ራሳቸውን በተሻለ እንዲገልጹ፣ ተግባቦታዊ ችሎታቸው እንዲያድግ፣ በሃሳብ ደረጃ ተጽእኖ ማድረግ እንዲለምዱ፣ ነገሮችንና ሁኔታዎችን በሚገባ እንዲለዩ፣ እንዲያወዳድሩ አቅም ይገነባላቸዋል (Heugh, et al, 2007)፡፡

ምንም እንኳን በአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን አፍ መፍቻ ቋንቋን የመማሪያ ቋንቋ ማድረግ ለተማሪዎች ስነ-ትምህርታዊ (አካዳሚያዊም)ሆነ የሰብእና እድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ ቢታመንም፤ ውጤታማነቱን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ተግዳሮቶች የትምህርት መሳሪያ ዝግጅት፣ የመምህራን ስልጠና፣ የጽህፈት ሥርአት፣ በቂ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላት ምስረታ፣ የተማሪዎች ዝግጁነትና ማህበረሰባዊ አመለካከት፣ አካባቢያዊ ምቹ ሁኔታና የመሳሰሉት ጉዳዮች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ አውድ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያደርጉ እንደሚችሉ Khejeri (2014)፣ Cohen (2000) Altaye (2001) ያስረዳሉ፡፡

በአፍሪካ እና በበርካታ የአለም ሀገራት ያለው በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጅማሮ ልምድ እንደሚያመለክተው የተማሪዎች አእምሮታዊ እድገት (cognitive development) በፍጥነት ሊዳብር የሚችለው የአፍ መፍቻ ቋንቋን የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ በማድረግ ነው (Brown, 2007)፡፡ ይህም ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በሚጀምሩበት እርከን ላይ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማራቸው ትምህርቱን በሚገባ ለመረዳት ይበልጥ የሚያግዛቸው መሆኑን ነው፡፡ በዚህ የትምህርት እርከን ላይ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማራቸው የሚሰጧቸውን መመሪያዎች በሚገባ መገንዘብ ስለሚያስችላቸው በትምህርቱ ሂደት ንቁ ተሳታፊ ያደርጋቸዋል፡፡

የጥናት ግኝቶች እንደሚያመለክቱት በጣም አዋጭ የሆነው የህጻኑ የመማሪያ መንገድ (medium) የአፍ መፍቻ ቋንቋ ነው (Seyoum, 2009)፡፡ በSeyoum እንደቀረበው ገለጻ በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ በትምህርት ሂደት የመጀመሪያ ቋንቋን መጠቀም ለተማሪዎች ውጤታማነት ወሳኝ ነው፡፡ የጥናት ውጤቶች እንደሚጠቁሙት የተማሪዎቹን የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ከማቅረብ ጋር የአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን ሁለንታዊ የመማሪያ ቋንቋ ማድረግ ተገቢ ነው (Brown, 2007)፡፡

ከፍ ሲል ከቀረቡት ሀሳቦች በተቃራኒ እንደ Baker (1988) ያሉ ምሁራን በርካታ ብዝሃ ቋንቋ ባሉባቸው ሀገሮች በርካታ አፍ መፍቻ ቋንቋዎችን ስራ ላይ ከማዋል መብት ጋር ተያይዞ የትምህርት ወጪና የትግበራ ችግሮች መኖራቸውን ለሙግት ያቀርባሉ፡፡ በሌላም በኩል ተማሪዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውጪ ባሉ ሌሎች ቋንቋዎች መማር የሚመርጡት በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ያለውን ጠቀሜታ ጠንቅቆ ባለመረዳትና ያለምንም መረጃ አስቀድሞ በሚያዝ መጥፎ ሃሳብ (prejudice) የተነሳ ነው (Holmes, 1992)፡፡ የቋንቋ አለመውደድ የሚነሳው ከፖለቲካዊ አድሎ (political bias)፣ በማህበራዊ አከፋፈል (social stratification)፣ በኢኮኖሚያዊ ልዩነት (economic incongruity) እና በሌሎች ማህበራዊ-ስነልቦናዊ መንስኤዎች ነው (Khejeri, 2014፣ Cohen, 2000)፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት እንዲሰጥ ተወስኖ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እየተተገበረ ቢሆንም፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎችን ለትምህርት መስጫነት ስለመጠቀም አዎንታዊና አሉታዊ አመለካከቶች በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ እንደሚታይ Seyoum (2009) ይገልፃሉ፡፡ ቋንቋ የአንድ ሀገር ባህላዊና ሁለንተናዊ ማንነት የማንፀባረቂያ ቁልፍ መሣሪያ ሆኖ የመገኘት ገጽታ ወደ ራስ ቋንቋ በመመለስ ለእድገትና ለተለያዩ ፈጠራዎች በማዋል የትምህርት መሠረታቸውን፣ ባህላቸውን፣ ምጣኔ ሀብታቸውን ማህበራዊ መስተጋብራቸውንና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምጥቀታቸውን በማይናጋ መሠረት ላይ አንፀው በተምሳሌትነት የምናነሳቸው ቻይና፣ ጃፓንና ጀርመን ተጠቃሽ እንደሆኑ Ogutu (2006) ይገልፃሉ፡፡ ይህ ጥናት የሚያተኩረውም በአፋን ኦሮሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እርከን የትምህርት መስጫ ቋንቋ ሆኖ እየተተገበረ ባለበት ሁኔታ ያጋጠሙትን መሰረታዊ ችግሮች መመርመር ላይ ይሆናል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የአፍ መፍቻ ቋንቋን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መሰረት ማድረግ በበርካታ የአለም ሀገራት በሰፊው ተቀባይነት ያገኘ የብዝሃ-ቋንቋ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በብዝሃ ቋንቋ ህብረተሰብ የቋንቋ ፖሊሲና የቋንቋ አጠቃቀም በተናጋሪው ግለሰብ የእለት ተእለት ህይወትና መስተጋብር ላይ ጉልህ ተጽእኖ የሚያሳድር በመሆኑ ነው (UNESCO 2005)፡፡ እንደ UNESCO ገለጻ የትምህርት ሥርአት አቢይ መርህ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመደገፍ ከመማር ማስተማሩ አውድ እጅግ የበለጠውን ውጤታማነት እንዲቀዳጁ ማስቻል ነው፡፡ አጥኚዋ በዚህ ርእሰ-ጉዳይ ላይ እንድታተኩር ያነሳሳት ምክንያት ከስራ ባልደረቦቿ ጋር ስትወያይ ያገኘችዉ ግንዛቤ ነው፡፡ Ball (2011) እንደገለጹት በአፍ መፍቻ ቋንቋ በማስተማር ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ ከሚችሉ ቁልፍ ጉዳዮች መካከል የወላጆች፣ የተማሪዎችና የመምህራን አመለካከት አንዱ ነው ፡፡ ይህ አስተያየት ምን ያህል እውነት እንደሆነ ለመመርመር አጥኚዋ ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ ጥናቶች ላይ የዳሰሳ ንባብ አካሂዳለች፡፡

ለረጅም አመታት አማርኛ ቋንቋ በብሄራዊ ደረጃ የስራ ቋንቋ ሆኖ ከመቆየቱ ጎን ለጎን በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት እርከን የመማሪያና የበርካታ ኢትዮጵያዊ ማህበረሰቦች እርስ በርሳዊ መስተጋብር የግንኙነት ቋንቋ ሆኖ በስፋት በከተማ ቀመስ አካባቢዎች ሲያገለግል መቆየቱ ገሃድ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ በብዙ ማህበረሰባዊ አካባቢዎች ተማሪዎች ወደትምህርት ቤት ከመላክ ጋር ተያይዞ የቆየው ማህበረሰባዊ አመለካከት አማርኛ ቋንቋን እንዲያውቁ እንጂ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን እንዲያጎለብቱ፣በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማካኝነት የሚማሩትን ትምህርት እንዲገነዘቡ የሚያበረታታቸው ምቹ ሁኔታ አልነበረም:: ይህም በርከት ላሉ አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የመማሩን ሂደት ውስብስብ አድርጎባቸው፤ ተግባቦትና ተሳትፏቸውን እንዲሁም ግንዛቤያቸውን ውሱን አድርጎት እንደቆየ የእነ Beeckman (2005)፣ Ayalew (2000) ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

ወቅታዊው የትምህርትና የስልጠና ሥርአት በግልጽ ባስቀመጠው የብዝሃ ቋንቋ የፖሊሲ ለውጥ የተለያዩ ማህበረሰቦች የራሳቸውን ቋንቋና ባህል እንዲንከባከቡ፣በአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ በመደረግ ላይ ይገኛል (MOE, 1994)፡፡ በዚህም መሰረት በተለያዩ አካባቢዎች ወደ 20 የሚደርሱ ቋንቋዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በማቅረብ ላይ ይገኛሉ፡፡

ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ላለፉት 29 አመታት ወይም በላይ በበርካታ ማህበረሰቦች ዘንድ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ሲሰጥ መቆየቱ ቢታወቅም፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጥራት እንደ ማንበብና መጻፍ አጣርቶ አለመቻል ያሉ ወሳኝ የትግበራ ተግዳሮቶች እንዳሉበት የሚጠቁሙ የ EGRA (Early Grade Reading Assessment) ሪፖርቶች አሉ (UNESCO, 2005)፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በቋንቋ ፖሊሲ እና በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አተገባበር ችግሮች ላይ የሚያውጠነጥኑ ጥናቶች በጣም ውሱን ሆነው ይገኛሉ፡፡ በተለይ የትምህርቱን ስራ በሚያካሂዱ ወይም በሚመሩና በሚማሩ እንዲሁም በወላጆች የመንግስት/ የግል ትምህርት ቤት/ ምርጫና በአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ የትምህርት አቀባበል ችግሮች ላይ ያተኮሩ ጥናቶች ውሱን ሆነው መገኘት የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

በሌላም በኩል በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት እርከን ተማሪዎች ትምህርት የመስጠት አስፈላጊነት ላይ ትኩረት ያደረገው የትምህርት ስርአት የሚገኝበትን ውጤታማነት ብሎም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ ተግዳሮቶችና መንስኤ ምክንያቶች ላይ ያተኮሩ ጥናቶች ተደራሽነት ጥያቄ እንዳለበት የአጥኚዋ እምነት ነው፡፡ በተለይ በጥናቱ አካባቢ በአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋነት እየተተገበረ ስላለው ትምህርት ከዚህ ቀደም የተሰሩ ጥናቶች እምብዛም አለመኖራቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት አጥኚዋ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ምርምር ለማካሄድ ተነሳስታለች፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች በተሟላ ሁኔታ እንደሚመልስ ይታመናል፡፡

1. በማና ወረዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አፋን ኦሮሞን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ረገድ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች ምን ምንድናቸው?

2. በማና ወረዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ የሚታዩ የመማር ማስተማር ሂደት ተግዳሮቶች መንስኤ ምክንያቶች ምን ይመስላሉ?

3. በማና ወረዳ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ወላጆች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

## 1.4 የጥናቱ አላማዎች

### 1.4.1 የጥናቱ አቢይ አላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ በጅማ ዞን በማና ወረዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አፋን ኦሮሞን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ረገድ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን መተንተን ነው፡፡

### 1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፡፡

- በማና ወረዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ የሚታዩ ተግዳሮቶችን መፈተሽ፤
- በማና ወረዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ የሚታዩ የመማር ማስተማር ሂደት ተግዳሮቶች መንስኤ ምክንያቶችን መለየት፤
- በማና ወረዳ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ወላጆች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል መተንተን፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማር ሂደት ላይ ተግዳሮት የሆኑ ስነ-ትምህርታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ስነልሳናዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች እንዳሉ Birgit (2010) ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ተግዳሮቶች ደግሞ በትምህርት ጥራቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ በዚሁ መሰረት ይህ ጥናት ከሚመልሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎችና ከሚደርስባቸው የመፍትሄ ሃሳቦች አንጻር የሚከተሉት ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ይታመናል፡፡

1. በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት ዙሪያ ጥናቱ የሚያቀርባቸው ችግሮች፣ የችግሮቹ ምንጮችና የመፍትሄ ሃሳቦች የትምህርት አመራሩን ለሚያቅዱና ለሚመሩ ውሳኔ ሰጪዎች እይታ የሚሆኑ በጥናት የተደገፉ ሃሳቦችን ለመጠቆም ይረዳል፡፡

በዚህ መነሻነት የጥናቱ ውጤት ለትምህርት ባለሞያዎችና ሀላፊዎች፣ ለስርዓተ ትምህርትና መማሪያ መጽሀፍት አዘጋጆች ጠቃሚ የሚሆን መረጃ ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህ ደግሞ የትምህርት ጥራቱን ለማሻሻል የተለያዩ የትምህርት ባለድርሻዎች ለሚያደርጉት ጥረት ቅንጅት ገንቢ የሆነ ሚና ይኖረዋል ተብሎ ታምኖበታል፡፡

2. በአንደኛ ደረጃ ትምህርት አውድ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተስተምህሮ ዙሪያ (በመማር ማስተማሩ ሂደት) የሚታዩ አበረታች ልምዶች /ካሉ/ እና ተግዳሮቶችን ለይቶ በማቅረብ ገንቢ ክንውኖች ይበልጥ የሚጠናከሩበትን እንዲሁም የትግበራ ክፍተቶች ተሻሽለው ወይም ተሟልተው ስለሚቀጥሉበት ሁኔታ በተለይ ለመምህራንና ለትምህርት ቤት ኃላፊዎች በጥናት የተደገፈ ጥቆማ ያቀርባል፡፡ በዚህ ረገድ ለአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አተገባበር መሻሻል የበኩሉ ስትራቴጂያዊ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል ይታሰባል፡፡

3. ተማሪዎች፣ መምህራንና ወላጆች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል በመተንተን ለመምህራንና ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ መረጃ ይሰጣል፡፡

4. ወደፊት በአፋን ኦሮሞም ሆነ በሌሎች አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቶች አተገባበር ዙሪያ ጥናት ለማካሄድ ለሚነሱ ተመራማሪዎች መነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ በተጨማሪም በመስኩ ሰፋ ያለ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች በተዛማጅ ጽሁፍነት እንደ መነሻ ሊያግዝ ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ ከጥናት ርእሰ ጉዳይ (ይዘት) እንዲሁም ከጊዜ አንጻር የተቃኙ ውሱንነቶች አሉበት፡፡ ይህን ጥናት ከቦታ አንጻር በክልል ወይም በዞን ደረጃ ማካሄድ የጥናቱን ተደራሽነትና የውጤት አስተማማኝነት ይበልጥ ከፍ ለማድረግ እንደሚረዳ የአጥኚዋ እምነት ነው፡፡ ይሁንና በጥናቱ ወቅት በሀገሪቱ ተከስቶ ባለው የኮሮና ወረርሽኝ የተነሳ በተለያዩ አካባቢዎች እንደልብ ተንቀሳቅሶ መረጃ ለመሰብሰብ ስላልተቻለ ብሎም በሰፊ ማህበራዊ አካባቢ ጥናቱን ለማስደገፍ ከሚጠይቀው መጠነ-ሰፊ የገንዘብና የጊዜ ፍጆታ አኳያ ጥናቱን በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በማና ወረዳ በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መወሰን አስፈልጓል፡፡

በዚሁ መሰረት ጥናቱ በማና ወረዳ ከሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአመቺ ናሙና በተመረጡት በስድስት/6/ ትምህርት ቤቶች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ እነርሱም፡- ሰሞዶ፣ ሳረዶ፣ ቢሊዳ፣ ገሩኬ ጅማቴ፣ ቡጡሬ እና ቡሩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ይህ ጥናት ያተኮረው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት እርከን የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋን እንደ አንድ የትምህርት አይነት በመማርና በዚሁ የአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን አፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋን የትምህርት ማቅረቢያ አድርጎ በመጠቀም ረገድ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በመመርመር ላይ የተወሰነ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ጥናቱ ከአፍ መፍቻ ቋንቋዎች መካከል አፋን ኦሮሞ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጓል፡፡ ጥናቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማር ሂደት ላይ ተግዳሮት የሆኑ ስነ-ትምህርታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ስነልሳናዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ አትኩሯል፡

ይህ ጥናት ከጊዜ አንጻር በ2013 ዓ.ም በማና ወረዳ በሚገኙ ስድስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ባሉ ተማሪዎች፣ ከክፍል ደረጃ አንጻር በአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን በሁለተኛ ሳይክል ደረጃ ትምህርታቸውን በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋነት በሚከታተሉ የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በአንጻራዊ ረዘም ላሉ አመታት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አውድ የቆዩ በመሆናቸው በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ በታችኛው የክፍል ደረጃ ካሉ ተማሪዎች አንጻራዊ የተሻለ የመማር ተሞክሮ ያላቸው እንዲሁም መረጃ መሰብሰቢያውን በጥንቃቄ አንብቦ ለመረዳት ይችላሉ ተብለው ታስበዋል፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላት አውዳዊ ፍቺ

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት** (Mother-Tongue Education):- ህጻኑ በትምህርት መጀመሪያ እድሜው ላይ ከተወለደ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመግባቢያነት የተጠቀመበትን የወላጆቹን ቋንቋ መጠቀሙን ያመለክታል፡፡ በትምህርት መጀመሪያ እድሜ ላይ ህጻናት በመጀመሪያ /የእናት/ ቋንቋቸው መማር ያለባቸው ስለመሆኑ አለማቀፋዊ ስምምነት አለ፡፡

**ተግዳሮት** (Challenge):- በዚህ ጥናት ውስጥ በብዝሀ ቋንቋ ህብረተሰብ በአንደኛ ደረጃ መማሪያ አውድ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ እንቅፋት የሚደቅኑ ችግሮችን ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናትና ተዛማጅ ጥናቶች ፍተሻ

### 2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ምንነት

በCalvet (2006) ገለጻ መሰረት የአፍ መፍቻ ቋንቋ (የመጀመሪያ ቋንቋ እየተባለም ይጠራል) አንድ ህጻን ከመወለድ በኋላ በቀጥታ የሚለምደው ከሌሎች ቋንቋዎች አስቀድሞ በዋንኛነት የሚለምደው ወይም የሚማረው ቋንቋ ነው፡፡ በየጊዜው የተነሱ የስነቋንቋ ተመራማሪዎችና የትምህርት ባለሙያዎች አንደኛ ቋንቋ (L1) ዋንኛ ቋንቋ የእናት ቋንቋ በሚሉ መጠሪያዎች ከሁለተኛ እና ሌሎች የውጭ ቋንቋዎች ይለዩታል፡፡ Calvet (2006) አክለው እንደሚሰጡት ገለጻ አፍ መፍቻ ቋንቋ የሚለው ጽንሰሀሳብ አንድ ሰው የግዴታ ከወላጁ ብቻ የሚማረው ወይም የሚወርሰው ላይሆን ይችላል፡፡ በቤት ውስጥና በመኖሪያ አካባቢ በስፋት የሚነገረውን ቋንቋ ሁሉ ያካትታል፡፡ ለምሳሌ፡-አንድ ጣሊያን ሃገር የተወለደ ህጻን ገና በአንድ ወይም ሁለት አመት እድሜው ከወላጆቹ ጋር ወደ እንግሊዝ አገር የመሄድና በእዚያ የመኖር እድል ቢያጋጥመው አፍ መፍታት በሚለምድበት ጊዜው ላይ በአካባቢው በስፋት የሚነገረውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከእናቱ ቋንቋ በበለጠ አቀላጥፎ መናገር ይለምድ ይሆናል፡፡ በአካባቢያዊ ተጽእኖ የተነሳ ህጻኑ በቀዳሚነት አቀላጥፎ የመናገርና የመግባባት ችሎታ የተቀዳጀበት ቋንቋ ከእናቱ ቋንቋ ቢለይም የመጀመሪያ ቋንቋው ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ከመምጣታቸው በፊት መማር የሚጀምሩት ከቤተሰባቸውና ከአካባቢያቸው ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ቋንቋ ወሳኝ መሳሪያ መሆኑን Wells (1994) ያስረዳሉ፡፡ ይሁንና ህጻናት ከቤተሰባቸውና ከአካባቢያቸው መማርን የሚጀምሩበት ቋንቋ የመጀመሪያ ወይም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ይባላል፡፡ ስለመጀመሪያ ወይም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመዳ ሂደት በዘርፉ ምሁራን የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች ይቀርባሉ፡፡ በባህሪያውያን አመለካከት በመጀመሪያ አንድ ህጻን በአካባቢው የሰማውን ድምጽና የድምጽ ቅላጼ ለማስመሰል ይሞክራል፡፡ ይህንን ተከትሎ ከልጁ ጋር ያሉ ወላጆች የልጁን ሙከራ በመስማት በደንብ እንዲናገር ያሰለጥኑታል፤ ወይም ያበረታቱታል፡፡ ብሎም ከተሳሳተ ያርሙታል፡፡ በመቀጠል ህጻኑም የሚሰማውን ማበረታቻ በመጠቀም ቋንቋውን

በበለጠ ለመናገር ጥረት ያደርጋል፡፡ በሂደትም ህጻኑ የቋንቋውን ባህሪ ይለምዳል፣ ወይም በትክክለኛ መንገድ ይቀረጻል፡፡ ይሁን እንጂ ቋንቋን የመማር ሂደት ከህጻንነት ጀምሮ እስከ ጎልማሳነት የማያቋርጥ ነው በማለት Hallidy (1993) ያስረዳሉ፡፡

ህጻናት ቋንቋን ከቤተሰባቸውና ከአካባቢያቸው ብቻ ሳይሆን ትምህርት ቤት ገብተውም ይማራሉ፡፡ ነገር ግን በትምህርት ቤት ውስጥ ቋንቋንም ሆነ ሌሎችን እውቀቶች የሚማሩበት ስልት ከቤተሰባቸውና ከአካባቢያቸው ከሚማሩበት ስልት የተለየ ነው፡፡ ሆኖም ግን የቋንቋ ለመዳ ሂደትን ጠቅለል አድርጎ በአራት ደረጃዎች መግለጽ እንደሚቻል Hallidy (1993) ይገልጻሉ፡፡ በቤተሰባቸውና በአካባቢያቸው ላይ ባለማወቅ ውስጥ የሚካሄድ መማር፣ ለእለት ተእለት ግንኙነት አስፈላጊ የሆነ የተግባቦት ቋንቋን የመማሪያ እድሜ ፣ ወደ ትምህርት ቤት በመግባት ከጽህፈት ቋንቋና ከትምህርታዊ እውቀት ጋር ለመተዋወቅ የሚደረግ የሽግግር ጊዜና ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት ቀጣይነት ባለው መንገድ የተለያዩ የትምህርት ዘርፎችን ሙያዊ እውቀቶች የመማሪያ ደረጃ ናቸው፡፡

ህጻናት ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ትምህርት ቤት ይገባሉ፡፡ በዚህ ወቅት ተማሪዎች ትምህርት ቤት ከመምጣታቸው በፊት ከነበራቸው የመማር ስልት የተለየ የመማር ስልት በትምህርት ቤት እንደሚቆያቸው Wells (1994) “Language-Based Theory of Learning” የተሰኘውን የሀሊደይና ቪጎትስኪን ስራ በመጥቀስ ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም ሳይንሳዊ ካልሆነ ባለማወቅ ውስጥ ከሚካሄድ የመማር ስልት ሳይንሳዊ ወደ ሆነ የመማር ስልት የሚካሄድ የሽግግር ወቅት ነው፡፡ የመማር ስልቱ ቢቀየርም የሚማሩበት ቋንቋ ግን መቀየር የለበትም በሚል የዘርፉ ምሁራን ይመክራሉ፡፡ ይህውም በዋናነት ከመማር ስልት በተጨማሪ ስነ ልሳናዊና ስነ ልቦናዊ ተግዳሮቶች በመማር ሂደቱ ላይ ተጨማሪ ጫና እንዳይፈጥሩ ነው በሚል Alidou (2006) ይገልፃሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በዘርፉ ምሁራን ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ይልቅ ሌላ የሰለጠነ ቋንቋን ለትምህርት መስጫነት መጠቀሙ ለመማር ማስተማሩ ሂደትም ሆነ ለተማሪዎቹ ቀጣይ ስኬት የተሻለ ነው የሚል የመከራከሪያ ሀሳብ ይቀርባል፡፡ የመከራከሪያ ሀሳቡም በዋናነት ከአለም አቀፋዊ ግንኙነትና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት የሚመነጭ ነው፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋን ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማ እንዲሆን በተለይም መምህራን የተለያዩ የማስተማር ስነ-ዘዴና ሥልቶችን ሊከተሉ ይገባል፡፡ መምህራኑ በተግባቦታዊ እና አሳታፊ የትምህርት አሰጣጥ ማሰልጠንና በአፍ መፍቻ ቋንቋ

ብቃታቸውን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ ህፃናት በርካታ የንግግርና የፅሑፍ ልምምዶችን እንዲያደርጉና በራሳቸው ቋንቋ መተማመንን እንዲያዳብሩ የማድረግ፣ የመጀመሪያቸውን አንድ ዓመት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ብቻ ንግግርና የፅሁፍ ክህሎቶችን እንዲማሩ ማድረግና በዚህ ደረጃ እያሉ የሌላውን የቋንቋ ትምህርት ማዘግየት ወይም የንግግር ክህሎትን ብቻ ማስተማር ያስፈልጋል በማለት Alidou (2006) ያስረዳሉ፡፡

## 2.1.2 የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለመጠቀም አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች

የአፍ መፍቻ ቋንቋን የመጠቀም ፍላጎት አነሳሽ ምክንያቱ ቋንቋንና ባህልን ከመጥፋት ለማዳን ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ማህበረሰብ ከሌሎች የማንነት መገለጫዎች ሁሉ በበለጠ ቋንቋን የባህሉና የእሴቱ ማስቀጠያ መሳሪያ አድርጎ ይመለከተዋል፡፡ ይህን ተከትሎም ቋንቋው የትምህርት መስጫ ቋንቋ እንዲሆን ሊወስን ይችላል በማለት Jacob (2015) ይጠቁማሉ፡፡ ምክንያቱም ከመጀመሪያው ቋንቋውን የመጠቀም አነሳሽ ምክንያትና ግብ ቋንቋንና ባህልን መጠበቅ እንጂ ስነትምህርታዊ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ቋንቋንና ባህልን ለማዳን በሚል የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ተግባራዊ ማድረግ ብዙ ጊዜ የሚማሩ ልጆችን መግደል ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋንም ሆነ ሌሎች ቋንቋዎችን እንደ ትምህርት ስለመማርም ሆነ በመማሪያ ቋንቋነት ስለመጠቀም ተማሪዎች የሚኖራቸው የተነሳሽነት ምክንያቶች ውጫዊና ውስጣዊ በሚል በሁለት ሊከፈሉ እንደሚችሉ Dornyei (1998) ይገልጻሉ፡፡ውጫዊ ምክንያቶች ሲባል የወላጅ ፣የመምህራንና የእኩዮች ተጽዕኖ አንዱ ሲሆን ተማሪዎች በቋንቋው በሚማሩበት ወቅት የሚያገኙት ሽልማት፣ የሚደርስባቸው ቅጣት ወይም ማዕቀብና ከሌሎች የሚገኝ ግብረመልስ ደግሞ ሌላው ነው፡፡ ማህበረሰቡ ለቋንቋው ያለው አመለካከት ከማህበረሰቡ ባህልና ከአካባቢው የትምህርት ሁኔታ ጋር ያለው ተዛምዶ ተያይዘው ይነሳሉ፡፡ ውስጣዊ ምክንያቶች የሚባሉት በቋንቋው ሲማሩ የሚያጋጥም ጭንቀት ፍርሃት በራስ መተማመን ለቋንቋውና ለቋንቋው ማህበረሰብ ላይ ያለ የቀደመ አመለካከት ለራስ የሚሰጥ ግምትና በቋንቋው ላይ የሚታይ ችሎታ ተጠቃሽ እንደሆኑ Dornyei (1998) አያይዘው ይገልጻሉ፡፡

በአንድ ሀገር ወይም ማህበረሰብ ውስጥ የትምህርት ስርዓት ሲታሰብ አይቀሬው ጉዳይ የትምህርት መስጫ ቋንቋ ምርጫ ነው፡፡ ምርጫው የሚከናወነው ከአፍ መፍቻ ፣ ከሁለተኛና ከውጭ ቋንቋዎች መካከል ሊሆን ይችላል፡፡ ከመምረጫ ምክንያቶች መካከል በተለይ በአፍሪካ ርዕዮተዓለም ብሄርተኝነት፣ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ስነልሳንና ስነትምህርታዊ ምክንያቶች ዋነኞቹ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ የቋንቋ አመለካከት ሌላው ምንጭ ቀረቤታ ተነሳሽነት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም የሌላ ማህበረሰብ ባህልን በማድነቅ በአኗኗር በመማረክና ከእነሱ ጋር ለመቀራረብ ወይም የማህበራዊ ህይወት ተጋሪ ለመሆን ተነሳስተው ከራሳቸው ቋንቋ ይልቅ በሚያደንቁት ማህበረሰብ ቋንቋ መማር ማስተማርን ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ ወይም ደግሞ በራስ ቋንቋ እራስን ለመግለጽና ለማስተዋወቅ በመፈለግ በራስ ቋንቋ የመማር ማስተማር ተነሳሽነት ሊፈጠር ይችላል በማለት Dornyei (1998) አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከትን በአፍ መፍቻም ቋንቋ ላይ ያስከትላል ይላሉ፡፡

### 2.1.3 የአፍ መፍቻ ቋንቋን የመማሪያ ቋንቋ የማድረግ ጠቀሜታ

እንደ UNESCO (2005) ገለጻ ሀገር በቀል የሆነንና በበርካታ ተናጋሪዎች ተግባቦት የሚካሄድበትን ቋንቋ በትምህርት መጀመሪያ እድሜ በመማሪያ ቋንቋነት መጠቀም የህጻኑን ግለ-ሰብእናዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ማንነት ለመገንባት አስተዋጽኦ አለው፡፡ ህጻኑ በአፍ መፍቻ ቋንቋው መማሩ ጥልቅ አስተሳሰብና የስነጽሁፍ ክህሎት እንዲያሳድግ የራሱ እገዛ ያደርግለታል፡፡ ጥናቶች እንዳመላከቱት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የሚከታተሉ ልጆች ትምህርቱን የተሻለ የመረዳት ችሎታ ያሳድጋሉ፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋን የመማሪያ ቋንቋ የማድረግ ጠቀሜታ በስፋት ጥናት የተካሄደበት ጉዳይ ነው፡፡ በበርካታ ጥናቶች እንደተመለከተው ህጻናት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ሲያበለጽጉ እግረ መንገዳቸውን ሌሎች አስፈላጊ እንደ ጥልቅ አስተሳሰብ (critical thinking) የማንበብና የመጻፍ ክህሎቶችን አብረው ያሳድጋሉ፡፡ እነዚህ ክህሎቶች በመደበኛ ትምህርት መስክ አብረዋቸው የሚጓዙና ተፎካካሪ ተማሪ የሚያደርጓቸው በመሆናቸው በሌሎች ቋንቋዎች ደግመው አስበው ለመረዳት ከመፍጨርጨር የሚታደጓቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ተማሪ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የቃላትን ፍቺ ከአውድ በመረዳት ረገድ ወይም በንባብ ጊዜ በመስመሮች መሃል በማንበብ ከመረጃዎች በመነሳት ትርጉምን መወሰን (infer meaning) ይሞክራሉ፡፡

በዚህ ወቅት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ያካበቱት እውቀት በሁለተኛ ቋንቋ አውድ ሊገጥማቸው የሚችለውን ውስብስብነት ያቃልልላቸዋል (Cummins, 2000)፡፡ Cummins (2000) አክለው እንደጠቆሙት፣ በህጻናት እድገትና በአፍ መፍቻ ቋንቋ መካከል የጠበቀ ዝምድና አለ፡፡ ህጻናት ከሁለተኛ ቋንቋቸው በተሻለ መልኩ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የጥልቅ መረዳትና ራስንና ፍላጎትን የመግለጽ ችሎታ ባለቤት ይሆናሉ፡፡ በCummins መሰረት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ የተመሰረተ የትምህርት አሰጣጥ ለተማሪዎች በርከት ያሉ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

- በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩ ተማሪዎች ራስን በብቃት የመግለጽና ችሎታቸውና በራስ ጥረት የመማር ተነሳሽነታቸው የተሻለ ይሆናል፡፡
- ተማሪዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውጪ ያሉ ሌሎች ቋንቋዎችን የመረዳቱን ሂደት ቀላል ያደርግላቸዋል፡፡
- በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ የተመሰረተ ትምህርት የተማሪዎችን ግለሰብእናዊ ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ማንነቶች ግንዛቤን ያጎለብታል፡፡
- የአፍ መፍቻ ቋንቋን መጠቀም ተማሪዎች ጥልቅ የሆነ አስተሳሰብ ፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታን እንዲያሳድጉ ያደርጋል፡፡
- ጥናቶች እንዳመላከቱት በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር የትምህርቱን አረዳድ የተሻለ ያደርጋል፡፡
- በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ድጋፍ የሚማሯቸው ክህሎቶች ወደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሽግግር በሚያደርጉበት ወቅት በቀላሉ አስታውሰው እንዲጠቀሙባቸው መንገድ ያመቻቹላቸዋል፡፡
- በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ አውድ ምቾት የሚሰማቸው፣ ደስተኛና ንቁ ተሳታፊ በመሆን የሚማሩትን ትምህርት በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመቀበል ያስችላቸዋል፡፡
- በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩ ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት የተጠናከረ ስለሚሆን ትምህርቱን በተመለከተ በቤት ውስጥ በሚያከናውኑት ተግባር የወላጆቻቸውን የቅርብ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡
- በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩ ተማሪዎች የትምህርት ተበረታችነት ከፍተኛ ነው (Cummins, 2000)፡፡

በአጠቃላይ የቋንቋ እውቀት ለአንድ የተወሰነ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ብቻ ሳይሆን በዚያ መደበኛ ቋንቋ ለሚሰጡ ሌሎች የትምህርት አይነቶች ሁሉ ቁልፍ ግልጋሎት አለው፡፡ ለምሳሌ የሂሳብ ትምህርት ይዘትን ብንወስድ ሂሳብን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ቀመሮች፣ ኢኩዌሽኖች፣ ወዘተ መረዳት የሚታሰበው የትምህርቱ ይዘት በሚቀርብበት ቋንቋ አማካኝነት ነው፡፡ ያለ ቋንቋ ሂሳብም ሃሳብም ስሌትም ሊኖር አይችልም፡፡ ያለ አፍ መፍቻ ቋንቋ ከፍ ያለ የመረዳት ችሎታን የሚጠይቁ ክንውኖች ሊተገበሩ አይችሉም፡፡

### 2.1.3.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስነ-ትምህርታዊ (Pedagogical) ጠቀሜታዎች

በCouncil of Europe (2011) እንደተገለጸው የተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማር በርካታ ስነ-ትምህርታዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጥ ትምህርት የተማሪዎችን የእውቀትና የመረዳት ችሎታ ያሳድጋል፤ የሚማሩትን ትምህርት በብቃት ይገበያሉ፤ መረጃ የመቀበልና የተለያዩ መረጃዎችን የማገናዘብ፣ በተለያዩ መረጃዎች መካከል ያሉ ግንኙነቶችንና ልዩነቶች የመመርመር፣ መረጃዎችን የማደራጀት፣ አቅምን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተሻለ ሁኔታ ይገነባሉ፤ ያገኙትን ስነትምህርታዊ መረጃ ከእውኑ አለም ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በቀላሉ ለማዛመድ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

Day & Conklin (2012) በበኩላቸው ስለአፍ መፍቻ ቋንቋ ስነ-ትምህርታዊ ጠቀሜታ ሲያብራሩ፤ የማሰብና የመመርመር፣ የባህል፣ የሞራል፣ የስነ-ውበት፣ የማንነትና እንዲሁም የቴክኖሎጂ ስነ-ትምህርታዊ ምንዝሮችን (components) ከታችኛው የትምህርት እርከን ጀምሮ እየለዩና እየገበዩ ለማደግ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ስነትምህርታዊ ጠቀሜታ በሁለተኛ ቋንቋ ከመማር በጣም የተሻለ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ አክለውም በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማር ሂደት ተማሪዎች የተለያዩ የእውቀት አሃዶችን በማገጣጠም ለነገሮችና ክስተቶች እንዳቅማቸው ትርጉም ለመስጠት ይነሳሳሉ፡፡ የማከናወን ብቃት፣ ችሎታ፣ በጎ አመለካከት፣ እሴትና አዎንታዊ ባህሪን ለማስረጽ አንዲሁም በታላሚው ቋንቋ ከትምህርት ቤት ውጪ ባሉ አውዶች በተነሳሽነት በመገልገል የቋንቋ ብቃታቸውን ለማጎልበት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ የተመሰረተ ትምህርት ምቹ ስነ-ትምህርታዊ መድረክ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

በCouncil of Europe (2011) በቀረበው ገለጻ መሰረት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስነትምህርታዊ ፋይዳ ሲጠቃለል፡-

- በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች ብዙ ነገሮችን በፍጥነት ይገበያሉ፡፡
- አፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች የሚማሩትን መሰረታዊ የማንበብና መጻፍ ክህሎቶች እንዲሁም ትምህርታዊ ይዘቶች ቀላል ያደርግላቸዋል፡፡
- አፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎችን በሚማሩት ትምህርት የተሻለ ውጤታማ ያደርጋቸዋል፡፡
- በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር አንብቦ መረዳትን ያቀላጥፍላቸዋል፡፡
- በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ተማሪዎች በመረዳት ላይ የተደገፈ የክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎን ያመቻችላቸዋል፡፡
- በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል (Council of Europe 2011)፡፡

## 2.1.3.2. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስነልቦናዊ (Psychological) ጠቀሜታዎች

Elliot (2003) የVygotsky ንድፈሃሳባዊ መሰረት መነሻ አድርገው ባቀረቡት ትንተና ማህበራዊ መስተጋብር ለስነአእምሮታዊ እድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ አስረድተዋል፡፡ Vygotsky (1978)ን ጠቅሰው Elliot (2003) ባቀረቡት ትንተና እንዳስረዱት የተሟላ ስነአእምሮታዊ እድገት ለመቀዳጀት የህጻኑ ማህበራዊ መስተጋብር ወሳኙን ሚና ይጫወታል፡፡ የእያንዳንዱ ህጻን ሁለንተናዊ እድገት የባህሉ ውጤት ነው፡፡ ማንኛውም ህጻኑ በባህሉ ውስጥ የሚያሳየው እድገት በሁለት መስኮች ይንጸባረቃል፡፡ የመጀመሪያው ህጻኑ በአካባቢው ካሉ ሰዎች ጋር የሚያካሂደው ስነልቦናዊ ግንኙነት ወይም ተራክቦ ሲሆን ህጻኑ በዚህ ግንኙነት ውስጥ በማለፍ በሁለት መልኩ ስነአእምሮአዊ እድገትን ይቀዳጃል፡፡ አንደኛው ስለባህሉ የሚገበየው አስተሳሰብና እውቀት ሲሆን ሁለተኛው በሚማረው ቋንቋ በከባቢ ባህሉ አማካኝነት አስተሳሰቡን ከፍ ካለ ደረጃ ለማድረስ የሚያደርገው ጥረት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ Ogutu (2006) አንድ ሰው ከተወሰነ ብሔረሰብ ወይም ከአንድ የቋንቋ ተናጋሪ ቡድን ጋር ተወግኖ የሚገለጽበት ቋንቋ እንዳለው በውስጣዊ መገለጫነት ይመድቡታል፡፡ ቻይና፣ ጃፓንና ጀርመን ሀገራቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የማንነታቸው ውስጣዊና ውጫዊ መገለጫ መሆኑን ተቀብለው አጎልብተው የማንነታቸውና የስብዕናቸው መገለጫ እንዲሆንም ተቀብለውታል፡፡

የአንድ ብሔረሰብ ወይም የቋንቋ ተናጋሪ አባል ተደርጎ እንዲወሰድ ወይም ከዚያ ብሔረሰብ ጋር በተዛመደ መልኩ እንዲገለጽ የሚያደርገው ቋንቋ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሆኑን አፅንኦት ሰጥተውት መደላድልን ፈጥረውለታል በማለት Ogutu (2006) ይገልፃሉ፡፡ በሌላ አገላለፅ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ለትምህርት መስጫነት ወይም ለማስተማሪያ ቋንቋነት አውለውት መምህራኑ የሚያስተምሩበት፣ ተማሪዎች የሚማሩበት ማዕቀፍ ተበጅቶለት ተግብረውታል፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትታቸውን የተማሩ ህፃናት ለቀጣይ ትምህርታቸው መሠረት የመገንባት መገለጫ ሲሆን የመጀመሪያ ቋንቋ ማስተማር ጽንሰ ሀሳቦችን እንዲረዱ ይረዳል፤ ወደ ሌሎች የመማሪያ ማስተማሪያ ቋንቋዎች ለመሸጋገር ማንበብና መጻፍ የተማሩ ህፃናት የሁለተኛና የሦስተኛውን ቋንቋ ማንበብና መጻፍ ለመማር የሚያስችላቸው ጠንካራ ማህበራዊ መሸጋገሪያ ድልድይ እንደሆነ Fasold (1984) ያስረዳሉ፡፡ ይህዉም ልጆች በትምህርት ቤት የሚያድርባቸው ፍራቻ ይቀንሳል፤ ትምህርት ቤቱም የበለጠ አሰደሳች ስፍራ ይሆንላቸዋል፤ ፅንሰ ሀሳብን ለማዳበርና የመፍጠር ችሎታን በሚያውቁት ቋንቋ ለማሳደግ ያግዛቸዋል፡፡

Kroskrity (2010) በበኩላቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስነልቦናዊ ጠቀሜታዎችን እንደሚከተለው አጠቃለው አቅርበዋል፡፡

- በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ምቾትና መነቃቃት የሚሰማቸው ሆነው እንዲማሩ ያደርጋቸዋል፡፡
- በአፍ መፍቻ ቋንቋ በሚማሩበት ክፍል ውስጥ ሀሳባቸውን ሳይሸማቀቁና ሀፍረት ሳይሰማቸው ለመምህሩና ለተማሪዎች ለመግለጽ ያስችላቸዋል፡፡
- ተማሪዎች ራሳቸውን በብቃት ለመግለጽና ከሌሎች ጋር ለመግባባትና ግብረ መልስ ለመስጠት ይደፋፈራሉ፡፡
- በሚናገሩት ቋንቋ ስህተት እፈጽማለሁ የሚል ፍርሃት አያሳስባቸውም፡፡
- ከመምህራን ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ያግዛቸዋል፡፡
- በትምህርት ቤት ቆይታቸው የስኬታማነት መንፈስ (sense of success) ያሳድጋሉ፡፡
- አካባቢያቸውን ፣ ባህላቸውንና ማንነታቸውን በራስ መተማመን ስሜት ለመግለጽ ያስችላቸዋል፡፡
- ለሌሎች ሰዎች ጥሩ ግምት እንዲኖራቸውና አክብሮት እንዲያሳዩ ያደርጋቸዋል፡፡

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ለተማሪዎች የሚያቀዳጀው ስነልቦናዊ ጠቀሜታ የሚማሩትን ትምህርት አዎንታዊ ድባብ በሰፈነበት፣ በራስ መተማመን በሚታይበት፣ አቻዊ ተሳትፎና ትምህርታዊ ተራክቦ ጉልህ በሆነበት ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት በምቾት፣ መነቃቃትና መበረታታት ትምህርቱን እንዲከታተሉ ለማድረግ ጉልህ ድርሻ ያለው መሆኑን እንረዳለን፡፡

### 2.1.3.3 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማህበራዊ (Sociological) ጠቀሜታዎች

Dumatog & Dekker (2013) እንዳቀረቡት ገለጻ ፤ በቋንቋና በባህል መካከል ያለው ጠንካራ ትስስር ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አይነተኛ የመነቃቃት ምንጭ ነው፡፡ የትኛውም ቋንቋ ከሌሎች ቋንቋዎች በበለጠ ሁኔታ የራሱን ባህል በብቃት ይገልጻል፡፡ በዚህም የተነሳ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማራቸው የተለየ አድናቆት ያሳድርባቸዋል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቻቸውን ለመግለጽ በእጅ እንዳለ መሳሪያ የሚቆጠር ነው፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት እርከን ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ማድረግ ከፍ ያለ ማህበራዊ ክብር እየተሰማቸው እንዲማሩ ለማድረግ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ጥናቶች እንዳመላከቱት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ የተማሪዎችን አእምሮአዊና ስነልቦናዊ እድገት ከፍ ከማድረግ ጎን የተማሪዎችን ውጤታማነት ለማሻሻል በሌላ ቋንቋ ከመማሪያ አውድ በላቀ መልኩ አይነተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል፡፡ ይህ በራሱ እንደ አንድ ማህበራዊ ግብ የሚወሰድ ስኬት ነው (Kroskrity 2010)፡፡ Kroskrity (2010) በተጨማሪ እንደጠቆሙት ቋንቋ ማህበራዊ ባህልን ለመንከባከብና ለመገንባት ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ በአንድ የተወሰነ ባህል ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ እሴቶችን በሌሎች ቋንቋዎች ተርጉሞ ለማስተማሪያነት ማቅረብ ያን ያህል ቀላል ክንዋኔ አይደለም፡፡ በዚህ የተነሳ ማህበራዊ ባህልን በጥልቀት ለመረዳት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተመራጩ ማህበራዊ ግንዛቤ ማጎልበቻ መሳሪያ ነው፡፡

ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ቢማሩ በላቀ ደረጃ እንዲመራመሩ፣ አዳዲስ ነገሮችን እንዲፈጥሩ፣ ባህላቸውን እንዲያውቁና እንዲፈትሹ፣ እራሳቸውን በቀላሉ ፈልገው እንዲያገኙ፣ ሳይመረምሩ በጭፍን የመቀበል ሂደትን እንዲያስቀሩና ትምህርቱን ከራሳቸው ማህበራዊ አውድ ጋር እንዲያቆራኙ የጎላ ጠቀሜታ ቢኖረዉም የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣

ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ስነ ትምህርታዊና ስነ ልሳናዊ ምክንያቶች በዘርፉ አጥኝዎች ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች በዘርፉ አጥኝዎች ብቻ ተወስነው የሚቀሩ ሳይሆኑ በወላጆች፣ በተማሪዎችና በመምህራን ዘንድ በስፋት ሊታዩ እንደሚችሉ Gardner (1985) ያስረዳሉ፡፡ ይህ ደግሞ በትምህርት ጥራቱ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከፍተኛ ነዉ፡፡

## 2.1.4. የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለመጠቀም ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች

የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ሂደት ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች መካከል በሌላ ቋንቋ ላይ ያለ አመለካከት አንዱ ነው፡፡ የውጭ ቋንቋዎች ብዙ ጊዜ በቅኝ ግዛት፣ በሃይማኖት፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ማደግ በፖለቲካና በኢኮኖሚ የበላይነት የተነሳ በአለም አቀፍ ደረጃ ልቀው የወጡትን እንደ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ፖርቱጊዝኛ ወዘተ ያሉትን የአውሮፓ ቋንቋዎች የሚመለከት ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ Ogutu (2006) እነዚህ ቋንቋዎች በተለይም በአፍሪካ በቅኝ ግዛትና በሌሎች ምክንያቶች የቀደመ ትውውቅ ያላቸው ቢሆንም ለትምህርት መስጫ እንዲውሉ በሚታሰብበት ጊዜ የተለያዩ አመለካከቶች ይነሱባቸዋል፡፡ በአንድ በኩል እነዚህን ቋንቋዎች መጠቀም ከአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን መረጃ ለማግኘት፣ አዳዲስ የሳይንስና ቴክኖሎጅ ውጤቶችን በቀላሉ ለማግኘት ፣ በተለያዩ አካባቢዎች ተንቀሳቅሶ የተሻለ ስራ ለማግኘት ወዘተ የተነሳ በውጭ ቋንቋዎች መማር የተሻለ ነው በሚል አዎንታዊ አመለካከት ይታያል ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል የውጭ ቋንቋዎች ለትምህርት መስጫነት መጠቀም አግባብ አይደለም የሚል አመለካከትም አለ፡፡ ይህ አመለካከት ብዙ ጊዜ የውጭ ቋንቋን ለትምህርት መስጫነት መጠቀም የራስን ባህልና ቋንቋ እንዳያድግ ያደርጋል፤ መምህራኑ የውጭ ካልሆኑ በቋንቋ ብቃት የተነሳ ትምህርቱ ባግባቡ ላይተላለፍ ይችላል የሚል ነው፡፡ ከዚሁ የውጭ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት የመጠቀም አላስፈላጊነት በሚመለከት የታዋቂውን የቅኝ ግዛት ተቃዋሚ ማህተመ ጋንዲን ንግግር በመጥቀስ Wells (1994) የውጭ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት ከተጠቀምን ልጆቻችን በገዛ ሀገራቸው እየኖሩ የውጭ ዜጎች እንዲሆኑ መፍረድ ነው ብለዋል፡፡ በሌላ በኩል ተማሪዎችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ከማስተማር ይልቅ በውጭ ቋንቋ እንዲማሩ ቢደረግ ትምህርት ቤት ከመምጣታቸው በፊት ከቤተሰባቸውና ከአካባቢያቸው የጀመሩት አዕምሯዊና ስነልሳናዊ እድገት ይስተጓጎላል፤ ገና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ በቋንቋ ምክንያት ትምህርት እንዲያቋርጡ ያደርጋል፤ ክፍል ይደግማሉ፤ ብዙ ያልተማረ ሰው በተለይም በገጠር እንዲኖር ምክንያት ሊሆን ይችላል፤

ትምህርቱና የሀገሪቱ ራዕይ እንዳይገናኝ ምክንያት ሊሆን ይችላል በማለት Wells (1994) ያስረዳሉ፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በውጭ ቋንቋ ከማስተማር ይልቅ በሀገርኛ ቋንቋዎች ማስተማር ከትምህርት ገበታቸው የሚያቋርጡና የሚደግሙ ተማሪዎችን ለመቀነስ ይረዳል፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ሂደት ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች የሁለተኛ ቋንቋ አመለካከት ነው፡፡ ሁለተኛ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት ስለመጠቀም የሚኖራቸው አመለካከት የአፍ መፍቻ ቋንቋን ስለመጠቀም በሚኖራቸው አመለካከት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ አለው፡፡ ሁለተኛ ቋንቋን የመጠቀም አመለካከትም እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ሁሉ በታሪካዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል (Alidou., 2006)፡፡ ይህም በዋናነት የተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ የመማር አመለካከት የሁለተኛ ቋንቋውን ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ደረጃ ከራሳቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር በማነጻጸር ከሚሰጡት ግምት ሊመነጭ ይችላል፡፡

## 2.1.5. በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መማር የሚያስገኘው ጥቅም

የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት መጠቀም ከስነልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ትምህርታዊ ፋይዳ አኳያ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ Fasold (1984) ያስረዳሉ፡፡ ይኸዉም ተማሪዎች ቀድመው ባወቁት ቋንቋ ትምህርቱ ከቀረበላቸው በቀላሉ ይረዱታል፤ የትምህርቱ ሂደት ፈጣን ይሆናል፤ ቋንቋ ለማወቅ ከሚል ተጨማሪ ጫና ይድናሉ፤ ከሚል መከራከሪያ ሀሳብ የመነጨ ነው፡፡ በተጨማሪም Mutasa (2006) በቅርብ ጊዜ የተካሄዱ ጥናቶችን በመጥቀስ ተማሪዎች አፍ ባልፈቱበት ቋንቋ ከሚማሩ በአፍ መፍቻቸው ቢማሩ በላቀ ደረጃ እንዲመራመሩ፣ አዳዲስ ነገሮችን እንዲፈጥሩ፣ ባህላቸውን እንዲያውቁና እንዲፈትሹ፣ እራሳቸውን በቀላሉ ፈልገው እንዲያገኙ፣ ሳይመረምሩ በጭፍን የመቀበል ሂደትን እንዲያስቀሩና ትምህርቱን ከራሳቸው ማህበራዊ አውድ ጋር እንዲያቆራኙ የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ይገልጻሉ፡፡

## 2.1.6 በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ዙሪያ የሚቀርቡ ሙግቶች

ምንም እንኳን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጠቀሜታ ዙሪያ የሚነሱ በርካታ አዎንታዊ ሀሳቦች ቢኖሩም ከዚህ በተቃራኒ እንደ Baker (1988) ያሉ ምሁራን በርካታ ብዝሃ ቋንቋ

ባሉባቸው ሀገሮች በርካታ አፍ መፍቻ ቋንቋዎችን ስራ ላይ ከማዋል መብት ጋር ተያይዞ የትምህርት ወጪና የትግበራ ችግሮች መኖራቸውን ለሙግት ያቀርባሉ፡፡ በሌላም በኩል ተማሪዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውጪ ባሉ ሌሎች ቋንቋዎች መማር የሚመርጡት በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ያለውን ጠቀሜታ ጠንቅቆ ባለመረዳትና ያለምንም መረጃ አስቀድሞ በሚያዝ መጥፎ ሃሳብ (prejudice) የተነሳ ነው የሚሉ እንደ Ogutu (2006)፣ Holmes (1992) አሉታዊ አስተያየቶችም አሉ፡፡ የቋንቋ አለመውደድ የሚነሳው ከፖለቲካዊ አድሎ (political bias)፣ በማህበራዊ አከፋፈል (social stratification)፣ በኢኮኖሚያዊ ልዩነት (economic incongruity) እና በሌሎች ማህበራዊ-ስነልቦናዊ መንስኤዎች ነው (Cohen, 2000)፡፡

የአፍ መፋቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት ማዋል ጠቀሜታ እንዳለው ሁሉ የሀገርን እድገት ይጎትታል፣ ከአለም አቀፋዊ ትስስር ያርቃል፣ ሀገራዊ አንድነትን ያላላል፣ ፖለቲካዊ አለመረጋጋትን ይፈጥራል፣ የሚጠይቀው ወጪ ከፍተኛ ነው፣ ወዘተ የሚሉ አሉታዊ አመለካከቶችም እንደሚሰነዘሩበት Ogutu (2006) ይገልጻሉ፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ በብሄረሰቦች መካከል ለሚፈጠር ግጭት አቢይ ምክንያት የኢኮኖሚ እኩል ተጠቃሚነት አለመኖርና አንዱ ብሄር በሌሎች ብሄሮች ላይ የበላይ ለመሆን መሞከር እንጂ ቋንቋን የመጠቀም ፖሊሲ አይደለም በማለት ያስረዳሉ፡፡ የተለያዩ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎችን በትምህርት መስጫነት መጠቀም በብሄረሰቦች መካከል የርስ በርስ ግጭት እንዲነሳ ምክንያት ይሆናል፣ የሚለው አመለካከት ተገቢ እንዳልሆነ Ogutu (2006)፣ Hirut (2008) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ቋንቋውን የመጠቀም አነሳሽ ምክንያቱ ስነትምህርታዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ በመሆኑ እንቅስቃሴው በቂ መምህራን ባልተዘጋጁበትና የትምህርት ቁሳቁሶች ባልተሟሉበት ይጀመራል፡፡ በመሆኑም እንቅስቃሴው ፖለቲካዊ ግቡን ከመታ በኋላ ብዙ ጊዜ ችላ ስለሚባል የትምህርቱን ጥራት ችግር ውስጥ ይጥለዋል በማለት ይገልጻሉ፡፡

## 2.1.7 የአፍ መፍቻ ቋንቋን በመጠቀም ዙሪያ ያሉ ተግዳሮቶች

እንደ ሌሎች ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሳይንሳዊ ጉዳዮች የትምህርት ጉዳይም ካደጉ ሀገራት ይልቅ ባላደጉ ሀገራት በተለይም በአፍሪካ ተግዳሮቶች እንደሚበዙበት ይታመናል፡ እንደ Birgit (2010) ገለጻ ባላደጉ ሀገራት የአፍ መፍቻ ቋንቋዎችን ለትምህርት መስጫነት ላለመጠቀም እንደ ችግር የሚነሱ ተግዳሮቶች ስነ ትምህርታዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ስነልሳናዊ፣ ስነማህበረ-ኢኮኖሚያዊ… ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ተግዳሮቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለትምህርት መስጫነት በመጠቀም ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.1.7.1 ስነ-ትምህርታዊ ተግዳሮቶች

Alexander (2003) እንደገለጹት፤ የትምህርት መስጫ ቋንቋ ጉዳይ ለአንድ የቋንቋ ትምህርት አይነት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም መርሃ-ትምህርቶች ተግባራዊነትና ስኬታማነት ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ የሚቀርበው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ እውቀት የሚተላለፍበት መንገድ ከቋንቋ ግንዘቤ ስለሚነሳ ወይም ደግሞ ከቋንቋ ጋር ጽኑ ትስስር ስላለው ነው፡፡ ቋንቋ አስተሳሰብን ያሳድጋል፡፡ በአግባቡ የተደራጀ የቋንቋ ትምህርት ወሳኝ የሚሆነውም ቋንቋ ከራሱ ከቋንቋ ትምህርቱ ባሻገር ለሌሎች የትምህርት ይዘቶች የተሰጠውን ድርሻ ስለሚያከናውን ማለትም ለመረዳትም ሆነ ለመግለጽ ስለሚያስችል ነው፡፡ ቋንቋ ተማሪዎች የተማሩትን ነገር ለማንጸባረቅ ያለው ሁነኛ መንገድ ነው፡፡ ስለ ተማሪዎቹ የትምህርት እርምጃ ግብረ-መልስ ማግኛው መንገድም ቋንቋ ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች በትምህርት መስጫነት ጥቅም ላይ ሲውሉ ከሚታዩት ስነትምህርታዊ ተግዳሮቶች መካከል ከቋንቋ መደበኛነት፣ ከመምህራን ስልጠና ከማስተማሪያ፣ መሳሪያዎች ዝግጅት፣ ከጽህፈት ስርዓትና የትምህርት ይዘቶችን በትክክል ወደ ቋንቋዎች የሚተረጉሙ ባለሞያዎች አለመኖር ተጠቃሽ ናቸው (Hirut, 2008)፡፡ በተለይም ባላደጉ ሀገሮች ከሚነሱት ስነትምህርታዊ ተግዳሮቶች መካከል የተደራጁ የማስተማሪያና አጋዥ የትምህርት መሳሪያዎች አለመኖር፣ ቢኖሩም እንደ በለጸጉ ቋንቋዎች በጥራትና በብዛት አለመዘጋጀታቸው ዋነኛው ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ቀድመው በሰለጠኑ የአውሮፓ ቋንቋዎች የተዘጋጁ የማስተማሪያና የመማሪያ የትምህርት ቁሳቁሶችን ለመጠቀም ሲባል ከራሳቸው ይልቅ የአውሮፓ ቋንቋዎችን በትምህርት መስጫነት ለመጠቀም ይገደዳሉ፡፡

ሌላው ተማሪዎች በቂ የሆነ የመማሪያና አጋዥ መጽሀፍት በሌሉበት መማራቸው፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ዙሪያ የቀደመ የንባብና የጽህፈት ተሞክሮ ከመማሪያ ክፍል ውጭ አለመኖር፣ መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለማስተማር በቂ ስልጠና ሳይወስዱ ማስተማራቸው ትምህርቱ በጥራት እንዳይሰጥ እንቅፋት ሊሆኑ እንደሚችሉ Hirut (2008) ያስረዳሉ፡፡ ይህም በማደግ ላይ ባሉ ብዙ ሀገራት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ሲሰጥ ልጆች በትምህርት ቤት ውስጥ የሚያገኙት ብቸኛው የትምህርት መሳሪያ የተማሪው

የመማሪያ መጽሀፍት ነው ይላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በአፍሪካዊቱ ፓፑዋ ኒው ጊኒ ከ800 በላይ ሀገረኛ ቋንቋዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 450 ቋንቋዎች በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በትምህርትነት ውለዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ቋንቋዎች ግን ተገቢው የትምህርት ቁሳቁስ እንዳልተዘጋጀላቸው ይገልጻሉ፡፡

ምንም እንኳ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ጽህፈት ተቀርጾ፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ቢዘጋጁም በቋንቋው የሰለጠኑ መምህራንና ባለሞያዎች እስከሌሉ ድረስ የተመረጠውን ቋንቋ ስራ ላይ ለማዋል ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተግባራዊ የሚያደርጉ የአፍሪካ ሀገራት በአብዛኛው ለመምህራኑ በቂ ስልጠና እንዲያገኙ አያደርጉም፡፡ ቋንቋውን የሚችል ሁሉ ማስተማር ይችላል በሚል ያልሰለጠኑ መምህራንን ይመድባሉ በማለት የኬንያን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ተሞክሮ ለአብነት ያነሳሉ፡፡ በተጨማሪም Daniel and Abebayehu (2006) በኢትዮጵያ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ሲገልጹ በ1994 የትምህርት ቋንቋ ፖሊሲው እንደ ጸደቀ በቀጥታ የተሰራው መማሪያ መጽሀፍቱን ከአማርኛ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመተርጎም ስራ ነው፡፡ በመቀጠልም ቋንቋውን ለሚችሉ ተወላጆች የአጭር ጊዜ ስልጠና በመስጠት ለመተግበር በሚሞከርበት ወቅት ልምድና ብቃት ያላቸውን ተወላጅ ያልሆኑ መምህራንና የትምህርት ባለሞያዎች ከትምህርት ቤት እንዲወገዱና ብቃት በሌላቸው እንዲተኩ ምክንያት ሆኗል በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህ ደግሞ በአብዛኛው ከስነ ትምህርታዊ ግብ ይልቅ ለፖለቲካዊ ግብ ቅድሚያ ከመስጠት የተነሳ ነው፡፡

## 2.1.7.2. ስነ-ልቦናዊ ተግዳሮቶች

በርካታ የማህበረ-ስነልቦናዊ አጥኚዎች እንደሚያቀርቡት የመከራከሪያ ነጥብ አመለካከት ስነልቦናዊ ጉዳይ ሲሆን በግልጽ በሚታዩ ባህርያት ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ ነው፡፡ በዝርዝር ሲጤን በቋንቋ ላይ የተያዘ አመለካከት በትምህርት ላይ የራሱ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል (Holmes, 1992)፡፡ እንደ Holmes ተጨማሪ ገለጻ፤ በቋንቋ ላይ ያለ አመለካከት መምህራን ከተማሪዎች ጋር እንዴት ባለ ሁኔታ መግባባት እንደሚኖርባቸው ተጽእኖ ሊያደርግ እንደሚችል ጥናቶች የደረሱባቸው ግኝቶች አሉ፡፡ Young (2009) እንዳቀረቡት ገለጻ፤ በብዝሃ ቋንቋ ማህበረሰብ ይዞታ በተማሪዎች የቋንቋ ምርጫ ላይ ተጽእኖ የሚያሳርፉ ሦስት ወሳኝ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነሱም መንግስት፣ ክልላዊ የማህበረሰብ ስብጥር እና ብሄረሰባዊ ተመሳስሎ እንዲሁም የማህበራዊ መገናኛዎች የቋንቋ ምርጫዎች ናቸው፡፡

ምንም እንኳን የቋንቋ ፖሊሲዎች በቋንቋ ምርጫ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ማቃለል እንደሚጠበቅባቸው ቢታመንም፤ አብዛኛውን ጊዜ የቋንቋ ፖሊሲዎች በቋንቋ ምርጫ ላይ ያሉ ፍላጎቶችና ጠቀሜታዎች ዙሪያ ሁነኛ አጽንኦት አድርገው አይሰሩም (Alexander, 2003)፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ Alexander እንዳቀረቡት ተጨማሪ ገለጻ፤ የቋንቋ ፖሊሲዎች በእውነቱ የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ጥቅም ለማስጠበቅ የተነደፉ የመንግስት ስትራቴጂዎች ሲሆኑ ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች በቋንቋ ፖሊሲ ንድፍ ያን ያህል ጉልህ የሚባል ትኩረት ሳያገኙ ይቀራሉ፡፡ በመሆኑም በብዝሃ ቋንቋ ማህበረሰብ አውድ ግልጽና አጠቃላይ የሆነ የቋንቋ ፖሊሲ መንደፍ በቋንቋ ምርጫ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ለማቃለል ብሎም የመማሪያ ቋንቋን ለመወሰን አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አጠቃቀምና እድገት የተለያዩ እንቅፋቶች ያጋጥሙታል፡፡ ከነዚህ መካከል አንዱ ራስን በመቆጠብ (self-denial) ሊንጸባረቅ የሚችል አመለካከት ተጠቃሽ ነው (Seyoum, 2009) ፡፡ በSeyoum መሰረት አንዳንድ ሰዎች የራሳቸውን ቋንቋ ስለመጠቀም ያላቸው አመለካከት በሃፍረት ጥላ ስር የወደቀ ነው፡፡ ይህን የአመለካከት ችግር ለማቃለል የሚረዱ የአመለካከት ለውጥ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡ በአንዳንድ ሀገራት ምንም እንኳ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ለትምህርት መስጫ እንዲውሉ ቢፈቀድም ማህበረሰቡ የወጣውን የቋንቋ ፖሊሲ አልቀበልም በማለት ሁለተኛን ወይም የውጭ ቋንቋን የሚመርጥበት ሁኔታ አለ በማለት Ogutu (2006) ያስረዳሉ፡፡ የመጀመሪያው ወላጆች ልጆቻቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ የስልጣኔ ምልክት የሆኑ ለምሳሌ፡- የአውሮፓ ቋንቋዎችን እንዲያውቁ መፈለጋቸው ነው፡፡ ይህም ከሀገርኛ ቋንቋዎች ይልቅ እንደ እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ያሉ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው መናገራቸው ከትምህርት በኋላ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፤ ከሚል እምነት የመነጨ ነው፡፡

ለምሳሌ 98 ከመቶ የሚሆኑ የደቡብ አፍሪካ ጥቁር ዜጎች ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ ልጆቻቸውን በራሳቸው ቋንቋ ከማስተማር ይልቅ በእንግሊዝኛ ማስተማር እንደሚፈልጉ በጥናት ተረጋግጧል (Mutasa, 2006)፡፡ በተለይ በአንድ ሀገር ወይም አካባቢ ውስጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋና በውጭ ቋንቋ ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በውጭ ቋንቋ እንደሚማሩት ተማሪዎች እኩል ላናውቅ ብሎም ወደፊትም በስራ እኩል መወዳደር ላንችል እንችላለን የሚለው የበታችነት ስሜት

በትምህርታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥርበት ሁኔታ እንዳለ በቦትስዋናና በማላዊ የተካሄዱ ጥናቶችን በመጥቀስ በኢኮኖሚ አቅማቸው የተሻሉ ወላጆች ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ በግል ትምህርት ቤቶችና በኮሌጆች ውስጥ ልጆቻቸውን በአውሮፓ ቋንቋዎች እንዲማሩ ማድረጋቸው ሌላው አመለካከታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ ያለ ጉዳይ እንደሆነ ነዉ፡፡

ይህም የውጭ ቋንቋ ማለት የሀብታም ልጆች መማሪያ ቋንቋ እንደሆነና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ደግሞ የድሃ ልጆች መማሪያ ቋንቋ ነው የሚል አመለካከት በወላጆችና በተማሪዎች እንዲፈጠር ምክንያት እየሆነ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ሌላው የማስተማሪያ ቋንቋ ምርጫን ከባህል ጋር አገናኝቶ ለመጠቀም መፈለግ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በተግዳሮትነት ይነሳል በማለት Beeckman (2005) አረብኛ በአፍሪካዊቷ ሱዳን ያለውን ቦታ በማሳያነት በማንሳት ይገልጻሉ፡ በዚህም የተነሳ ያልተማረው የህብረተሰብ ክፍል እነሱን በማየት ከአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ይልቅ በአውሮፓ ቋንቋዎች ማስተማር የተሻለ ነው የሚል አመለካከት እንዲያድርባቸው እያደረገ ይገኛል፡፡ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግዳሮቶች መካከል ወላጆች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በቤት ውስጥ በአብዛኛው ያለመጠቀም ችግር በልጆች አመለካከት ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ እንደሚፈጥር Jacob (2015) ይገልጻሉ፡፡ ለአብነትም በታይዋን ውስጥ የሚኖሩ አብዛኞቹ ወላጆች የራሳቸውን የአፍ መፍቻ ቋንቋ በቤት ውስጥ ከመጠቀም ይልቅ ቻይንኛን መጠቀማቸው በልጆች የአፍ መፍቻ ቋንቋ አመለካከት ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ እንደሆነ በጥናት መረጋገጡን ገልጸዋል፡፡

ትምህርትን ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጭ ማሰብ አይቻልም ከሚል የአዕምሮ ባርነትና ፍርሃት የተነሳ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በመተው በዋናነት እንግሊዝኛ ቋንቋን መምረጥ በብዙ የቅኝ ግዛት ታሪክ ባላቸው የአፍሪካ ሀገራት እንደ ችግር ይነሳል፡፡ ይኸውም ከቅኝ ግዛት በተጨማሪ እንደ ኋላ ቀርነትና ድህነት ያሉ ችግሮች የሚፈጥሩት የበታችነት ስሜት የራስን ቋንቋ ከመጠቀም ይልቅ የሰለጠኑና ያደጉ ሀገራትን ቋንቋዎች የመጠቀም ፍላጎት እንደሚፈጥር Ramachandran and Rauh (2016) በቅኝ ግዛት ተጽዕኖ የተነሳ ከስሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት እስካሁንም ድረስ ሀገረኛ ቋንቋዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በትምህርት መስጫነት እያገለገሉ አይደለም በማለት ይገልጻሉ፡፡

ህጻናት አፍ በፈቱበት ቋንቋ መማራቸው ሌላ ተጨማሪ ቋንቋ እንዳያውቁ እንቅፋት ይሆናል የሚል አመለካከት መኖር ሌላው ተጠቃሽ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ Elisabeh (1999) በኢትዮጵያ የመስክ ጥናት ባካሄዱበት ወቅት ከአንድ የገጠር ውስጥ አባወራ የገጠማቸውን ገጠመኝ ሲገልጹ "ልጄን አፍ በፈታበት ቋንቋ እንዲማር ለምን ትምህርት ቤት እልከዋለሁ? እኔ አባቱ ከቤት አላስተምረውም ወይ በብሄራዊው ቋንቋ አማርኛ እንዲማር እንጅ ትምህርት ቤት የምልከው፡፡" በማለት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን እንደማይፈልጉ የገለጹላቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያን ጨምሮ አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት የመጀመሪያ ደረጃ (በአብዛኛው ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል) ብቻ በአፍ መፍቻ ቋንቋ አስተምረው ከዚያ ባለፈ ባሉ የትምህርት ደረጃዎች ትምህርት የሚሰጡት በውጭ ቋንቋ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ዘላቂነት በሌለው ቋንቋ መማር ማስተማር ምን ያደርጋል? የሚል አመለካከት በዋናነት በተማሪዎችና በወላጆች እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡

## 2.1.7.3. ፖለቲካዊ ተግዳሮቶች

ባላደጉ ሀገራት በተለይም በአፍሪካ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች የትምህርት መስጫ እንዳይሆኑ እንቅፋት ከሚሆኑ ጉዳዮች አንዱ ፖለቲካ ነው (Birgit, 2010)፡፡ ከእነዚህ ፖለቲካዊ ጉዳዮች መካከል ጎልተው የሚጠቀሱት ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡ የአንድ ሀገር የፖለቲካ አቋም አወዛጋቢ ይሆንና በሀገሪቱ የትምህርትና የቋንቋ ፖሊሲ ላይ በአብዛኛው ችግር ይፈጥራል፡፡ ብዙ ቋንቋዎች በሚነገሩበት ሀገር ብሄረሰቦችን ለማሰባሰብና አንድ ለማድረግ በሚል ሰበብ በመላ ሀገሪቱ በቋንቋና በባህል ላይ የሚወሰድ የፖሊሲ እርምጃ አለ፡፡ ለምሳሌ በሀገሪቱ ከሚነገሩ ቋንቋዎች መካከል አንዱን ወይም የተወሰኑትን ያለተጨባጭ ጥናት መርጦ የትምህርት ወይም የስራ ቋንቋ እንዲሆን በጫና ይወሰናል፡፡ በዚህ ወቅት በብሄረሰቦች መካከል የእኛም ቋንቋ መመረጥ አለበት በሚል በሚነሳ የፍክክር ግጭት ሀገርኛ ቋንቋዎችን ለትምህርትም ሆነ ለሌሎች መንግስታዊ ግልጋሎቶች ለመጠቀም እንቅፋት ይሆናል፡፡ ይህን ተከትሎም በገላጋይነት ከሁሉም ብሄረሰቦች ውጭ የሆነ ሁለተኛ ወይም የውጭ ቋንቋን መጠቀም ይሻላል የሚል ፖለቲካዊ ውሳኔ ይወሰናል፡፡

ልሳነ ብዙ በሆነ ሀገር ውስጥ ከሀገረኛ ቋንቋዎች ይልቅ የቅኝ ገዥዎችን ቋንቋ ለትምህርት መስጫነት የመጠቀም ውሳኔ ከሚደረሰባቸው ፖለቲካዊ ምክንያቶች መካከል አንዱ ብሄረሰብ ሌላውን ወይም ሌሎችን ጨቁኗል የሚል አተያይ በሚኖርበት ወቅት ነው

በማለት Ramachandran and Rauh (2016) ይገልጻሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ገለልተኛ የሆነ የውጭ ቋንቋን በመጠቀም እኩል እንጠቀም ወይም እኩል እንጻ ወደሚል ውሳኔ ይደረሳል በማለት በዛምቢያ የተካሄደን ጥናት ይጠቅሳሉ፡፡ በ2015 በዛምቢያ በተካሄደ ጥናት 71 በመቶዎቹ ዛምቢያውያን ከሀገረኛ ቋንቋዎች ይልቅ እንግሊዝኛን እንደሚመርጡ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በደቡብ ሱዳንም የሀገሪቱ የስራም ሆነ የማስተማሪያ ቋንቋ እንግሊዝኛ ነው፡፡ ሆኖም ከሀገሪቱ ህዝብ ውስጥ እንግሊዝኛን መናገር የሚችለው 15 በመቶው ብቻ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ይህን ተከትሎም ከራሳችን ቋንቋዎች ይልቅ ከሰለጠኑና ገለልተኛ ከሆኑ የአውሮፓ ቋንቋዎች መካከል ታሪካዊና ፖለቲካዊ ቅርበት ያለውን መርጦ ለትምህርትም ሆነ ለሌላ መንግስታዊ ግልጋሎት መጠቀም ይሻላል የሚል ፖለቲካዊ ውሳኔ ይወሰናል፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለትምህርት መስጫነት የመጠቀም ተነሳሽነት አንዳንድ ጊዜ ተጨቁነን ቆይተናል በሚሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ከጭቆናቸው የሚላቀቁበት ፖለቲካዊ መሳሪያ አድርገው ያስቡታል፡፡ ለአብነትም የሚያነሱት ጥቁር ደቡብ አፍሪካዊያን የራሳቸውን ቋንቋ ለማስተማሪያነት እንዲውል የሚፈልጉት ለስነ ትምህርታዊ ፋይዳው ሳይሆን ከቅኝ ገዥዎቻቸው ነጻ ለመውጣታቸው በማሳያነት ለመጠቀም መሆኑን ነው፡፡ በአፍሪካ ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለማስተማሪያነት የመጠቀም ወይም ያለመጠቀም ውሳኔዎች መሰረታዊ ምክንያታቸው በአብዛኛው ስነትምህርታዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ ነው በማለት Ferguson (2006) ይገልጻሉ:: በአንድ በኩል በሀገር ውስጥ በሚገኙ ብሄረሰቦች መካከል የእኔም ቋንቋ ይመረጥ የሚል የፍክክር ግጭትን ለማስቀረት ገለልተኛ የሆኑ የአውሮፓ ቋንቋዎችን ይጠቀማሉ፡፡ በሌላ በኩል መንግስታት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ለፖለቲካዊ ግብ በሚፈልጉበት ወቅት ማህበረሰቡ ሳይፈልግ እንኳ በጫና ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ሌላው የሚነሳው ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ በተግባር ሲፈተሽ ለተማሪዎች ጥሩ ትምህርት ለማድረስና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በዘመናዊ ትምህርት አግዞ ለማሳደግ ያለመ ሳይሆን በራስ ቋንቋ የመጠቀም መብትን አስከብሪያለሁ፤ ለሚል ፖለቲካዊ ፍጆታ ሊሆን ይችላል፡፡ ፖለቲካዊ አላማውም በተግባር የሚገለጽ የፖለቲካ ቁርጠኝነት የማያገኝበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህንን ሀሳብ Ball (2011) ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አተገባበር ስኬትና ውድቀት ዋናው ነገር ሀገራዊ ወይም አካባቢያዊ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ነው ይላሉ፡፡ ምክንያቱም የፖለቲካ ቁርጠኝነት በጀት ከመመደብ ጠንካራና ግልጽ የሆነ ፖሊሲ ከማዘጋጀት ህዝብን

ከመቀስቀስና ከማስተባበር ከትምህርት አስተዳድር ወዘተ አኳያ ጥብቅ የሆነ ቁርኝነት አለው፡፡

## 2.1.7.4. ስነ-ልሳናዊ ተግዳሮቶች

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለትምህርት መስጫነት እንዳይውል እንቅፋት ከሚሆኑ ጉዳዮች አንዱ ስነልሳናዊ ተግዳሮት ነው በማለት Birgit (2010) ያስረዳሉ፡፡ ከስነልሳናዊ ተግዳሮቶች መካከል በቃል ሲነገር የቆየን ቋንቋ በጽሁፍ የማዋል ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ቋንቋው የጽሁፍ ቋንቋ ከመሆኑ በፊት መደበኛ ሰዋስዋዊ ስርዓቱን መለየት፣ ለጽሁፍ የሚያገለግሉ ቃላትን መምረጥ፣ በቋንቋው ውስጥ ለሚገኙ ድምጾች ተስማሚ ሆሄያትን መፍጠር፣ የቋንቋው የመደበኛነት ችግር፣ ሳይንሳዊና ሙያዊ ስያሜዎችን የሚተኩ ቃላት አለመኖርን የሚመለከት ነው፡፡ ሆኖም ግን በቋንቋው ውስጥ የዘዬዎች መብዛትና መራራቅ ሲያጋጥምም የጽህፈት ስርዓቱን በቀላሉ ለማዘጋጀት ያስቸግራል፡፡ በዚህም የተነሳ አብዛኞቹ የአፍሪካ ቋንቋዎች በጽህፈት ቀረጻ፣ በመዝገበ ቃላት ዝግጅት፣ በቋንቋ መደበኛነት እና በትምህርት ቁሳቁሶች ዝግጅት ያልተሟሉና ያልበለጸጉ በመሆናቸው ለማስተማሪያነት ለመጠቀም ጥረት በሚደረግበት ወቅት ችግር መፈጠሩን ይገልጻሉ፡፡

ከዚሁ ጋር በተገናኘ Hoben (1994) ሲገልጹ በደርግ ዘመነ መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎችን ለመሰረተ ትምህርት ማስተማሪያነት ለመጠቀም ሲፈለግ ካጋጠሙ አብይ ተግዳሮቶች መካከል የቋንቋ መደበኝነት ጉዳይ አንዱ እንደ ነበር በሌላ በኩል የቋንቋ መደበኛነት ጉዳይ አንዳንዴ በፖለቲካዊ ምክንያት ሊደናቀፍ እንደሚችል Daniel and Abebayehu (2006) ይገልጻሉ፡፡ ለዚህም በአብነት የሚያነሱት ወላይትኛ ፣ ጋሞኛ፣ ጎፍኛና ዳውሮኛ ቋንቋዎችን እንደ አንድ ቋንቋ አድርጎ በመጨፍለቅ ለትምህርት መስጫነት ለመጠቀም የተካሄደው ሂደት በፖለቲካ ምክንያት የ40 ሚሊዎን ብር ኪሳራና የሰባት ሰዎች ሞት አስከትሎ መቋረጡን ገልጸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የቋንቋ መደበኛነት ትግባራ ሲከናወን ስነልሳናዊ ምክንያቱ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ምክንያቶችም ቀድመው መጠናት እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው፡፡

## 2.1.7.5. ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች

ብዝሃ ቋንቋ በሚኖርበት ህብረተሰብ ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫ ቋንቋነት ለመወሰን የሚደረገው ምርጫ ካሉበት ችግሮች ዋንኛው ለትምህርት መርጃነት

የሚውሉ ጥሬ ሀብቶች (resources) በበቂ ሁኔታ መኖር ነው፡፡ እንደሚታወቀው ነባሩን /አሮጌ/ የትምህርት ስርአት በመቀየር ዙሪያ ታሳቢ የሚደረጉ ልዩ ልዩ ግብአቶች በመዋእለ ንዋይ ድልድል የሚሳለጡ ናቸው፡፡ የስርአተ ትምህርት ለውጡ ታሳቢ የሚያደርጋቸው የስርአተ ትምህርት ንድፍ፣ የመርሃ-ትምህርቶች ዝግጅት በታላሚው ቋንቋ ማስተማሪያና መማሪያ መጻህፍት ትርጉምና ዝግጅት፣ የተለያዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላትን በታላሚው ቋንቋ አቻ ትርጉም አሟልቶ ማቅረብ፤ ልሳነ-ዋህድና ልሳነ-ክልኤ መዝገበ ቃላትን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አዘጋጅቶ በአጋዥነት ስራ ላይ ማዋል፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መምህራን ስልጠና ሰፊ የሀብት ግብአትን የሚጠይቁ ጉዳዮች መሆናቸውን Baker (1988)፣ Cohen (2000)፣ Seyoum (2009) ይጠቁማሉ፡፡

በሌላም በኩል እንደ Khejeri (2014) ገለጻ፤ ትክክለኛ የፊደላት ድርድር ተቀባይነት ባለው መንገድ መቅረጽና መሰነድ፣ ሰዋሰው ማደራጀት፣ መማሪያ መጻህፍትና ተጨማሪ ተነባቢ ጽሁፎችን በትምህርት አጋዥነት ማቅረብ በኢኮኖሚ ላይ የተመሰረቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የማይዘለሉ ግብአቶች ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በተለያዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች ጫና ተገቢ አተገባበራቸው ሊደናቀፍና እድገታቸው ሊቀጭጭ ይችላል፡፡ Khejeri (2014) አክለው እንዳስገነዘቡት፤ የፖለቲካ የቋንቋ ፖሊሲ ስለትምህርት መስጫ ቋንቋ አጠቃላይ መርህና የቋንቋ ትምህርት ግቦችን በመንደፍ ያቀርባል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ይህ ፖሊሲ ስለ በጀት፣ ሰብአዊና የማሳለጫ ግብአቶች ትኩረት አለመስጠቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን የሚያዳክም ምክንያት ነው፡፡ የፖለቲካ የቋንቋ ፖሊሲ ቅድሚያ የሚያተኩረው በፖለቲካዊ ርእዮተ-አለማዊ ጉዳይ እንጂ ለስነማስተማር ዘዴ ጠቀሜታ (pedagogical merits) አይደለም፡፡

ቋንቋን መንከባከብና ማሳደግ ጊዜን የሚጠይቅና ሀብትን የሚጠቀም እንደመሆኑ መጠን በተለይ እንደ አፍሪካ ባሉ ለማደግ በሚፍጨረጨሩ ሀገራት ውሱን የመዋእለ ንዋይ አቅም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ጥራት ላይ ገደብ የሚፈጥር ጉዳይ ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህን ችግር በተሻለ የሚረዱ የተማሩ እና/ወይም የተሻለ የገቢ አቅም ያላቸው ወላጆች ልጆቻቸውን የቋንቋ ፖሊሲ ማእቀፍ የግዴታ በሚተገበርባቸው በከተሞች አካባቢ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ለማስተማር አይሹም፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ፖሊሲ ልል ወደሆነባቸው የግል ትምህርት ቤቶች ያዘነብላሉ ሲሉ Cohen (2000)፣ Seyoum (2009) እና Baker (1988) አጥብቀው ይሞግታሉ፡፡

ይህ አይነቱ ተሞክሮ የኢትዮጵያ የቋንቋ አጠቃቀም ፖሊሲ ፍላጎትና ግባዊነት ተጻራሪ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማቅረቢያነት ዙሪያ የሚታዩ ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች ምን እንደሚመስሉ አስሶ ለማቅረብ ሞክሯል፡፡

ከኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚጠቀሰው ተግዳሮት አለማቀፋዊ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ትስስር እየጠነከረ መምጣት ወይም ሉላዊነት ነው፡፡ ምክንያቱም በፍጥነት የሚከናወነው የአለም አቀፍ መረጃና እውቀት ስርጭት የሚካሄደው በአደጉ ሀገራት ቋንቋዎች መሆኑ ያላደጉ ሀገራት ዜጎች የራሳቸውን ቋንቋ ችላ እንዲሉ አድርጓቸዋል፡፡ ለምሳሌ እንደ እንግሊዝኛ ያሉ ቋንቋዎች የአለም አቀፍ ተቋማትና ስብሰባዎች መምሪያ፣ የአዳዲስ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ህትመቶች ማቅረቢያ፣ የአለም አቀፍ ባንኮችና የንግድ ተቋማት የስራ ቋንቋ፣ የአለም አቀፍ ሸቀጦች ማስተዋወቂያ፣ አለም አቀፍ የዜና አውታሮች ፊልሞችና፣ ሙዚቃዎች ማቅረቢያ፣ የአለም አቀፍ የደህንነትና የህግ ተቋማት የስራ ቋንቋ መሆናቸው ያላደጉ ሀገራት ቋንቋዎቹን ለትምህርት መስጫነት በመጠቀም ሂደት ላይ ተጽእኖ እየፈጠረ ይገኛል፡፡

ይህም ከላይ ከተዘረዘሩት ተቋማት ጋር በቀላሉ ለመገናኘትና ከትምህርት በኋላ በእነዚህ ተቋማት ተቀጥሮ ስራ ለመስራት ዋስትና ስለሚሰጥ የድሃና ኋላ ቀር ሀገራት ዜጎች ከራሳቸው ቋንቋ ይልቅ እንደ እንግሊዝኛ ባሉ ቋንቋዎች መማርና ማስተማርን ይመርጣሉ ምክንያቱም የኢኮኖሚ ኢምፔሪያሊዝምና የስነልሳን ኢምፔሪያሊዝም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ በ1992 በዙምባብዌ በተካሄደ ጥናት፣ ተማሪዎች እንግሊዝኛ ቋንቋ በትምህርት መስጫነት መቀጠል አለበት በሚል ከመረጡ በኋላ በምክንያትነት ያቀረቡት ለአለም አቀፋዊ ግንኙነት እንግሊዝኛ ከሀገረኛ ቋንቋዎች የተሻለ ነው የሚል ነው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለማስተማሪያነት ለማዋል ሲተሳብ የገንዘብ ምንጭ ከየት ማግኘት እንደሚቻልና አጠቃቀሙን ጭምር በቅድሚያ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ አለበለዚያ ግን የመጠቀም እቅዱና አተገባበሩ ችግር ውስጥ ይወድቃል፡፡ ይህዉም የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለማስተማሪያነት በመጠቀም ሂደት እንደ ተግዳሮት ከሚነሱ ጉዳዮች አንዱ የበጀት እጥረት መኖርና የተመደበውን በጀት በአግባቡ አለመጠቀም ነው፡፡

## 2.1.7.6 የቁሳቁሳዊ ግብዓቶችና የሰው ኃይል ተግዳሮቶች

ብቁ መምህራንን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ማሰልጠንና ለተማሪዎቹ ባህላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ስነትምህርታዊ ፍላጎቶች የሚመጥኑ የማስተማሪያ ግብአቶችን ማቀድ፣ መምረጥ፣ ማዘጋጀትና በበቂ ሁኔታ ማዳረስ ሰፊ መዋእለ ንዋይ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የመዋእለ ንዋይ ጥያቄ ተሟልቶ በተገኘበት ሌላው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ከመተግበር በፊት የሚነሳ ቁልፍ ጥያቄ የቋንቋ ምሁራን፣ የትምህርት ባለሙያዎች ፣ የፖለቲካ መሪዎችና የማህበረሰብ አዋቂዎችን ቁልፍ ባለድርሻነት የሚጠይቀው ጉዳይ ታላሚው የአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማሪያ ቋንቋነት እንዲቀርብ የሚያስፈልግ የመማሪያ ቁሳቁስ ዝግጅት ጉዳይ ነው፡፡ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ ትግበራ የሚያስፈልጉ መርሃ-ትምህርቶችን ማቀድ፣ ከሚገኙበት ምንጭ በተገቢ መስፈርቶች ተደግፎ መምረጥ፣ ወደ ታላሚው ቋንቋ በቋንቋ ምሁራን አማካኝነት በመተርጎም ማዘጋጀትና በበቂ መጠን ማሰራጨት ትልቅ ትኩረትና ዝግጁነት እንዲሁም የኢኮኖሚ ድጋፍ ይጠይቃል (Benson, 2004)፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ የአፍ መፍቻ ቋንቋውን በተሟላ መልኩ የሚወክሉ ፊደላት ዝግጅት እንዲሁም ከልዩ ልዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላት ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ አቻ ፍቺ በመስጠት የማስተማሪያ ግብአቶችን ማዘጋጀት መሆኑን (Wolff, 2006፣ Benson, 2004) ይጠቁማሉ፡፡

የሰው ኃይልና የቁሳቁሳዊ ግብአቶች ተግዳሮት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራን በማሳለት ረገድ ያላቸው ድርሻ እጅግ ትኩረት የሚጠይቅ ነው፡፡ በታላሚው አፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት ማካሄድ ስለቻሉ ብቻ መምህራን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ያለምንም ስልጠና እንዲያካሂዱ ማድረግ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡ Cohen (2000)ና Seyoum (2009) እንደገለጹት፣ በዋንኛነት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ክሂሎች የሰለጠነ መምህር ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በተገቢ ሁኔታ መመደብ አለመቻል በተማሪዎቹ ፍላጎት፣ ውጤታማነት፣ አመለካከት ወዘተ ዙሪያ ታላላቅ እንቅፋቶችን ይደቅናል፡፡ የመምህራን ስልጠና የቋንቋ ክሂሎችን ተፈላጊውን ግብ ለማቀዳጀት ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በቋንቋም ማስተማር ዙሪያ ተፈላጊውን ሙያዊ ብቃት ያልያዙ መምህራንን በዘፈቀደ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አውድ ማሰማራት ለትምህርቱ ጥራት ፣ ለተማሪዎቹ ተፎካካሪነትና

መነሳሳት፣ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት እቅድ አለመሳካት አሉታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

Benson (2004) እንደገለጹት፤ የመምህራን ሙያዊ ብቃትና በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ዝግጅት በትምህርት ቤት ቆይታቸው ለተማሪዎች ሞዴል በመሆን መገለጽ መቻል ይኖርበታል፡፡ በትምህርት ቤት ቆይታ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ በግቢ ውስጥ በታላሚው ቋንቋ ከተማሪዎቻቸው ጋር ተግባቦቶችን ለማካሄድ ፍላጎትና ተነሳሽነት ያላቸው ብሎም የታላሚው ቋንቋ እውቀትና ክህሎት ያላቸው መምህራን ተመርጠው መሰልጠናቸው ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራና ግባዊነት መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎችን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ተነሳሽነት፣ መነቃቃት ቀልጣፋ የክፍል ተሳትፎ ይወስነዋል፡፡

በሌላ በኩል የማስተማሪያ ግብአቶችን በተገቢው ሁኔታ ማዘጋጀትና በበቂ ሁኔታ ማሰራጨት ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ ስኬት ዋንኛውን ድርሻ ይወስዳል (Kroskrity 2010)፡፡ እንደ Kroskrity ገለጻ የመማር ማስተማር ክንዋኔን በሚገባ ለማካሄድ ከተማሪዎቹ ስነትምህርታዊ፣ ባህላዊና ስነልቦናዊ፣ ወዘተ ሁኔታዎች ጋር በሚገባ የተገናዘቡ ጠቃሚ ይዘቶችን መምረጥ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ጥልቅ እውቀት መያዝ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ማለት ውጤታማ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የተመሰረተው በሚዘጋጀው የመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ጥራትና ተደራሽነት ነው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ መርሃ-ትምህርቶች የመምህሩ መምሪያ ፣ መጻህፍት ፣ የተማሪዎቹ መማሪያ መጻህፍት የክፍል ውስጥ ትምህርቶችን በሚገባ ለማሳለጥ ወሳኝ ድርሻ አላቸው፡፡ ከእነዚህ ግብአቶች በተጨማሪ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ ልሳነ-ዋህድና ልሳነ-ክልኤ መዝገበ ቃላት፣ አጋዥ መጻህፍት፣ ከባህሉ ጋር አግባብ ያላቸው የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ፣ ተጨማሪ የንባብ መጻህፍት ለምሳሌ፡- በታላሚው ቋንቋ የተዘጋጁ ልቦለዶች ፣ ጋዜጤችና ሌሎች ተነባቢ መጻህፍት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ሂደትን ለማጠናከርና ውጤታማ ለማድረግ የበኩላቸው ጉልህ ደርሻ አላቸው (Wolff, 2006)፡፡

እንደ Wolff ተጨማሪ ገለጻ፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ ማጣቀሻ መጻህፍት እና/ወይም ተጨማሪ የንባብ መጻህፍት የተማሪዎችን የማወቅ ፍላጎት ለማነሳሳትና በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የተለያዩ ነገሮችን አንብበው ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ለማድረግ ይረዳቸዋል፡፡ ከባህልና ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር የተገናዘቡ ተነባቢ

ነገሮችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በአንድ ማእከል በማሰባሰብ ለተማሪዎች ለማቅረብ የትምህርት ቤት ቤተ-መጻህፍት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ይህም የተማሪዎቹን የትምህርት ውጤታማነት ከፍ ለማድረግ ያግዛል፡፡

የትምህርት መሳሪያዎችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተደራሽ ማድረግ ለተማሪዎች ውጤታማነት ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ ጎን ለጎን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራንም የመማር ማስተማሩን ሂደት ጠቃሚ ለማድረግ በቂ የማስተማሪያ ግብአት ሊሆኗቸው እንደሚችሉም ይታሰባል (Kroskrity (2010)፡፡ በዚህ መሰረት ይህ ጥናት ከመምህራን ስልጠና እና ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማሪያ ግብአቶች ዝግጅትና ተደራሽነት ጎን ለጎን የአፋን ኦሮሞ ትምህርትን ለመተግበር የተበየኑት ፌደላት ዝግጅትና የመማር ማስተማሩን ሂደት ለመተግበር የተዘጋጁት መጻህፍት ትርጎማ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት እርከን ለሚተገበረው የመማር ማስተማር ሂደትና ለቋንቋ እቅዱ ስኬታማነት ተስማሚ ሆነው እንደቀረቡ መቃኘት የዚህ ጥናት አንዱ ትኩረት ነው፡፡

## 2.1.7.7 ከትምህርት መስጫ አካባቢ (School context) ጋር የሚያያዙ ተግዳሮቶች

የትምህርት መስጫ አካባቢ የትምህርት መተግበሪያ ስነምህዳር (ecology) ሲሆን የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚካሄድበት ተቋማዊ ይዞታን የሚመለከት ነው፡፡ ጤናማ የትምህርት አካባቢ ለጤናማና ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት መሰረቱ ነው፡፡ የትምህርት ተቋሙ መማሪያ ክፍሎች ምቹነት፣ ልዩ ልዩ ፋሲሊቲዎች ተሟልተው መገኘት ፣ ግልጽና አበረታች የስነስርአት ደንብ መኖር፣ የመምህራንና ተማሪዎች አዎንታዊ ግንኙነት ፣ የመምህራን ብዛት(በሚፈለገው ደረጃ)፣ የክፍለ ጊዜያት ስርጭት፣ የተጓዳኝ ትምህርት ክበባት እንቅስቃሴ ፣ የቤተመጻህፍት አደረጃጀት፣ የመማሪያ ቁሳቁሶች ተሟልቶ መገኘት፣ የወላጆችና ሌሎች ባለድርሻዎች ተሳትፎ እንዲሁም ሌሎች ደህንነቱ የተጠበቀና ለመማር ማስተማሩ ሂደት አጋዥና አበረታች ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘት የጤናማ የትምህርት መስጫ አካባቢ መገለጫዎች እንደሆኑ Mutasa and Negota (2008) ይገልጻሉ፡፡

በትምህርት አካባቢ የትምህርት ቤቱ ህንጻዎች(ክፍሎች)፣ መምህራንና የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያሳልጡ ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኘት ብቻውን ምቹ አያሰኘውም የሚሉት Khejeri (2014) በበኩላቸው የትምህርት ቤቱ ውስጥና በዙሪያው የሚገኘው ማህበረሰብ

ለትምህርቱ ሥራ ያለው አመለካከት፣ ድጋፍና ለትምህርት ቤቱና ለመማር ማስተማሩ ሂደት መጎልበት የሚያሳየው ተነሳሽነት (commitment) እና ተጨባጭ ጥረትንም ያካትታል ብለዋል፡፡ በሌላ በኩል Khejeri (2014) እንደገለጹት ትምህርት ቤት ወጣቶችን በእውቀት ለማነጽና የባህሪ ለውጥ ለማምጣት ወሳኝ ተቋም ነው፡፡

የተሻለ ጥራት ያለው የመማር ማስተማር ሂደት ምቹ የመማሪያ ተቋም መፍጠርንና የትምህርት ባለድርሻ አካላት የአመቻችነት ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ምቹ የመማር ማስተማር ሂደት መፈጠር ጥራት ያለው ትምህርት ለተማሪዎች ለማድረስ ወሳኝ እንደመሆኑ መጠን ይህ የሚሳካውና የሚለካው ደግሞ በጥሩ የትምህርት ቤት አመራር፣ በወላጆችና ሌሎች አጋሮች ዘላቂ ተሳትፎ ብሎም አበረታች የትምህርት ቤት ባህል (school culture) በመፍጠር ነው፡፡

## 2.1.7.8 ከተማሪዎች ዝግጁነቶች ጋር የሚያያዙ ተግዳሮቶች

የተማሪዎች የማንበብና መጻፍ፣ የማዳመጥና መናገር ክህሎቶች ለመማር የመጀመሪያው የቋንቋ መሰረታዊ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት ውስብስብ የሆኑ ጽንሰ ሀሳቦችን፣ ልምድና ተሞክሮዎችን፣ ክሂሎችን እየተገነዘቡ ያድጋሉ፡፡ በጥሩ ሁኔታ በትምህርት ግብአቶች በተደገፈ የትምህርት አሰጣጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋን መሰረት ያደረገ ትምህርት በተከታታይ ለስምንት አመታት ያህል የተሰጣቸው ተማሪዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር በአጥጋቢ ሁኔታ ተግባቦት ለማካሄድና ቀጣይ አካዳሚያዊ እውቀት ለምቅሰም ብቁ ይሆናሉ ተብሎ በስነትምህርት ምሁራን ይታመናል (Heugh, 2006)፡፡ ይሁንና በተለያዩ ተጽእኖ ፈጣሪ ምክንያቶች ተማሪዎች በታቀደው ጊዜ ይደርሱበታል ተብሎ ከሚጠበቀው የስኬት መስመር ወደኋላ ሊቀሩ እንደሚችሉ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች ግላዊ፣ ስነልቡናዊና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ግላዊ የሚባሉት ከተማሪው ከራሱ ሰብእና የሚነሱ የትምህርት ዝግጁነት፣ የአመለካከትና የተሳትፎ ችግሮች ናቸው፡፡ ተማሪው በራሱ ራእይ አልባነት፣ በአሉታዊ የአቻ ግፊት፣ በትምህርት ጠል ባህሪ፣ በድጋፍ ማጣት፣ በወላጆች አሉታዊ ተጽእኖ እንዲሁም በሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተነሳ በሚካሄደው የመማር ማስተማር ክንዋኔ ንቁ ተሳታፊ ላይሆን ይችላል፡፡ የሚሰጠውን የእለት ተእለት ትእዛዝ አለማክበር፣ ጥለኛ /ሞገደኛ/ ሆኖ መገኘት፣ አዘውትሮ መቅረት፣ ትምህርት ማቋረጥ የመሳሰሉት ሁኔታዎች ከተማሪው ዝግጁነት ማነስ ጋር የተቆራኙ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ስኬታማነት እንቅፋቶች ናቸው (Heugh, 2006)፡፡

ተማሪዎች በየጊዜው የሚያዳብሩት እውቀትና ልምድ በማህበራዊ ተግባቦቶቻቸው፣ በእርስ በእርስ ተፎካካሪነታቸው፣ በቋንቋ ውስጥ ያሉ ባህል፣ ልማድና እሴቶች ዙሪያ በሚያካሂዷቸው ተራክቦዎች እየበለጸጉ እንደሚጓዙ የታመነ ነው፡፡ የቀደመ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ክህሎት፣ እውቀትና ልምዳቸው ሌላውን ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ምቹ ተሞክሮ ይፈጥርላቸዋል፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ብቃት የታነጹ ህጻናት የቀደመ ልምድና እውቀት በሚጠበቀው መልኩ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ ያደርጋቸዋል (Cummins, 2005)፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ መንስኤዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ስኬታማ መሆን ያልቻሉ ህጻናት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አውድም በአብዛኛው ይኸው ችግር አብሯቸው ይዘልቃል፡፡ በመሆኑም በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ ወቅት የህጻናቱን የማንበብና የመጻፍ ክህሎቶች በጥሩ መሰረት ማነጽ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚሰጡ ሌሎች ቀጣይ ትምህርቶችንም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋዎችን በአጥጋቢ ሁኔታ ለመገብየት ቁልፍ መነሻ መሆኑን ትምህርት ቤቶች ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

## 2.1.8 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ንድፈ-ሀሳባዊ መሰረቶች

የቋንቋ ፖሊሲ የዚህ ጥናት ንድፈ ሀሳባዊ መሰረት ነው፡፡ በብዝሃ ቋንቋ ህብረተሰብ የብዝሃ ቋንቋ ፖሊሲ ውጤታማ የሚሆነው ሁነኛ ርእዮተ-አለማዊና ትግበራዊ ስፍራ በመስጠት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በሀገር ደረጃ ያሉ የቋንቋ ፖሊሲ አተገባበር ባለድርሻዎች በቋንቋ ፖሊሲው አማካኝነት የብዝሃ ቋንቋ ትምህርትን በመራመድ የሚያገኙት ሁለንተናዊ ጠቀሜታ በግልጽ የሚደገፍና ተጨባጭ መሆን ይኖርበታል፡፡ ቋንቋ ሁልጊዜም በመማር ማስተማሩ ሂደት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ማንኛውንም የትምህርት አይነት ያለ ቋንቋ ግብአትነት ሊነገር፣ ሊደመጥ፣ ሊጻፍ እና ሊነበብ አይችልም፡፡ መናገርና መጻፍ በቋንቋ የማሰብና የማሰላሰል ተግባር የሚከናወኑባቸው ናቸው፡፡ ተማሪዎች በቋንቋ አማካኝነት የሚማሩ እንደመሆናቸው መጠን የቋንቋ ችሎታቸው ደከም ያለ ከሆነ ትምህርቱን የመቀበል ችሎታቸውም እንዲሁ ሊዳከም ይችላል (Magwa and Mutasa, 2007)፡፡

በቋንቋ ትምህርት ላይ ትልቅ አጽንኦት በመስጠትና በቀጣይነት እያደገ በሚሄድ ጥልቀት ባለው የትምህርት ይዘት ማስደገፍ አስፈላጊ የሚሆነውም የቋንቋ ትምህርት ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ይዘት የተሰጠውን ድርሻ በኃላፊነት የማከናወን ተልእኮ በውስጡ ስላለ ነው፡፡ የቋንቋና የትምህርት ይዘት ጥብቅ ወይም ውስብስብ ትስስርም ተማሪዎች ቋንቋን በተገቢ መንገድ ከተረዱና የበለጸገ የቋንቋ ችሎታ ካዳበሩ በቋንቋ ትምህርቱ ብቻ

ሳይሆን በሌሎች የትምህርት አይነቶችም ይበልጥ ውጤታማ እንደሚያደርጋቸው ስለሚታሰብ ነው፡፡በትምህርታቸው ይበልጥ ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች በሕይወታቸውም በተሻለ ሁኔታ ስኬታማ ይሆናሉ፡፡

ስለዚህም ነው የትምህርት ይዘትና ቋንቋ በማይነጣጠሉበት ሁኔታ በጥብቅ የተወሳሰቡ ናቸው የሚባለው (Stubbs, 2008፣ Andrews, 2007)፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋን የመማሪያ ቋንቋ የማድረግ እሳቤ ከብዝሃ ቋንቋ ፖሊሲ የሚመነጭ ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት እሳቤ ተማሪዎችን ከትምህርት መጀመሪያ እድሜያቸው ጀምሮ በማህበረሰባዊ የእለት ተእለት ተግባቦታቸው ተፎካካሪ ለማድረግ የሚረዳ እንደሆነ ይታመናል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች እውቀት፣ ክህሎትና ልምድ የተዋቀረበት፣ ከሚኖሩበት ማህበረሰብ የተወረሰ ልምድና ችሎታን የትምህርቱ አውድ መግባቢያ ለማድረግ የታለመ ነው፡፡ እነዚህ የተማሪዎች ችሎታዎችና ተሞክሮዎች መነሻቸውን ማህበረሰባዊ ትውፊቶች፣ ባህሎች፣ እምነቶች፣ በጎ ልማዶችና ማህበራዊ ስርአቶች ያደረጉ በመሆናቸው ተማሪዎቹ አስቀድመው የሚያውቋቸውን ልምዶችና እውቀቶች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ስርአት ባለው ሁኔታ ተቀናብሮ ከሚቀርበው መደበኛ ትምህርት ጋር በማቀናጀት ተማሪዎቹን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የሚታቀድ ነው (Magwa and Mutasa, 2007)፡፡ በውጤቱም በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩ ልጆች በሚያውቁት የመጀመሪያ ቋንቋ ድጋፍ ስለሚማሩ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡

በ Khejeri (2014) እንደተገለጸው የተማሪዎች አእምሯዊና ስነስሜታዊ (affective) እድገት በተጨባጭ እውን የሚሆነው በዋንኛነት ተማሪው አስቀድሞ በሚያውቀው ቋንቋ እንዲማር ሲደረግ ነው፡፡ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክተው Kroskrity (2010) ባቀረቡት ገለጻ ተማሪዎች እንዲማሩበት፣ መምህራንም እንዲያስተምሩበት በሚፈለገው ቋንቋ አስቀድሞ የሰረጸ ግንዛቤ ያላቸው ከሆነ ለትምህርቱ ጥራት አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ የቋንቋ ክህሎታቸውንና እውቀታቸውን ያሳድጋል፡፡ ከዚህም በላይ ተማሪዎች ከፍ ያለ በራስ የመተማመን ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡ የሚማሩትን ትምህርት ጽንሰሃሳብም በበለጠ ይገነዘባሉ፡፡ በመሆኑም ስርጸት ባለው መንገድ የተደራጀ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ ለሆነ የመማር ማስተማር ሂደት ብሎም ለተሻለ ክህሎትና ግንዛቤ እንደ አዋጭና ምቹ ቅድመ ሁኔታ ሊወሰድ የሚገባው ነው፡፡

በStubbs (2008) ገለጻ መሰረት ለውጤታማ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የመምህራን ዝግጅት ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በስልጠና ብቃት የታገዙ መምህራን ተማሪዎቹን ከቋንቋ ፖሊሲ ግቦች አኳያ ለማብቃትና የትምህርት ተሃድሶን ወደ መማሪያ ክፍል ለማምጣት ተነሳሽ እንደሚያደርጋቸው ይታመናል፡፡

ከዚህም በላይ ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በቀላሉ እንዲረዱት ለማድረግ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ የመማሪያ ቋንቋውን አጣርተው የሚያውቁ ተማሪዎች በአብዛኛው ጽንሰሃሳባዊ ይዘቶችን ለመረዳት አይቸገሩም፡፡ ይሁንና ተማሪዎች አጣርተው በማያውቁት ቋንቋ እንዲማሩ የሚገደዱ ከሆነ የሚማሩትን ትምህርት ይዘት ለማወቅ ብቻ ሳይሆን የሚማሩበትን ቋንቋ ቃላትና አገላለጾች ለመረዳት ትግል የሚገጥሙ መሆኑን ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ተማሪዎቹ በትምህርታቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ አዳጋች ሁኔታ ያጋጥማቸዋል፤ የቋንቋ ፖሊሲ ግባዊነትም አጠያያቂ ይሆናል::

ከፍ ሲል ከቀረበው ሃሳብ ጋር በተያያዘ Kroskrity (2010) በግልጽ እንዳስረዱት የአንድ ሰው ቋንቋ ሰውየው የባህሉን እሴቶች ለመግለጽና አካባቢውን ለመረዳት ቀዳሚው መሳሪያው ነው፡፡ ይህም ማለት የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ የራሳቸውን ልምዶች ፣ እውቀቶች ፣ አመለካከቶችና ክህሎቶች ለመግለጽ በቅርበት ያላቸው መሳሪያ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በትምህርት መጀመሪያ እርከን ለመማር የሚጋለጡበት ቋንቋ በመማር ተሞክሯቸውና ስሜታቸው ላይ የራሱን ተጽእኖ ያሳርፋል፡፡ የጥናት ውጤቶች እንዳረጋገጡት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በሚገባ መልመድ ያልቻሉ ህጻናት ሌሎች ቋንቋዎችን አቀላጥፈው ለማወቅ ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ Kroskrity (2010) በተጨማሪ እንደገለጹት እንደ ቋንቋ ፖሊሲ ውሳኔ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ እንዲቆዩ የሚታቀደው የጊዜ ርዝማኔ የተማሪዎችን የተፎካካሪነት ጥንካሬ፣ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ብቃት ብሎም በትምህርት ቤት ሊያሳዩ የሚችሉትን ውጤታማነት ለመተንበይ ይረዳል፡፡ ይህ ማለት ተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ ቆይታቸው በጣም ያጠረ ከሆነ በትምህርታቸው ደከም ያሉ፣ በአጠቃላይ ተሞክሯቸው ተፎካካሪነታቸው ያነሰና በስራ መስክ ተወዳዳሪነታቸው የቀነሰ ሊሆኑ እንደሚችሉ፤ እነዚህ ሁኔታዎች በስነልቦናዊ ሁኔታዎቻቸው ላይ ሳይቀር አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚፈጥሩ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

በሌላ በኩል የቋንቋ ግንዛቤ (Language awareness) በተለያዩ አውዶች ስለቋንቋ አጠቃቀም መሰረታዊ ንቃተ ህሊና ወይም እውቀት ይዞ መገኘትን የሚያመለክት ጽንሰሀሳብ ነው፡፡ ይህ ግንዛቤ በምን አይነት ማህበራዊ አውድ ቋንቋን በተገቢው ሁኔታ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ማወቅን የሚጠይቅ ነው፡፡ አንድን የተወሰነ የቋንቋ አሀድ ወይም ቅንብር በየትኛው ማህበረ-ፖለቲካዊና ባህላዊ አውድ መጠቀም እንደሚገባ የቋንቋ ግንዛቤ ዳራዊ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል (Andrews, 2007)፡፡ Andrews አያይዘው እንደጠቆሙት የተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀም ግንዛቤ እድገት በትምህርት ላይ የሚመሰረትና በቋንቋ መማሪያ ክፍል በተደጋጋሚ በሚደረጉ ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ሞዴል ልምምዶች የሚሰርጽ ነው፡፡

በአጠቃላይ በማህበረሰብም ሆነ በትምህርት ቤት ስለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የተያዘ አመለካከትና ትግበራ በቋንቋው አጠቃቀም ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ከመንግስት ፖለቲካዊ ፍላጎት እና አመለካከት ሌላ የቋንቋ እቅድና የመማሪያነት ምርጫ በሰዎች አሉታዊ አመለካከት ተጽእኖ ስር ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም የተነሳ በመማሪያ ቋንቋነት የተመረጠ ቋንቋ በትግበራ ደረጃ እንቅፋቶች ይጋረጡበታል፡፡ አንድ ለትምህርት መስጫነት በፖሊሲ ደረጃ የተመረጠን ቋንቋ ከኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊታ፣ ሪካዊና ሌሎች ታሳቢ ሁኔታዎች ምቹነት አኳያ አመዛዝኖ ተተግባሪነቱን ማረጋገጥም የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት ቤት በመተግበር ረገድ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለማቃለል ይረዳል፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ተግዳሮቶችን በቀጥታ የቃኙ በአማርኛ ቋንቋ የተሰሩ ተዛማጅ ጥናቶችን እምብዛም ለማግኘት አልተቻለም፡፡ ይሁንና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ ተግዳሮቶችን የሚመለከቱ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተሰሩ የተወሰኑ ጥናቶችን አጥኚዋ ለመፈተሽ ሞክራለች፡፡

የመጀመሪያው ተዛማጅ ጥናት በJeilan (2013)፣ challenges hampering mother-tongue education with special reference to Afan Oromo in the Eastern Hararge Zone በሚል ርእስ የቀረበ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ነው፡፡ የጄላን ጥናት የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋን በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር የአመለካከት፣ የትምህርት ግብአቶች የመምህራን ስልጠና ፣ የባለድርሻዎች ድጋፍ፣ የወላጆች ትምህርትና ግንዛቤ እንዲሁም የትምህርት ቤት ተሳትፎ

ምክንያቶችን በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እርከን አተገባበር መቃኛ ነጥቦች አድርገዋል፡፡ ጄላን በዚህ ጥናታቸው መጠናዊና አይነታዊ የጥናት ዘዴን ለመጠቀም በሚያስችለው ቅይጥ የጥናት ስልትን በመከተል፣ አሳሽ መጠይቆችን (survey questionnaires) ለ634 መምህራንና ለ134 ተማሪዎች በማቅረብ እንዲሁም በክፍል ምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በሰነድ ፍተሻ የተደገፉ መረጃዎችን በመጠናዊና አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች አደራጅተው በመተንተን የጥናት ውጤታቸውን አቅርበዋል፡፡ በጥናት ግኝታቸውም የፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ድጋፎች ጉድለት፣ ስለ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የማህበራዊ ግንዛቤ ክፍተት ፣ የወላጆችና የባለድርሻዎች የትምህርት ተሳትፎ ችግሮች የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትግበራ እንቅፋቶች መሆናቸውን አመላክተዋል፡፡

ይህ የኔ ጥናት ከጄላን ጥናት ጋር የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩባቸው ነጥቦች አሉ፡፡ የጄላን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ሁለቱም ጥናቶች አፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት ማቅረቢያ ቋንቋነት በመተግበር ዙሪያ በሚታዩ ችግሮች ላይ ያተኮሩ መሆናቸው ሲሆን፤ የሚለያዩት ደግሞ ጄላን ችግሩን ለመፈተሽ በተጠቀሙበት የመረጃ መሰብሰቢያ ተማሪዎች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል መተንተንን ያካተተ በመሆኑ ይለያያሉ፡፡ ከዚህም ሌላ የጄላን ጥናት ያተኮረበት አካባቢ ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ሲሆን ይህ ጥናት የተካሄደበት አካባቢ ደግሞ ጅማ ዞን ማና ወረዳ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም አካባቢያዊ ልዩነቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋው አተገባበር ልዩነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይህ ጥናት ታሳቢ አድርጓል፡፡

ሁለተኛው ጥናት በAlemayehu (2005) The Challenges of Mother Tongue Education: The Case of Wolayta በሚል ርእስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የአለማየሁ ጥናት አላማ በደቡብ ህዝቦች ክልል በተመረጡ የወላይታ ዞን አራት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በወላይትኛ አፍ መፍቻ ቋንቋ የሚሰጠው ትምህርት አተገባበር የሚታዩበትን ችግሮች በመፈተሽ መፍትሄ መጠቆምን ያለመ ነው፡፡ ጥናቱ በገላጭ የአጠናን ስልት በመመርኮዝ ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተን በደረሰበት ማጠቃለያ መሰረት፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት መጠቀም ለተማሪዎቹ ስነ-ትምህርታዊ፣ ስነልቦናዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎችን በማስገኘት ላይ የሚገኝ መሆኑን፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር የሚያስችሉ

የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የትምህርቱ ዘርፍ ባለድርሻዎች ድጋፍና አስተዋጽኦ ክፍተት የሚታይበት መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ይህ ጥናት ከአለማየሁ (2005) የቀደመ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ሁለቱም ጥናቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን መዳሰስ ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ነው፡፡ የሚለያዩት ደግሞ ሁለቱ ጥናቶች በተለያዩ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቦናዊና ባህላዊ አመለካከት ባሏቸው ማህበራዊ አካባቢዎች እና የተለያዩ ቋንቋዎች ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው በጥናት አካባቢዎቹ ሊኖሩ ከሚችሉ ስነልቦናዊና ባህላዊ ልዩነቶች የተነሳ የጥናት ውጤቶቹ ወደተራራቀ መደምደሚያ ሊደርሱ እንደሚችሉ የአጥኚዋ እምነት ነው፡፡

ሶስተኛዉ ተዛማጅ ጥናት በኀሰው የሺዋስ (2010 ዓ.ም) በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሶስተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ሲሆን “የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት የመጠቀም አመለካከቶችና ተግዳሮቶች፡- በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በከምባታና በወላይታ ቋንቋዎች ተተኳሪነት” በሚል ርዕስ የተጠና ነዉ፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ረገድ እየታዩ ያሉ አመለካከቶችንና እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን ማጥናት ነው፡፡ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ተግባር ላይ የዋሉት ዘዴዎች የፅሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ ሲሆኑ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም የተገኙ መረጃዎች ቅይጥ  የመረጃ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም በየንዑስ ርዕሰ ጉዳዮች ስር ተደራጅተው በገላጭ የትንተና ስልት ተተንትነዋል፡፡

ከመረጃ ትንተናዉ የተገኘዉ ዉጤትም አብዛኞቹ የጥናቱ ተተኳሪዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመሰጠቱ ደስተኞች እንደሆኑና እንደሚደግፉ ፣ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል) ባለፈ ግን ለትምህርት መስጫነት ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ይልቅ እንግሊዝኛን እንደሚመርጡ ለማወቅ መቻሉን የአመለካከቶቹ መንስኤዎችም ባብዛኛው ኢኮኖሚያዊ ፣  ስነትምህርታዊና ስነልቦናዊ ሆነው መገኘታቸውን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በማስተማር ሂደት አብይ ተግዳሮት ሆኖ የተገኘው ስነትምህርታዊ ተግዳሮት መሆኑንና የዚህ መንስኤው በአብዛኛው የፖለቲካ ቁርጠኝነት አለመኖር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የበጎሰው ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ጉዳይ የጥናቶቹ ርዕሶች የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ረገድ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች ዙሪያ ማተኮራቸዉ፣ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ተግባር ላይ የዋሉት ዘዴዎች የፅሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ መሆናቸው እና መረጃዎች ቅይጥ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም በየንዑስ ርዕሰ ጉዳዮች ስር ተደራጅተው በገላጭ የትንተና ስልት መተንተናቸዉ ነዉ፡፡

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከበጎሰው ጥናት ጋር የሚለይበት ሁኔታ አለ፡፡ ይኸዉም የበጎሰው ጥናት የተካሄደዉ በደቡብ ክልል በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በከምባታና በወላይታ ቋንቋዎች ተተኳሪነት ሲሆን ይህ ጥናት ግን በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በማና ወረዳ  አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ያተኮረ መሆኑ የበጎሰው ጥናት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ይህ ጥናት ግን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ የተወሰነ መሆኑ በጎሰው  የስልጤ፣ የሀዲያ፣ የከምባታና የወላይታ ቋንቋዎችን ያጠና ሲሆን፤ ይህ ጥናት አፋን ኦሮሞ ቋንቋ ላይ ያተኮረ መሆኑ እንዲሁም በጎሰው በጥናቱ የተማሪዎችን የቋንቋ አመለካከትና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ ያልዳሰሰ መሆኑ ይለያያቸዋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

## 3.1 የጥናቱ ስልት

ይህ ጥናት የሚከተለው ዘዴ ገላጭ (descriptive) ጥናታዊ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ በመታገዝ ትምህርታዊ ችግሮችን በቀረቡበት ሁኔታ በገለጻ አስደግፎ ለመተንተንና መፍትሄዎቻቸውን ለማቅረብ ምቹ በመሆኑ የተመረጠ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ መጠናዊና አይነታዊ ትንተናዎችን አጣምሮ የያዘ በመሆኑ ቅይጣዊ ዘዴ ላይ ያተኩራል፡፡

### 3.2 የጥናቱ አካላዮች

የዚህ ጥናት አካላዮች በጅማ ዞን በማና ወረዳ የሚገኙ ስድስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ እነዚህ በአመቺ ናሙና ዘዴ የጥናቱ አካላይ የተደረጉ በማና ወረዳ የሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሰሞዶ፣ ሳረዶ፣ ቢሊዳ፣ ገሩኬ ጅማቴ፣ ቡጡሬ፣ እና ቡሩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዚህ ጥናት አካላዮች ናቸው፡፡

## 3.3 የተጠኚዎች አመራረጥና የናሙና መጠን

## 3.3.1 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ በአንድ ወረዳ ውስጥ በአመቺ ናሙና ዘዴ በተመረጡ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አቀባበል ላይ የሚያተኩር በመሆኑና በጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በ6ኛ መማሪያ ክፍሎች የሚገኙ ተማሪዎች አጠቃላይ ቁጥር አንጻራዊ ውሱንነት የሚታይበት በመሆኑ ናሙና ተማሪዎችን ከመምረጥ ይልቅ ሁሉንም የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በመረጃ አቀባይነት ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ አጥኚዋ ወስናለች፡፡ በዚሁ መሰረት በጠቅላይ ንሞና ዘዴ በመደገፍ በጥናት ተተኳሪነት በተመረጡት ስድስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ2013 ዓ.ም በ26 መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከሚገኙ ጠቅላላ ቁጥራቸው 643 ተማሪዎች ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎች ለመሰብሰብ ታቅዶ በዚሁ መሰረት ተከናውኗል፡፡

## ሰንጠረዥ 1፡- የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች ንሞና

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤት ስም | መማሪያ ክፍል | የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች | የናሙና ብዛት | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መምህራን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰሞዶ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 4 | 110 | 110 | 2 |
| 2 | ሳረዶ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 3 | 82 | 82 | 1 |
| 3 | ቢሊዳ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 4 | 120 | 120 | 2 |
| 4 | ገሩኬ ጅማቴ 1ኛ ደረጃ ትምህርት | 4 | 126 | 126 | 2 |
| 5 | ቡጡሬ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 4 | 107 | 107 | 2 |
| 6 | ቡሩ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 3 | 98 | 98 | 1 |
| | ጠቅላላ ድምር | 22 | 643 | 643 | 10 |

*(ምንጭ፡-የ2013ዓ.ም. የየትምህርት ቤቶቹ የተማሪ ቅበላ ስታቲስቲክስ)*

በእነዚህ የጥናት ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2013ዓ.ም. ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በሰሞዶ በ4 መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 110፣ በሳረዶ በ3 የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ 82፣ በቢሊዳ በ4 መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 120፣ በገሩኬ ጅማቴ በ4 መማሪያ ክፍሎች 126፣ በቡጡሬ በ4 መማሪያ ክፍሎች 107 እና በቡሩ በ3 መማሪያ ክፍሎች 98 ተማሪዎች ናቸው፡፡

## 3.3.2 የመምህራን፣ ርእሰ መምህራንና የወላጅ ተወካዮች አመራረጥ

በሌላ በኩል የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት በማና ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች በአመቺ ናሙና ዘዴ በተመረጡት ስድስት ትምህርት ቤቶች ለመረጃ አቀባይነት የተመረጡት መምህራን፣ የትምህርት ቤት ርእሳነ መምህራንና የየትምህርት ቤቶቹ የወላጅ መምህራን ህብረት ሊቃነመናብርት በአላማ ተኮር ናሙና ዘዴ የተመረጡ ናቸው፡፡፡ በዚሁ መሰረት በታላሚዎቹ ትምህርት ቤቶች አፋን ኦሮሞ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን አጠቃላይ ብዛት 10 /አስር/ የየትምህርት ቤቶቹ ርእሳነ መምህራን ብዛት 6 /ስድስት/ የየትምርት ቤቶቹ ወመህ ሊቃነመናብርት 6 /ስድስት/ በመሆናቸው በአጠቃላይ 22 /ሃያ ሁለት/ መረጃ አቀባዮች መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶ በዚሁ መሰረት ተከናውኗል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት ሦስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ እነሱም፡- የጽሑፍ መጠይቅ፣ ቃለመጠይቅ እና የክፍል ምልከታ ናቸው፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመደገፍ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎቹ ከተጠኚዎቹ ተሰብስበዋል፡፡

### 3.4.1 የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሑፍ መጠይቅ ከተማሪዎቹ መረጃ አቀባዮች አስፈላጊውን መረጃ ለመቀበል የተዘየደ በመሆኑ በፍጥነትና በተገደበ ሁኔታ ተማሪዎቹ ሊሰጡ የሚገባቸዉን መረጃ እንዲያቀብሉ ለማድረግ ረድቷል፡፡ የተማሪዎቹ መጠይቅ የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአተገባበር ችግሮች ላይ ያተኮሩ 40 ዝግ መጠይቅ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል፡፡ ተማሪዎቹ የሚሰጡትን መረጃ በተቀላጠፈ አኳኋን ሞልተው እንዲያጠናቅቁ እና ብዙ ከማሰላሰል ተቆጥበው ከቀረቡላቸው አማራጭ መልሶች አንዱን በመምረጥ በቀላሉ እንዲመልሱ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ በዚሁ መሰረት ለተማሪዎቹ የቀረበላቸው መጠይቅ ወጥ በሆነ መልኩ ከሙሉ በሙሉ እስማማለሁ እስከ ፈጽሞ አልስማማም ባለ አምስት አማራጭ መልሶችን ያያዙ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል፡፡ የመጠይቅ ጥያቄዎቹን አቀራረብ በተሻለ አስተማማኝነት ለማስደገፍ ሲባል ከዚህ ቀደም በእነ Jeilan (2013)፣ Alemayehu (2005)

ለተመሳሳይ የጥናት አላማ መረጃ ለመሰብሰብ ተግባር አገልግለው ውጤታማ ከሆኑት ይዘቶች ለዚህ ጥናት እንዲስማሙ አድርጎ በማቀናበር ለመረጃ ስብሰባው ጠቀሜታ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡ በLikert Scale መመዘኛ መሰረት ለእያንዳንዱ የተማሪዎቹ ምላሽ ከ 1 እስከ 5 ነጥቦች ተሰጥተዋቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- ፈጽሞ አልስማማም------------1 ነጥብ
- አልስማማም------------------2 ነጥብ
- አቋም አልያዝኩም-------------3 ነጥብ
- እስማማለሁ------------------- 4 ነጥብ
- በጣም እስማማለሁ------------ 5 ነጥብ ይይዛሉ፡፡

ለተማሪዎቹ የቀረበው መጠይቅ ግልጽነት ለመጠበቅ ሲባል ተጠኚዎቹ በይበልጥ በሚገባቸው ወይም በሚረዱት የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ በመተርጎም የቀረበላቸው ሲሆን፣ ተማሪዎቹ በታላሚዎቹ ትምህርት ቤቶች መጠይቆቹን በሚሞሉበት ወቅትም አጥኚዋ በ6ቱም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአካል ተገኝታ የጥናቱን አላማ በማስረዳት ስለመጠይቁ አሞላል ግንዛቤ በመስጠት በጥንቃቄ እንዲሞሉ እገዛ አድርጋለች፡፡

### 3.4.2 ቃለ መጠይቅ

ቃለመጠይቅ በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች አፋን ኦሮሞ ቋንቋ ከሚያስተምሩ አስር መምህራን፣ ስድስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሳነ መምህራን፣ እንዲሁም ስድስት የወላጅ መምህራን ህብረት (ወመህ) ሊቃነመናብርት ጋር ተካሂዶ አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ለእነዚህ አካላት እንደየስራ ድርሻቸው የተለያየ የቃለመጠይቅ ይዘት ያላቸው በከፊል የተዋቀሩ የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

### 3.4.3 የክፍል ምልከታ

የክፍል ምልከታ ለዚህ ጥናት ቁልፍ መረጃ መሰብሰቢያ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ተመራማሪዎች ከሚፈልጓቸው ተጠኚዎች ጋር በመሆን የሚያደርጉትን እና የሚናገሩትን ነገር በቅርበት ሆነው እያዩና እየሰሙ በመመዝገብ መረጃ እንዲያገኙ የሚረዳ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ ከቃለ መጠየቁና ከጽሁፍ መጠይቁ በተጨማሪ በክፍል ውሰጥ የመማር ማስተማርን ሂደት በመምህሩ እና በተማሪዎቹ በኩል የሚፈለገውን መረጃ በቀጥታ በአይን እያዩ ለመሰብሰብ አስተማማኝ መሆኑን ስላመነችበት ጥቅም ላይ አውላለች፡፡ አጥኚዋ የክፍል ምልከታዎቹን ከማድረጓ በፊት በየትምህርት ቤቶቹ በመገኘት ከርእሰ መምህራኑ እና ከአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መምህራኑ ጋር በመገናኘት ትምህርቱ የሚሰጥበትን ክፍለ ጊዜ በማመቻቸት ለምልከታዋ አመቺ ጊዜ መርጣለች፡፡

በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መማሪያ ክፍሎች የትምህርት አተገባበርን በመማሪያ ክፍሎች ተገኝቶ እየተሰጠ ያለውን ትምህርት በመመልከት መረጃ የማግኘት ስራ ተከናውኗል፡፡ በዚሁ መሰረት በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በነሲብ በተመረጡ 6 /ስድስት/ የስድስተኛ መማሪያ ክፍሎች ለ2 /ሁለት/ ዙር ምልከታ በማካሄድ በ12 የምልከታ ዙሮች መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶ ነበር፡፡ ይሁንና በጊዜ እጥረት በ6ቱ ትምህርት ቤቶች አንድ አንድ ዙር ምልከታ ማዳረስ የተቻለ ሲሆን ሁለተኛው ዙር ምልከታ ማካሄድ የተቻለው ከስድስቱ በሦስቱ ብቻ

በማካሄድ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በዚህ መሰረት የክፍል ምልከታ ክትትሉ ከታቀደው በ75% የተከናወነ ነው፡፡ የክፍል ምልከታ መቃኛ ነጥቦች (Observation Check-List) በየትምህርት ቤቶቹ የተካሄዱትን ምልከታዎች ወጥነት ለመጠበቅና በየክፍሎቹ የተቃኙ የመማር ማስተማር ሂደቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

አጥኚዋ የጥናቱን አላማ ከግብ ለምድረስ እንዲቻላት መረጃዎችን ከሰበሰበች በኋላ የተገኙትን መረጃዎች ለጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች አመላለስ እንዲረዳት በሶስት ደረጃዎች በመክፈል አዘጋጅታለች፡፡ከጥናቱ ጥየቄዎች ጋር ባላቸው ተያያዥነት የእያንዳንዱን ጭምቅ ሀሳብ ወደ አንድ በማምጣት በገለጻና ማብራሪያ ተደግፈው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ከተማሪዎቹ የተሰበሰቡ መጠናዊ መረጃዎችን በስታቲስቲካዊ ስሌቶች ማለትም በፐርሰንት፣ በአጠቃላይ አማካይና መደበኛ ልይይት መስፈሪያዎች በመለካት በበቂ ትንተና እና ማብራሪያ በማስደገፍ አቅርባለች፡፡ ከመጠናዊ መረጃ ትንተናው በማስከተልም ከክፍል ምልከታ እና ከቃለ ምልልስ የተገኙትን መረጃዎች አይነታዊ የአተናተን ስልትን በመከተል በበቂ ትንተና እና ማብራሪያ በማስደገፍ ታቀርባለች፡፡ በተተነተኑት መጠናዊ እና አይነታዊ መረጃዎች በመመርኮዝም ማጠቃለያ ላይ ደርሳለች፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ መረጃዎች ትንተና

የዚህ ጥናት አካላዮች ከሆኑት በጅማ ዞን በማና ወረዳ የሚገኙ በአመቺ ናሙና ዘዴ የተመረጡ ስድስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሰሞዶ፣ ሳረዶ፣ ቢሊዳ፣ ገሩኬ ጅማቴ፣ ቡጡሬ እና ቡሩ  አስፈላጊ የጥናቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ይህን ጥናት ለማሳካት ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን (1) ለጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ ፣ ለጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መምህራን፣ርእሰ-መምህራንና የወላጅ መምህራን ህብረት (ወመህ) ተወካዮች ቃለመጠይቅና በሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የኦሮምኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍሎች የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ያተኮሩ የክፍል ምልከታዎች ስራ ላይ ውለው ችግሩን ለመተንተንና ለማብራራት የሚረዱ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

በእነዚህ የጥናት ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2013ዓ.ም ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በሰሞዶ በ4 መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 110፣ በሳረዶ በ3 መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 82፣ በቢሊዳ በ4 መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 120፣ በገሩኬ ጅማቴ በ4 መማሪያ ክፍሎች 126፣ በቡጡሬ በ4 መማሪያ ክፍሎች 107 እና በቡሩ በ3 መማሪያ ክፍሎች 98 በአጠቃላይ በ22 የመማርያ ክፍሎች በ6 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ643 ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተደገፈ መረጃ ለመሰብሰብ የታቀደ ቢሆንም፤ ይህን ጥናት የሚመለከቱ መረጃዎች ለመሰብሰብ አጥኚዋ በተተኳሪዎቹ ትምህርት ቤቶች በተንቀሳቀሰችባቸው ወቅቶች ተማሪዎች በየመማሪያ ክፍሎቻቸው ተሟልተው ያለመገኘት ችግር ጎልቶ ይስተዋል ስለነበር፤ መረጃ ለመሰብሰብ የቻለችው ከ502 የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ብቻ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት በአጥኚዋ ከታቀደው 78.1% የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተደገፈ መረጃ ለመሰብሰብ የተቻለ ሲሆን፤ ባለንበት የኮሮና ወረርሽኝ ወቅት በገጠር ቀመስ አካባቢዎች ከሚገኙ ተጠኚዎች መረጃ ለመሰብሰብ ያለውን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት የተገኙት መረጃዎች በቂ እንደሆኑ በማሰብ የጥናቱን ትንተና በነዚሁ መረጃ አቀባዮች ተጨባጭ የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ተሞክሮ ላይ በማስመርኮዝ ተከናውኗል፡፡ ከተማሪዎቹ መረጃ አቀባዮች የተሰበሰቡ መረጃዎች መጠናዊ የመረጃ አተናተን ዘዴ ላይ በመደገፍ በዚህ ምዕራፍ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

በሌላ በኩል ከአስር የየትምህርት ቤቶቹ የኦሮምኛ ቋንቋ መምህራን፣ ከስድስት የየትምህርት ቤቶቹ ርእሳነ-መምህራንና ከስድስት የወላጅ መምህራን ህብረት /ወመህ/ ተወካዮች በድምሩ ከሃያ ሁለት ተሳታፊዎች በቃለመጠይቅ የተደገፈ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን፤ በተጨማሪ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መማሪያ ክፍሎች የትምህርት አተገባበርን በመማሪያ ክፍሎች ተገኝቶ እየተሰጠ ያለውን ትምህርት በመመልከት መረጃ የማግኘት ስራ ተከናውኗል፡፡ በዚሁ መሰረት በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በነሲብ በተመረጡ የስድስተኛ መማሪያ ክፍሎች ለ2 /ሁለት/ ዙር ምልከታ በማካሄድ በ12 የምልከታ ዙሮች መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶ ነበር፡፡ ይሁንና በጊዜ እጥረት በ6ቱ ትምህርት ቤቶች አንድ አንድ ዙር ምልከታ ማዳረስ የተቻለ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ዙር ምልከታ ማካሄድ የተቻለው ከስድስቱ በሦስቱ ብቻ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የክፍል ምልከታ ክትትሉ ከታቀደው በዘጠኙ /75%/ የተከናወነ ሲሆን፤ የክፍል ምልከታ መቃኛ ነጥቦች (Observation Check-List) በየትምህርት ቤቶቹ የተካሄዱትን ምልከታዎች ወጥነት በመጠበቅ በየክፍሎቹ የተቃኙ የመማር ማስተማር ሂደቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ተሰብስበው በአይነታዊ ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ የጥናቱ መረጃዎች ትንተናና ማብራሪያ ቀርቧል፡፡

## 4.1 የጥናቱ መረጃ አቀባዮች ግላዊ መረጃዎች ትንተና

የዚህ ንኡስ ምዕራፍ ቅኝት ያተኮረው በተጠኚዎቹ ተማሪዎች ግላዊ መረጃዎች ላይ ነው፡፡ የተጠኚዎቹ ግላዊ መረጃዎች ለዋናው ጥናት የሚረዱ የመረጃ ግብአቶችን ለማግኘት ያላቸውን እገዛ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የተማሪዎቹ እድሜ፣ ጾታ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ችሎታ ደረጃ፣ የወላጅ /አሳዳጊ/ የትምህርት ዳራ፣ የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጋልጦ እና በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መጻፊያ (ቁቤ) መጻፍ ተጠኚዎቹ ያላቸው አመለካከትና ፍላጎትን የሚመለከቱ በጽሁፍ መጠይቅ ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች ለተማሪዎቹ መረጃ አቀባዮች ቀርበውላቸው የሰጧቸው ምላሾች ከዚህ በታች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 41.1. የመረጃ አቀባይ ተማሪዎች እድሜና ጾታ

በዚህ ጥናት ተሳታፊ ከሆኑት 502 የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በጾታ 271 (53.98%) ወንድ ሲሆኑ የተቀሩት 231 (46.02%) ሴቶች ናቸው፡፡ ይህም ምንም እንኳ የወንዶች ተማሪዎች ቁጥር

አንጻራዊ ብልጫ ያለው ቢሆንም በወንድና ሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ዙሪያ ያን ያህል ጉልህ የትምህርት ተሳትፎ ልዩነት አለመኖሩን አመላካች ነው፡፡

በሌላ በኩል የጥናቱ መረጃ አቀባዮች የእድሜ ስብጥር እንደሚያሳየው ከሁሉም የሚበዙት 156 (31.1%) እድሜያቸው 13 ዓመት የሆኑት ሲሆኑ፣ ቀጥሎ 124 (24.7%) 14 ዓመት፣ 112 (22.3%) እድሜያቸው 12 እና በታች የሆኑ፣ 64 (12.7%) እድሜያቸው 15 ዓመት፣ 36 (7.2%)እንዲሁም የተቀሩት 10 (2%) ከ16 ዓመት እድሜ በላይ እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ መረጃ መገንዘብ እንደተቻለው አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች 392 (78.1%) በእድሜ ከ12 እስከ 14 አመት የሆኑ ተጠኚዎች ናቸው፡፡ ከዚህ የመረጃ አውድ በተለይ የምንገነዘበው አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች ትምህርት በመጀመሪያ እድሜያቸው ላይ ሲደርሱ በኦሮምኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍሎች የመማር እድል (access) ያገኙና ልጆች ለመማር በደረሱበት እድሜ በኦሮምኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ለመማር፣ ወላጆችም ልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ትምህርት እንዲከታተሉላቸው አጠቃላይ ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት እንዳለ በተዘዋዋሪ ለመገመት የሚያስችል ነው፡፡

## 4.1.2. የመረጃ አቀባይ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ችሎታ

የተጠኚዎቹን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ችሎታ ደረጃ ለማወቅ በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

*ሰንጠረዥ 1፡- የተጠኚዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ዳራ*

| ተ.ቁ | የቋንቋ ክሂል | እጅግ በጣም ጥሩ | | በጣም ጥሩ | | ጥሩ | | ደህና | | ዝቅተኛ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በ | በ% | በቁ. | በ% | |
| 1 | መናገር | 302 | 60.2 | 178 | 35.5 | 22 | 4.4 | --- | --- | --- | --- | 502 |
| 2 | ማዳመጥ | 291 | 58.0 | 180 | 35.9 | 31 | 6.2 | --- | --- | --- | --- | 502 |
| 3 | ማንበብ | 176 | 35.1 | 166 | 33.1 | 91 | 18.1 | 69 | 13.7 | --- | --- | 502 |
| 4 | መጻፍ | 112 | 22.3 | 138 | 27.5 | 152 | 30.3 | 54 | 10.8 | 46 | 9.2 | 502 |

*(ምንጭ፡- ከጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተገኘ የመስክ መረጃ፣ 2013ዓ.ም.)*

ከፍ ሲል ስለተጠኚዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የተለያዩ ክሂሎች ዳራ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያለውን ተጨባጭ የቋንቋ ልምድ በግልጽ የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ ከሁሉም የክሂል ዘርፎች ተጠኚዎቹ በመናገርና ከዚያም ቀጥሎ በማዳመጥ ክሂሎች ያላቸው ዳራ እውቀት ከማንበብና መጻፍ ክሂሎች የተሻለ መሆናቸውን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ በእርግጥ ተፈጥሯዊ

በሆነው የቋንቋ መማር ባህሪ መናገርና ማዳመጥ በትምህርት ቤት ውስጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ከመጀመራቸው አስቀድሞም ከወላጆቻቸውና ከማህበራዊ አካባቢያቸው ጋር በሚያደርጓቸው መስተጋብሮች መልመድ የሚጀምሯቸው ናቸው፡፡

ይህ መሰረታዊ የቋንቋ ለመዳ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመማር መነሻ ሆኖ የሚታሰብ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁንና የተማሪዎቹ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ከመናገርና ማዳመጥ ክሂሎች ችሎታዎቻቸው ጋር ሲነጻጸሩ አንጻራዊ ዝቅታ ላይ የሚገኙ (ከፍ ያለ ብቃት እንደሌላቸው) መረጃዎቹ ይጠቁማሉ፡፡ በተለይ ከሁሉም የክሂል አይነቶች የተጠኚዎቹ አጠቃላይ ችሎታ በአንጻራዊ  አንሶ የሚገኘው በአፍ መፍቻ ቋንቋ መጻፍ ክሂል ዙሪያ መሆኑን እናጤናለን፡፡ ከአጠቃላዮቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች በመጻፍ ክሂል እጅግ ከፍ ያለ ተፎካካሪነት እንዳላቸው ያረጋገጡት 112 (22.3%) ብቻ ሲሆኑ በማንበብ ክሂል ደግሞ 176 (35.1%) እጅግ ከፍ ያለ ተፎካካሪነት ያላቸው መሆናቸውን የጠቆሙ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የተጠኚዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ብቃት (ከመጻፍ ክሂል በቀር) ሲታይ በአብዛኛው በጣም ጥሩ ሊባል የሚችል ነው፡፡ ይህም በተዘዋዋሪ መንገድ በተጠኚዎቹ ዘንድ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር አሉታዊ አመለካከት ወይም ፍላጎት መኖሩን አያሳይም፡፡

## 4.1.3. የመረጃ አቀባይ ተማሪዎች ወላጆች የትምህርት ዳራ

ቀጥሎ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማር ወላጆች /አሳዳጊዎች/ ያላቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጠቀሜታ ግንዛቤ ወሳኝ ነው፡፡ ይህንኑ መሰረት በማድረግ አጥኚዋ የጥናቱ ተሳታፊዎች ወላጆች የትምህርት ዳራ ምን እንደሚመስል ከዋናው መረጃ ትንተና በፊት ለማጤን የሚያስችል መረጃ ሰብስባለች፡፡ ይሁንና በዚህ ጥናት የወላጆችን የትምህርት ዳራ ለማጤን የተሞከረው ብዙ ተምረዋል ወይም አውቀዋል ከሚል አንድምታ ሳይሆን ትምህርት ቀመስ የሆነ ወላጅ /ማህበረሰብ/ ልጆቹን ይማሩልኝ ብሎ ወደ ትምህርት ቤት ከመላክ ተነሳሽነት ባለፈ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማራቸውና ስለ ጠቀሜታው የተሻለ መረዳት ይኖረዋል፣ የሚል አስተሳሰብን በመያዝ ነው፡፡ በዚሁ መነሻ በሰንጠረዥ 2 ከስር የተጠኚዎቹን ወላጆች አጠቃላይ የትምህርት ዳራ የሚመለከት ምላሽ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

*ሰንጠረዥ 2፡- የተጠኚዎቹ ወላጆች የትምህርት ዳራ*

| | የወላጆች የትምህርት ዳራ ሁኔታ | በቁጥር | በ% |
|---|---|---|---|
| 1 | አባትና እናት ማንበብና መጻፍ የተማሩ | 64 | 12.7% |
| 2 | ከሁለቱ አንዳቸው ማንበብና መጻፍ የተማሩ | 85 | 16.9% |
| 3 | ሁለቱም ቢያንስ ማንበብና መጻፍ ያልተማሩ | 157 | 31.3% |
| 4 | ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው 8ኛ ክፍል የጨረሱ | 78 | 15.5% |
| 5 | ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው 10ኛ ክፍል የጨረሱ | 66 | 13.2% |
| 6 | ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው ኮሌጅ ዲፕሎማ የጨረሱ | 38 | 7.6% |
| 7 | ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው ከዲፕሎማ በላይ የጨረሱ | 14 | 2.8% |
| | ድምር | 502 | 100% |

*(ምንጭ፡- ከጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተገኘ የመስክ መረጃ፣ 2013ዓ.ም.)*

ከፍ ሲል በሰንጠረዥ 2 የቀረበው የወላጆች የትምህርት ዳራ መረጃ ስለጥናቱ ተሳታፊዎች የመማር ተሞክሮ በርካታ ጉዳዮችን ያስጨናል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በቁጥር የሚበዙት 157 (31.3%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሁለቱም ወላጆች ቢያንስ ማንበብና መጻፍ ያልተማሩ መሆናቸውን የጠቆሙ ናቸው፡፡ ሌሎች አንጻራዊ ብልጫ ያላቸው 85 (16.9%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ወላጆች ከሁለቱ አንዳቸው ማንበብና መጻፍ የተማሩ መሆናቸውን የጠቆሙ፣ ከዚህ በቁጥር በመጠኑ ዝቅ ያሉ 78 (15.5%) ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው 8ኛ ክፍል የጨረሱ መሆናቸውን የጠቆሙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ የሚነጻጸሩ 66 (13.2%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው ወላጆቻቸው 10ኛ ክፍል የጨረሱ መሆናቸውን የጠቆሙ ናቸው፡፡ ሌሎች በቁጥር 64 (12.7%) የጥናቱ ተሳታፊዎች አባትና እናት ማንበብና መጻፍ የተማሩ መሆናቸውን የገለጹ ሲሆኑ፣ ዝቅተኛ ቁጥር ያላቸው 38 (7.6%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው ኮሌጅ ዲፕሎማ የጨረሱ መሆናቸውን የጠቆሙ ናቸው፡፡ በመጨረሻም በጣም ዝቅተኛ ቁጥር ያላቸው 14 (2.8%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው ወላጆቻቸው ከዲፕሎማ በላይ የጨረሱ መሆናቸውን የጠቆሙ ናቸው፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋን የመማሪያ ቋንቋ የማድረግ እሳቤ ከብዝሃ ቋንቋ ፖሊሲ የሚመነጭ ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት እሳቤ ተማሪዎችን ከትምህርት መጀመሪያ እድሜያቸው ጀምሮ በማህበረሰባዊ የእለት ተእለት ተግባቦታቸው ተፎካካሪ

ለማድረግ የሚረዳ እንደሆነም ይታመናል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች እውቀት፣ ክህሎትና ልምድ የተዋቀረበት ከሚኖሩበት ማህበረሰብ የተወረሰ ልምድና ችሎታን የትምህርቱ አውድ መግባቢያ ለማድረግ የታለመ ነው፡፡ በዚህ እሳቤ መሰረት ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በትጋትና በተሻለ ተፎካካሪነት እንዲማሩ ወላጆች ያላቸው ሚና ከፍ ያለ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ በዚህ መሰረት በጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ወላጆች ልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማራቸውን በተሻለ ግንዛቤ ላይ ተመስርተው ሊያበረታቱ እንደሚችሉ የሚታሰቡት ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው ከዲፕሎማ በላይ የጨረሱ ፣ ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው ኮሌጅ ዲፕሎማ የጨረሱ፣ ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው 10ኛ ክፍል የጨረሱ እና ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው 8ኛ ክፍል የጨረሱ በሚሉት የምላሽ መክፈያዎች የተካተቱት እንደሆኑ ይታሰባል፡፡ ሆኖም እነዚህ የተጠኚዎቹ ወላጆች አጠቃላይ ድምር 196 (39%) ነው፡፡ ከጥናቱ ተሳታፊዎች በጣም የሚበዙት 306 (61%) ያህሉ ወላጆቻቸው ጉልህ የመማር ተሞክሮ አላቸው የማይባሉ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት የሚበዙት የጥናቱ ተሳታፊዎች ወላጆች ለትምህርት ያላቸው አስተሳሰብ ልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማራቸው የሚያስገኘው ጠቀሜታ የሚያሳስባቸውና በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርን በቅርበት የሚያግዙ ወይም የሚያበረታቱ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡

## 4.1.4 የመረጃ አቀባይ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጋልጦ

ሌላው ጥናቱ በቀዳሚነት ካተኮረባቸው ግላዊ መረጃዎች መካከል ተጠኚዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መበረታታት አስተዋጽኦ እንዳለው ታሳቢ የተደረገው የታላሚው ቋንቋ አካባቢያዊ አገልግሎት ነው፡፡ ተማሪዎች በመኖሪያ አካባቢያቸው አፍ የፈቱበት ቋንቋ በስፋት የሚነገር ከሆነና ለአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሰፊ ተጋልጦ ያላቸው ከሆነ ይኸው ቋንቋ በትምህርት ማቅረቢያነት ማገልገሉ የሚሰጧቸውን ተግባራት ለመረዳትና በቅጡ ለማከናወን እንዲሁም ከአጠቃላይ የመማር አመለካከታቸው፣ ተነሳሽነታቸው፣ የክፍል ተሳትፏቸውና ተግባቦታቸው ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለው የሚታሰብ ነው፡፡ በዚህ መነሻ በመኖሪያ አካባቢያችሁ በስፋት የሚነገረው መግባቢያ ቋንቋ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁሉም 502 (100%) የጥናቱ ተሳታፊዎች የጠቀሙት ኦሮምኛ ቋንቋ (አፋን ኦሮሞ) መሆኑን ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ለተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማሪያ ቋንቋነት መቅረብና ለታላሚው ቋንቋ ያላቸው አካባቢያዊ ተጋልጦ ሙሉ በሙሉ በአዎንታዊ

ዝምድና የሚጨን መሆኑን ነው፡፡ ይህም ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ተነሳሽነትና ፍላጎት መቀስቀስ የራሱ ድርሻ ያለው ነው፡፡

## 4.1.5 ተጠኚዎች በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መጻፊያ (ቁቤ) ያላቸው ተነሳሽነት

በመጨረሻ የቀረበላቸው ጥያቄ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መጻፊያ (ቁቤ) መጻፍ ላንተ/ቺ/ እንዴት ነው? የሚል ሲሆን የመጻፍ ክሂል ለበርካቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች ከባድና ውስብስብ መሆኑን የሚጠቁሙ ምላሾችን ከጥናቱ ተሳታፊዎች ማግኘት ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት ከጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል በቅደም ተከተል ሁለት ራሳቸውን የቻሉ ቡድኖች እያንዳንዳቸው 66 (13.1%) ‹‹በጣም ቀላል ነው›› እና ‹‹ቀላል ነው›› የሚሉ አቻ ምላሾችን የሰጡ ናቸው፡፡ ሌሎች 89 (17.7%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ደግሞ ‹‹ምንም አይልም›› ያሉ ሲሆኑ፣ 101 (20.1%) ‹‹ከባድ ነው›› እንዲሁም ከሁሉም የሚበልጡት 200 (39.8%) ‹‹በጣም ከባድ ነው›› የሚሉ ምላሾችን ሰጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ በእፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መጻፊያ (ቁቤ) መጻፍ ከግማሽ በላይ (ወደ 60% ለሚጠጉ) የጥናቱ ተሳታፊዎች በጣም ከባድ ወይም ከባድ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ በእርግጥ በሁሉም ቋንቋ መማሪያ አውዶች የመጻፍ ክሂል እጅግ ውስብስብነት የሚታይበትና በበርካታ አእምሯዊና ስነልቦናዊ ምክንያቶች አስቸጋሪነት የሚታይበት ክሂል ነው፡፡ በኦሮምኛ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ ይህን የተማሪዎችን በ‹‹ቁቤ›› የመጻፍ ችግር በስፋትና በጥልቀት መርምሮ ሳይንሰዊ መፍትሄ መሻት የሌሎች የመስኩ አጥኚዎችን ተሳትፎ የሚጋብዝ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ከታችኛው የክፍል እርከን ጀምሮ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሃሳብ የማመንጨትና የመግለጽ ተሞክሮን እያዳበሩ መጓዝ ወደፊት በእውኑ አለም ተግባቦቶቻቸው ራሳቸውን በሚገባ ለመግለጽና ተፎካካሪ ጸሃፊ ለመሆን ከወዲሁ የመጻፍ ተነሳሽነታቸው ላይ ያለው ተግዳሮት መወገድ አለበትና፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ወደ ጥናቱ ቁልፍ መረጃዎች ትንተና እንሸጋገራለን፡፡ በተለያዩ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት የጥናቱ መረጃዎች የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ባላቸው ተዛምዶ መሰረት ከዚህ በታች በቅደም ተከተል ቀርበው ትንተናና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 4.2. አፋን ኦሮሞን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ረገድ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮች

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ውጪ ማስተማር ዓሳን ከሰፊው መኖሪያ ውሃው ውጪ አውጥቶ በትንሽ ገንዳ ውስጥ እንደማኖር የሚቆጠር ነው፡፡ ቋንቋና ባህል ለአንድ ማህበረሰብ የግንዛቤውና የእውቀቱ መሰረቶች ናቸው፡፡ ከተለያየ ማህበረሰብ ተውጣጥተው ወደ ትምህርት ቤቶች የሚመጡ ህጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የተላመዷቸው የተለያዩ ማህበራዊ ዳራዎች፣ ልዩ ልዩ ተግባቦታዊና ተግባራዊ ልምዶች፣ ክሂሎችና አመለካከቶች አሏቸው፡፡ እነዚህ ዳራዊ ሁኔታዎች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚማሯቸውን ትምህርቶች ቀላል ለማድረግ አጋዥ በመሆናቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማራቸው የሚማሯቸውን ነገሮች በይበልጥ እንዲረዱ፣ የመማር ተነሳሽነትና ፍላጎታቸው ከፍ እንዲል፣ በትምህርታቸውም ውጤታማ እንዲሆኑ አጋዥ ነው፡፡ ይሁንና የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዱ በተለያዩ ተግዳሮቶች ተጽእኖ ስር የሚገኝ ከሆነ ከመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጠበቀውን ውጤታማነት ዝቅ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋንኛ ትኩረት በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያነት በመካሄድ ላይ የሚገኘው የመማር ማስተማር ክንዋኔ የሚታዩበትን ችግሮች መፈተሽ በመሆኑ፤ በተለያዩ የመረጃ መቀበያ ስልቶች የተገኙ ውጤቶች ከዚህ በታች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በዚህ መሰረት በቅድሚያ የተተነተኑት ከተማሪዎቹ የተሰበሰቡ መጠናዊ መረጃዎች ሲሆኑ አንጻራዊ ተመሳሳይነት ያላቸውን ገላጮች /አመልካቾች/ አንድ ላይ በሰንጠረዦች በማደራጀት በአጠቃላይ አማካይ በመደበኛ ልይይት ስታቲስቲክ እየተሰሉ ትንተናና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ቀጥሎም ከተለያዩ የጥናቱ ተሳታፊዎች በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ባላቸው ጠቀሜታ መሰረት አይነታዊ መረጃዎች መጠናዊ መረጃዎች ትንተናን ተከትለው እየቀረቡ ትንተናና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

### 4.2.1 ከትምህርት የይዘት አቀራረብ ጋር የተያያዙ ችግሮች

*ሰንጠረዥ 3፡- የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ይዘት አቀራረብ ዙሪያ ስላሉ ተግዳሮቶች የሰጧቸው ምላሾች*

| | ገላጮች /አመልካቾች/ (n=502-1) | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ለጽሁፍ የሚያገለግሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላት ስያሜዎች ለመረዳት ይከብዳሉ፡፡ | 4.54 | .378 |
| 2 | የተለያዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላትን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ አቻ ትርጉም አሟልቶ የያዘ መዝገበ ቃላት በቤተመጻህፍት አናገኝም፡፡ | 4.50 | .407 |
| 3 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የጽሁፍ ቋንቋ ከመሆኑ ጋር ሰዋስዋዊ ስርዓቱን መለየት ትምህርቱን ከባድ አድርጎብኛል፡፡ | 4.01 | .521 |
| 4 | በክፍል ውስጥ እውቀት የሚተላለፍበት መንገድ ከቋንቋ ግንዘቤዬ ጋር የተገናዘበ በመሆኑ ለኔ የመማር ሂደት አስደሳች ነው፡፡ | 3.67 | .501 |
| | አጠቃላይ የአማካይ አማካይ | 4.187 | 0.451 |

*(ምንጭ፡- ከጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተገኘ የመስክ መረጃ፣ 2013ዓ.ም.)*

ከፍ ሲል የቀረበው ሰንጠረዥ ተጠኚዎቹ ከአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ይዘት አቀራረብ ጋር የሚያያዙ ስነ-ትምህርታዊ ችግሮችን የጠቆሙ ሲሆን ፤ የሰጧቸውን ምላሾች ከፍ ካለው ውጤት ዝቅ ወዳለው ውጤት (descending order) በመዘርዘር ቀርበዋል፡፡ በሰንጠረዥ 3 እንደቀረበው የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ አሉታዊ እና የመጨረሻው አንዱ አዎንታዊ የጥያቄ አቀራረብን የተከተሉ ናቸው፡፡ ከ502 የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል ይበልጡን እጅ የያዙት 176 (35.1%) በጣም እስማማለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቆሙ፣ 149 (29.7%) እስማማለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቆሙ፣108 (21.5%) አልስማማም የሚለውን አማራጭ ያመለከቱ እና 69 (13.7%) መልስ ከመስጠት እታቀባለሁ የሚለውን አማራጭ ያመለከቱ ሲሆኑ ፈጽሞ አልስማማም ያሉ መላሾች የሉም፡፡በሌላ በኩል የጥናቱ ተሳታፊዎች በሰንጠረዥ 3 ለቀረቡት ገላጮች የሰጡት ምላሽ (ከፍ ሲል በቀረበው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ በቀረበው መሰረት) አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ)= 4.187 ሲሆን አማካይ መደበኛ ልይይት= 0.451 ነው፡፡ አማካይ መደበኛ ልይይቱ ዝቅተኛ (ከ0.5) በታች ሆኖ መገኘቱም እያንዳንዱ ምላሽ ሰጪ የሰጠው ምላሽ ከአጠቃላይ የአማካይ አማካዩ ያልራቀ (ያላፈነገጠ) መሆኑን ወይም ተጠኚዎቹ ለገላጮቹ የሰጧቸው ምላሾች ተቀራራቢነትን የሚያሳይ ነው፡፡

በዝርዝር ሲታይ፤ የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ለጽሁፍ የሚያገለግሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላት ስያሜዎች ለመረዳት ይከብዳሉ የሚለው የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዱ አንገብጋቢ ችግር ሆኖ የተጠቆመ ሲሆን አጠቃላይ አማካይ 4.54 እና መደበኛ ልይይት ልኬት 0.451 ነው፡፡ በቅደም ተከተል ቀጥሎ የተለያዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላትን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ አቻ ትርጉም አሟልቶ የያዘ መዝገበ ቃላት በቤተመጻህፍት በበቂ አናገኝም የሚሉት የጥናቱ መረጃ አቀባዮች በአጠቃላይ አማካይ 4.50 እና በተጓዳኝ መደበኛ ልይይት ልኬት 0.407 የተሰላ ሲሆን፤ የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የጽሁፍ ቋንቋ የጥናቱ መላሾች አስተያየት አጠቃላይ አማካይ 4.01 እና መደበኛ ልይይት 0.521 የተሰላ ሲሆን ፤ በክፍል ውስጥ እውቀት የሚተላለፍበት መንገድ ከቋንቋ ግንዘቤዬ ጋር የተገናዘበ በመሆኑ ለኔ የመማር ሂደት አስደሳች ነው፤ የሚለው ገላጭ በአጠቃላይ አማካይ 3.67 እና በተጓዳኝ መደበኛ ልይይት ልኬት 0.501 ተሰልቷል፡፡

መ.ቁ.4፣5 እና 6 በበኩላቸው እንደገለጹት ምንም እንኳን ኦሮምኛ ቋንቋ በባህሉ ውስጥ በሚገባ የሚታወቁ ጽንሰሀሳቦችን ለመግለጽ በራሱ ብቁ ሆኖ ሳለ፤ በመጽሐፉ ዝግጅት ወቅት አንዳንድ ሳይንሳዊ ቃላትን በተሟላ ሁኔታ የመተርጎም ችግሮች እንደሚታዩና ይህም በተማሪዎቹ መረዳት ላይ የራሱ ተጽእኖ እንዳለው አስረድተዋል፡፡ አያይዘውም አንድ የመማሪያ ቋንቋ በተናጋሪዎቹ ዘንድ በሚገባ በሚታወቁ መገልገያ ቃላት ተጠቅሞ ሃሳቦችንና ውስብስብ ጉዳዮችን በማብራራት ተግባቦትን ማገዝ ያለበት በመሆኑ በኦሮምኛ አፍ መፍቻ ቋንቋ አውድ ይኸው መሟላት ስላለበት፤ ለሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ እንዲሁም በባህሉ ለማይታወቁ አንዳንድ ጽንሰሃሳቦች መፍቻ የሚያገለግል ትምህርታዊ መዝገበ ቃላት ዝግጅት በብዛትእና በጥራት ከአፍ መፍቻ ቋንቋው ትግበራ ጋር አብሮ መታሰብ ያለበት መሆኑ ይሰማኛል ብለዋል፡፡

አንድን አፍ መፍቻ ቋንቋ በመማሪያ ቋንቋነት በስራ ላይ ከማዋል ጋር ወደ ታላሚው ቋንቋ ባህል የሚመጡ እንግዳ ወይም አዳዲስ ቁሶችን፣ ነገሮችን፣ ሂደቶችንና ጽንሰሃሳቦችን ከማህበረ-ባህላዊው እድገትና ለውጥ ጋር አብሮ ማስኬድ መቻል ሲሉ መ.ቁ.7 እና 8ም በተመሳሳይ መልኩ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ በርካታ ተማሪዎች አስተካክለውና አርመው ለመጻፍ እንደሚቸገሩ አስተውያለሁ፡፡ ይህ ከአጻጻፍ ጋር ተያይዞ የሚስተዋል ችግር ምናልባትም የላቲን ፊደል አጻጻፍን የሚጠቀሙ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን የሚተገብሩ ከኦሮምኛ ቋንቋ ውጪ ያሉ ሌሎች ቋንቋዎችም ችግር ሊሆን ይችላል፡፡ ችግሩ

ከጽህፈት ስህተት እርማት ተደጋጋሚ የመምህሩ ጥረት ውጪ እንዴት ሊቃለል እንደሚችልም ልገልጽልሽ አልችልም፣ ሲሉ የግል አስተያየታቸውን አጠቃለዋል፡፡

ሌላው በቃለ መጠይቁ ወቅት የተሰጠው አስተያየት፣ የአንደኛ ክፍል መጽሀፍ ብዙ ጊዜ ቃላትና ከዚያ በላይ የሆኑ የቋንቋ መዋቅሮችን በማስጠናት ነው የሚጀምረው፡፡ይህ አቀራረብ ቅድመመደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው ለመጡ ተማሪዎች ተገቢ ሊሆን ቢችልም፣ ገጠር ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎች ግን ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ገጠር ውስጥ የሚኖሩ ህጻናት ቅደመመደበኛ ትምህርት እንደ ከተማ ህጻናት በአግባቡ አይማሩም፡፡ሆኖም ግን ከተማ ውስጥ ቅድመመደበኛ ትምህርት ከተማሩ ተማሪዎች ጋር በተመሳሳይ መማሪያ መጻህፍት እንዲማሩ መደረጋቸው ችግር እየፈጠረ ነው ብለዋል፡፡ ሌላው በመማሪያ መጽሀፍቱ ውስጥ ተደጋጋሚ የትምህርት ይዘቶች መኖራቸው፣ በአመቱ የትምህርት ክፍለጊዜ የማይጠናቀቅ አድርጎታል ብለዋል፡፡

ሲጠቃለል እንደ የቃለመጠይቁ ተሳታፊ መምህራን ጥቆማ የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለትምህርት መስጫነት በመጠቀም ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ተግዳሮቶች መካከል የማስተማሪያ ቋንቋው የመደበኛነት ችግር፣ ሳይንስን ለማስተማር የሚሆኑ የአፍ መፍቻ ቃላት እጥረት ወይም አለመኖር፣ የመማሪያ መጻህፍት ይዘት ለተማሪዎቹ ችሎታ መመጠን ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በመማሪያ መጽሀፍቱ ውስጥ ያሉት ቃላት፣ ጽንሰሀሳቦችና የትምህርቱ ይዘቶች በአብዛኛው እንኳን የሚከብዱ ናቸው፡፡ የሚሉ መምህራን ጥቆማ የችግሩን ስፋት ለመረዳት የሚያግዝ ነው፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፍቱ ውስጥ የሚቀርበው የትምህርት ይዘት የተማሪዎችን የክፍል ደረጃና እድሜ ባማከለ መልኩ ቢዘጋጅ ጥሩ ነው የሚል አስተያየት መምህራኑ ሰጥተዋል፡፡

### 4.2.2 ከመማርያ አውድ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ድጋፍ አሰጣጥ ጋር የተገናኙ ችግሮች

የትምህርቱን ስራ በባለቤትነት የሚመሩ፣ የሚያስተባብሩና የመማር ማስተማሩን ሂደት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያካሂዱ ርእሰመምህራንና መምህራን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን በማጠናከር ትምህርቱ የታለመለትን መርሃግብራዊ ግብ እንዲመታ በማድረግ ረገድ ያላቸው ድርሻ ወሳኝ ነው፡፡ በሌላም በኩል የትምህርት ባለድርሻዎችና አጋሮች ድጋፍና ክትትል የትምህርቱን ስራ አጠናክሮ ለማስቀጠል ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንዳለው

ይታመናል፡፡ በዚህ መሰረት ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መጠናዊና አይነታዊ መረጃዎች ከዚህ በታች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

*ሰንጠረዥ 4፡- የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ ስለሚያገኙት ድጋፍ የሰጧቸው ምላሾች*

| | ገላጮች /አመልካቾች/ (n=502-1) | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደር በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርን በሚገባ ያበረታታል፡፡ | 4. 25 | .445 |
| 2 | የአፍ መፍቻ ቋንቋን መሰረት ባደረገው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የእስካሁኑ ተከታታይ ቆይታዬ ያገኘሁት ግንዛቤና ተሞክሮዬ በበኩሌ አበረታች እንደሆነ እረዳለሁ፡፡ | 4.19 | .550 |
| 3 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የቋንቋና የባህል ክበባት በማደራጀት ተማሪዎች ተሳትፎ እንድናደርግ ያበረታታል፡፡ | 3.78 | .587 |
| 4 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደርና መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ አጠቃቀም አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖረን በየጊዜው ግንዛቤ ይሰጡናል፡፡ | 3.35 | .518 |
| 5 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመማር ያገኘሁት እድል ሌሎች ሁለተኛ ቋንቋዎችን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት አስተዋጽኦ አድርጎልኛል፡፡ | 2.72 | .318 |
| | አጠቃላይ የአማካይ አማካይ | 3.67 | 0.484 |

*(ምንጭ፡- ከጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተገኘ የመስክ መረጃ፣ 2013ዓ.ም.)*

ከፍ ሲል በቀረበው ሰንጠረዥ 4 የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ ስለሚያገኙት ድጋፍ የሰጧቸውን ምላሾች በስታቲስቲካዊ ዋጋ ክብደት መሰረት በቅደም ተከተል ተፈርጀው ተተንትነዋል፡፡ ከ502 የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል ይበልጡን እጅ የያዙት 152 (30.3%) እስማማለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቆሙ፣ 129 (25.7%) በጣም እስማማለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቆሙ፣ 101 (20.1%) መልስ ከመስጠት እታቀባለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ ያመለከቱ፣ 86 (17.1%) አልስማማም የሚለውን አማራጭ የጠቆሙ እና ቀሪዎቹ 34 (6.8%) ፈጽሞ አልስማማም የሚለውን አማራጭ ያመለከቱ ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት የጥናቱ ተሳታፊዎች ከፍ ሲል

በሰንጠረዥ 4 ለቀረቡት ገላጮች የሰጡት ምላሽ አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ)= 3.67 ሲሆን አማካይ መደበኛ ልይይት= 0.484 ነው፡፡ እዚህም ላይ አማካይ መደበኛ ልይይቱ ዝቅተኛ (ከ0.5) በታች ሆኖ መገኘቱ እያንዳንዱ ምላሽ ሰጪ የሰጠው ምላሽ ከአጠቃላይ የአማካይ አማካዩ ያልራቀ (ያላፈነገጠ) መሆኑን ወይም ተጠኚዎቹ ለገላጮቹ የሰጧቸው ምላሾች ተቀራራቢነት ጉልህነቱን የሚጠቁም ነው፡፡

በሰንጠረዥ 4 እንደምናጤነው፣ በቀዳሚነት የጥናቱ ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስተዳደሮች የተማሪዎቹን በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርን እንደሚያበረታቱ በአጠቃላይ አማካይ 4.25 እና ከዚሁ ተጓዳኝ በሆነው መደበኛ ልይይት 0.445 መስክረዋል፡፡ ቀጥሎም የአፍ መፍቻ ቋንቋን መሰረት ባደረገው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የእስካሁኑ ተከታታይ ቆይታቸው ያገኙት ግንዛቤና ተሞክሮ በየበኩላቸው አበረታች እንደሆነ መገንዘባቸውን የገለጹበት ስታቲስቲካዊ ልኬት በአጠቃላይ አማካይ 4.19 እና ከዚሁ ተጓዳኝ በሆነው መደበኛ ልይይት 0.550 የተደገፈ ነው፡፡ በቅደም ተከተል የየትምህርት ቤቶቹ አስተዳደሮች የቋንቋና የባህል ክበባት በማደራጀት ተማሪዎች ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያበረታቱ ስለመሆናቸው የተገለጸበት ስታቲስቲካዊ ልኬት በአጠቃላይ አማካይ 3.87 እና ከዚሁ ተጓዳኝ በሆነው መደበኛ ልይይት 0.587 የተደገፈ ነው፡፡ (በሁለቱ ገላጮች የሚታዩ ከ0.5 በላይ የሆኑ መደበኛ ልይይቶች አንጻራዊ ስፋት የጥናቱ ተሳታፊዎች ለገላጮቹ ያላቸው አቋም በመጠኑ የተራራቀ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡)

በሌላ በኩል የትምህርት ቤቱ አስተዳደርና መምህራን ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ አጠቃቀም አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው በየጊዜው ግንዛቤ የሚሰጡ ስለመሆኑ በተጠኚዎቹ የተገለጸበት ስታቲስቲካዊ ልኬት በአጠቃላይ አማካይ 3.78 እና በተጓዳኙ መደበኛ ልይይት 0.518 ተደግፏል፡፡ ይህም የጥናቱ ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርእሳነመምህራንና መምህራን ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ አጠቃቀም አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው የሚያደርጉት የግንዛቤ ድጋፍ እጅግ ጉልህ ነው ለማለት ባይቻልም ጥረቱ በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በመጨረሻም በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመማር ያገኙት እድል ሌሎች ሁለተኛ ቋንቋዎችን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት አስተዋጽኦ ያደረገላቸው ስለመሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች እማኝነት የተገለጸበት ስታቲስቲካዊ ልኬት በአጠቃላይ አማካይ 2.72 እና በተጓዳኙ መደበኛ ልይይት 0.318 ተደግፎ ቀርቧል፡፡

ይህ በጣም ዝቅተኛ ውጤት የሚያሳየው በጥናቱ ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመማር ያገኙትን እድል ሌሎች ሁለተኛ ቋንቋዎችን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት አስተዋጽኦ እንዲያደርግላቸው የሚደረገው እገዛ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ ተተኳሪ የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ ከርእሰ መምህራንና መምህራን የሚያገኟቸው ድጋፎች በአጠቃላይ የአማካይ አማካይ 3.67 ስታቲስቲካዊ ልኬት የሚመዘኑ መሆናቸው የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደትን በእጅጉ ለማጠናከር ከፍ ያለ ተነሳሽነት መኖሩን አመላካች አይደለም፡፡ በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች ድጋፎቹ ውሱንነቶች የሚታይባቸው ቢሆንም ጥረቶቹ እጅግ በጣም የተቀዛቀዙ ናቸው ለማለት ግን አይቻልም፡፡

## 4.2.3 ከመምህራን ስልጠና ጋር የተያያዙ ችግሮች

ተማሪዎችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዶች በሚገባ ለማትጋት የመምህራን ዝግጁነት ትልቅ ገንቢ ሚና ያለው ነው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ስኬት የበርካታ አመላካቾች ጥንካሬ ድምር ውጤት ነው፡፡ ይሁንና የመምህራን የማስተማር ተነሳሽነትን ያህል በጣም አስፈላጊ መሰረታዊ ሁኔታ የለም ለማለት ይቻላል፡፡ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ የሚያገኙት ድጋፍ ጥንካሬ የመምህራኑ ዝግጁነት ፣ ስልጠና ፣ ተሃድሶ ፣ ሙያዊ ተደሳችነት ውጤት ነው፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች ባልተሟሉበት ለተማሪዎቻቸው የሚያደርጓቸው ድጋፎች የሚያበረታቱ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

*ሰንጠረዥ 5፡- የጥናቱ ተሳታፊዎች ከመምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ተበረታችነት ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች የሰጧቸው ምላሾች*

| | ገላጮች /አመልካቾች/ (n=502-1) | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሁሉንም የትምህርት አይነቶች የሚያስተምሩ መምህራን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ በሚገባ የመናገርና የመጻፍ ችሎታ ያላቸው ናቸው፡፡ | 4. 05 | .445 |
| 2 | መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ችሎታ የመማር ማስተማሩን ሂደት ተስማሚ አድርጎልኛል፡፡ | 3.97 | .561 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | እኔ በምማርበት ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት እንድበረታታ ተከታታይ በሆነ መልኩ እገዛ ያደርጉልኛል፡፡ | 3.88 | .662 |
| 4 | መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የሚያጋጥሙኝን ችግሮች በማቃለል ሁሌም ድጋፍ ያደርጉልኛል፡፡ | 3.01 | .499 |
| | አጠቃላይ የአማካይ አማካይ | 3.88 | 0.542 |

*(ምንጭ፡- ከጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተገኘ የመስክ መረጃ፣ 2013ዓ.ም.)*

ከፍ ሲል በሰንጠረዥ 5 እንደቀረበው የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ ስለሚያስተምሩ መምህራን ተበረታችነት የሰጧቸውን ምላሾች በስታቲስቲካዊ ዋጋ ክብደት መሰረት በቅደም ተከተል ተሰልተው ቀርበዋል፡፡ ከ502 የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል ይበልጡን እጅ የያዙት 139 (27.7%) እስማማለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቆሙ 112 (22.3%) በጣም እስማማለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቆሙ፣ 98 (19.5%) መልስ ከመስጠት እታቀባለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ ያመለከቱ፣ 84 (16.7%) አልስማማም የሚለውን አማራጭ የጠቆሙ እና ቀሪዎቹ 69 (13.7%) ፈጽሞ አልስማማም የሚለውን አማራጭ ያመለከቱ ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት የጥናቱ ተሳታፊዎች ከፍ ሲል በሰንጠረዥ 5 ለቀረቡት የመምህራን ተበረታችነት ገላጮች የሰጡት ምላሽ አጠቃላይ የአማካይ አማካይ ($\ddot{x}$) = 3.88 ሲሆን አማካይ መደበኛ ልይይት =0.542 ነው፡፡ እዚህም ላይ አማካይ መደበኛ ልይይቱ ዝቅተኛ (ከ0.5) በላይ ሆኖ መገኘቱ እያንዳንዱ ምላሽ ሰጪ የሰጠው ምላሽ ከአጠቃላይ የአማካይ አማካዩ በመጠኑ የራቀ (ያፈነገጠ) መሆኑን ወይም ተጠኚዎቹ ለገላጮቹ የሰጧቸው ምላሾች ተቀራራቢነት የሌላቸው መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

በተጠኚዎቹ ምላሽ መሰረት በቅደም ተከተል ሁሉንም የትምህርት አይነቶች የሚያስተምሩ መምህራን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ በሚገባ የመናገርና የመጻፍ ችሎታ ያላቸው ስለመሆናቸው በአጠቃላይ አማካይ 4.05 እና በመደበኛ ልይይት 0.445 የተደገፈ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ቀጥሎም መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ችሎታ የመማር ማስተማሩን ሂደት ተስማሚ አድርጎልኛል ለሚለው ገላጭ በአጠቃላይ አማካይ 3.97 እና በመደበኛ ልይይት 0.561 የተደገፈ ነው፡፡ በሌላ በኩል እኔ በምማርበት ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት እንድበረታታ ተከታታይ በሆነ መልኩ እገዛ

ያደርጉልኛል ለሚለው ገላጭ በአጠቃላይ አማካይ 3.88 እና በመደበኛ ልይይት 0.662 የተደገፈ ነው፡፡ በቅደም ተከተል በቀረቡት ሁለቱ ገላጮች በመደበኛ ልይይት የተመዘገበው አንጻራዊ ስፋት ጉልህነት የሚያመለክተው ተጠኚዎቹ ለገላጮቹ የሰጡት ምላሽ የተራራቀ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ይህም በተተኳሪዎቹ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ችሎታና ተበረታችነት የመማር ማስተማሩን ሂደት ተስማሚ ለማድረግ ያለው እገዛ ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት የሚለያይ መሆኑን የሚያሳይ ይሆናል፡፡ ቀጥሎም መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የሚያጋጥሙኝን ችግሮች በማቃለል ሁሌም ድጋፍ ያደርጉልኛል ለሚለው ገላጭ ተጠኚዎቹ የሰጡት ምላሽ በአጠቃላይ አማካይ 3.01 እና በመደበኛ ልይይት 0.499 የተደገፈ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ይህም የመምህራኑን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ድጋፍ መጠን ውሱንነት የሚታይበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

የመምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ተበረታችነት ለመማር ማስተማሩ ሂደት ስኬታማነትና ለተማሪዎቹ ውጤታማነት ያለው ድጋፍ ገደቦች የሚታዩበት መሆኑን የተተነተኑ መጠናዊ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ መናገር ይቻላል፡፡ ይህንኑ ከመምህራኑ ዝግጁነት መጠን ጋር አያይዞ ለማወቅ ለጥናቱ ተሳታፊ መምህራን በቃለመጠይቅ መረጃ መቀበያ ላይ ያተኮረ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መምህርነት ያለዎት ስልጠና እንዴት ነው? በቋንቋው በማስተማር ያለዎት ልምድስ ምን ይመስላል? በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ በማስተማር ላይ እያሉ ያገኙት የስራ ላይ ስልጠና ካለ አያይዘው ቢገልጹልኝ? ይህን የመጠይቅ ጥያቄ ማቅረብ ያስፈለገው የመምህራኑን ሙያዊ ዳራ፣ የማስተማር ልምድና የስራ ላይ ስልጠና /ተሃድሶ/ ሁኔታዎችን የሚመለከቱ መረጃዎች ተማሪዎችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዶች በሚገባ ለማትጋት ያላቸውን ጠቀሜታ ለማወቅ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት በዚህ የቃለመጠይቅ 2 መምህራን በመምህራን በሌላ የትምህርት ዘርፍ በማሰልጠኛ ተቋም የሰለጠኑ መሆናቸውን የገለጹ ሲሆን 6 መምህራን ደግሞ በአፋን ኦሮሞ ትምህርት በኮሌጅ የሰለጠኑ እና የተቀሩት 2 መምህራን ደግሞ ከመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ስልጠና በኋላ ለዲግሪ መርሃ ግብር የሙያ ማሻሻያ ስልጠና በጅማና ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲዎች የክረምት ኮርሶችን በመከታተል ላይ ያሉ መሆናቸውን

ጠቁመዋል፡፡ በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ በማስተማር ከ5 እስከ 18 አመት የማስተማር ልምድ ያላቸው ሲሆኑ፤ የረጅም ጊዜ የማስተማር ልምድ ያላቸው በተለይ በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም የሰለጠኑ መሆናቸው ታውቋል፡፡ በሌላ በኩል ሁሉም መረጃ አቀባዮቹ መምህራን አፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆኑ ሲሆኑ ከፊሎቹ በሁለተኛ ቋንቋ የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ችሎታቸው "በጣም ጥሩ" ወይም "ጥሩ" መሆኑን የገለጹ ሲሆኑ፤ ከፊሎቹ ደግሞ "ደህ" ወይም "ዝቅተኛ" እንደሆነ የጠቆሙ ናቸው፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ችሎታቸው "እጅግ በጣም ጥሩ" የተግባቦት ችሎታ ያላቸው የአንደኛ ደረጃ መምህራን የሉም፡፡

ከሁለቱ የዩኒቨርሲቲ የክረምት ኮርስ የመከታተል እድል ካገኙ መምህራን በቀር የተቀሩት መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህርነት በመስራት ላይ ባሉበት ወቅት ሁሉ ምንም አይነት የተሃድሶ ስልጠና አግኝተው የማያውቁ ናቸው፡፡ በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ በቅድመ ስራ ከሰለጠኑት መምህራን መካከልም በቀጥታ ከሰለጠኑበት የትምህርት አይነት ጋር የተገናኙ ትምህርቶችን የማያስተምሩ አንዳንድ መምህራን እንዳሉ በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ለምሳሌ፣ አንዱ መምህርት በማህበራዊ ሳይንስ የስልጠና ፓኬጅ ውስጥ የሚገኙ ትምህርቶች ላይ ከሰለጠኑ በኋላ የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርትን እንዲይያስተምሩ መደረጋቸውን ጠቁመዋል፡፡

በተጎበኙት ትምህርት ቤቶች ብዙ የስልጠናም ሆነ የተሃድሶ እድሎችን ያላገኙ መምህራን በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዶች በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡ከእነዚህ መምህራን አንዳንዶቹ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ አፍ ፈት ስለሆኑ ወይም ቋንቋውን አጣርተው ስለሚያውቁ ብቻ አስቀድሞ ከነበረው የትምህርት ስርአት ወደ አፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማሪያ አውድ የመጡ ነባርና የረጅም ጊዜ የማስተማር ልምድ ያላቸው ናቸው፡ የረጅም ጊዜ የማስተማር ልምድ ስላላቸው ወይም ታላሚውን ቋንቋ አጣርተው ስለሚያውቁ /ስለሚግባቡበት/ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዱ መመደባቸው ችግር ላይኖርበት ይችላል፡፡ ነገር ግን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ እንዴት እንደሚያስተምሩ በዎርክሾፕ፣ ሴሚናርና ኮንፈረንስ የመሳሰሉ የተሃድሶ እድሎች እንዲሳተፉ በማድረግ ዘመኑ ከደረሰባቸው አዳዲስ ስነዘዴ ተኮር የሆኑ ክህሎቶችና ግንዛቤዎች ጋር እንዲተዋወቁ አልተደረጉም፡፡

ይህም አፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን ከመማር ማስተማር ጋር ተያይዘው የሚታዩ ችግሮችን ለማቃለል ወይም ተማሪዎቹን በተገቢ ሁኔታ ለመደገፍ ያስቸግራል፡፡ መምህራን የቋንቋው ተናጋሪ ስለሆኑና ልምድ ስላላቸው ብቻ እንዲያስተምሩ መመደብ ተገቢ አይደለም፡፡ በእርግጥ የመምህራን እጥረት በየገጠሩ በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጉልህ ችግር ነው፡፡ በእድሜ ወጣት የሆኑ የቅርብ ጊዜ ቅጥር መምህራን አብዛኞቹ ለፍልሰት /ስራ ለመልቀቅ/ የተጋለጡ ከመሆናቸው በቀር፣ ባሉበት ትምህርት ቤት በታላሚው ቋንቋ ሁለት ወይም ሶስት ተጓዳኝ የትምህርት አይነቶችን በአፍ መፍቻ ለማስተማር የሚያስችል የቅድመ ስራ ስልጠና ያገኙ ናቸው፡፡ ነባር መምህራን ግን ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር የተገናኘ ስልጠናም ሆነ ተሃድሶ ያላገኙ ናቸው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎችን ችግሮች በማቃለል ተማሪዎቹ ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲኖራቸው፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመማር እንዲበረታቱትና በራስ የመተማመን ባህሪ እንዲይዙ ሁሉም መምህራን ከሚያስተምሩበት መማሪያ መጽሐፍ ይዘትና አተገባበር ጋር የተያያዙ የተሃድሶ ስልጠናዎችን ጭምር ማግኘት ግድ የሚል ቢሆንም ይህ መሰረታዊ ጉዳይ በቂ ትኩረት አላገኘም፡፡

ከመምህራን ስልጠና ጋር በተያያዙ ተግዳሮቶች ዙሪያ ከጥናቱ ተሳታፊዎች ጋር በጥልቅ ወይይቶች የተደገፉ መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ እንደ ር/መ.ቁ.1 ገለጻ የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለትምህርት መስጫነት ለመጠቀም ወደ ተግባር ከተገባበት ወቅት ጀምሮ ካጋጠሙ ተግዳሮቶች መካከል አንዱና ዋንኛው በቋንቋው የሰለጠኑ መምህራን እጥረት አንዱ ነው:: እኔ በምመራበት ትምህርት ቤት ውስጥ በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ በማስተማር ሂደት በታላሚው የአፍ መፍቻ ቋንቋ በአግባቡ የሰለጠነ የሰው ሀይል  እጥረት ሲያጋጥመኝ ቆይቷል፡፡ የሰለጠነ የሰው ሀይል ለመማር ማስተማሩ ሂደት ስኬታማነት በተለይም ለትምህርቱ ጥራት ቁልፍ አስተዋጽኦ እንዳለው ቢታሰብም፣ በየትምህርት አይነቱና ባሉን ክፍሎች ስፋትና የተማሪዎች ብዛት ልክ መምህራን የሉንም ብለዋል፡፡

ር/መ.ቁ.2 በበኩላቸው የሰው ሀይል እጥረት ችግርን ሲያብራሩ፣ እንደሚታወቀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በአብዛኛው አፋን ኦሮሞ አፍ ፈት በሆኑ መምህራን የሚካሄድ ወይም በሌላ ቋንቋ አፍ ፈት ሆነው አፋን ኦሮሞ ቋንቋን በሚገባ የሚችሉ መምህራን መኖርን የግድ ይላል፡፡ ይሁንና በርካታ መምህራን በገጠር በሚገኙ ትምህርት ቤቶች እየሰሩ መቆየት ምቾት አይሰጣቸውም፡፡

በመሆኑም የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ተናጋሪ መሆናቸው ሊያስገኙላቸው የሚችሏቸውን ሌሎች አማራጮች ወደ መሞከር ፈጥነው ይሸጋገራሉ፡፡ ለመምህራን የገጠር አኗኗር የሚመጥን ደሞዝ መኖሪያቤት፣ጥቅማ ጥቅሞች ባለመኖራቸውና የኑሮ ንረት በሚፈጥሩባቸው ጫናዎች የተነሳ በገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር መቆየት የሚመርጡት በአብዛኛው ትዳርና ልጆች ያሏቸው መምህራን መሆናቸውን ከረጅም ጊዜ የሃላፊነት ተሞክሮዬ ያረጋገጥኩት ጉዳይ ነው፡፡ እኔ የማውቃቸው በርካታ ስራ የቀየሩ መምህራንም አሉ፡፡አንዳንዶቹ በቋንቋ እውቀታቸውና ከኦሮሞ ማህበረሰብ የወጡ መሆናቸውን መነሻ በማድረግ በገጠር ከማስተማር ሙያ ፈጥነው ለመላቀቅ የአካባቢው ታዋቂ ፖለቲካ ድርጅት አባል ይሆናሉ፡፡ አንዱ መምህር በዝምድና፣ በጓደኝነት፣ በመሳሰሉት መተገኛዎች በመጠቀም ወደ ከተማ ከተዛወረ ሌላውም ይህን አይነት እድሎችን ተጠቅሞ ለመልቀቅ ይተልማል፡፡በወረዳ ርእሰ ከተማ ወደሚገኝ የትምህርት ወይም ሌላ ቢሮ የሚደረግ ሽግግር /promotion/ በፖለቲካ አመለካከት እየተደገፈ ይካሄዳል፡፡

የፖለቲካውን ጠፍ ምህዳር በሰው ሃይል ለማልማት ሰው በአብዛኛው እንዲፈልስ የሚደረገው ከትምህርት ቤትና ከመምህራን ነው፡፡ መምህራን ደግሞ ታላሚውን ቋንቋ የሚያቀላጥፉ በመሆናቸው ይሳባሉ፡፡ በሌላ በኩል ሲሉ የሚቀጥሉት ር/መ.ቁ.2 አክለውም፤ በግል ጥረታቸው በቅርብ ርቀት ጅማ ዩኒቨርሲቲ በማታው ፕሮግራም የሚሰጠውን መርሃ ግብር በመከታተልና በማጠናቀቅ ወይም በተለያዩ የግል ኮሌጆች የርቀት ትምህርት ተከታትለው በመጨረስ የመምህርነት ሙያውን የሚለቁ መምህራንም አሉ፡፡ ይህም የሙያ ዘርፉ በሰለጠነ የሰው ሃይል ያለበት ነባር ችግር እንዳይቀረፍ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በርከት ያሉ ወጣት መምህራን ከማስተማር ሙያ ፈጥነው ለመላቀቅ የሚያስችሏቸውን ከማስተማር ስራ ውጪ ያሉ ምርጫዎች ለማጤን ከሶስት አራት አመት የበለጠ ጊዜ አይወስድባቸውም ብለዋል፡፡ይህ እንግዲህ መምህራን በገጠር በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እያስተማሩ ለመቆየት ካሉባቸው ስነልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚያሳይ ነው፡፡

ሌላው ር/መ.ቁ.3 እንደገለጹት፤በአፍ መፍቻ ቋንቋ እያስተማሩ ያሉት አንዳንዶቹ መምህራን አፋን ኦሮሞ ቋንቋን አጣርተው የሚናገሩ ይሁኑ እንጂ በአማርኛና በእንግሊዝኛ እንጂ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የሰለጠኑ አይደሉም፡፡ ቋንቋውን ይችላሉ በሚል ብቻ ተመድበው የሚያስተምሩ አሉ፡፡

በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማር ስልጠና ያገኙትም ቢሆን በመምህራን እጥረት የተነሳ የሰለጠኑበትን ትምህርት ብቻ የሚያስተምሩ አይደሉም፡፡ ያሉብንን የመምህር ክፍተቶች ለመሙላት ስንል ሌሎች የትምህርት አይነቶችን መጻህፍት አንብበው እንዲያስተምሩ የምናደርግበት ጊዜ ብዙ ነው ብለዋል፡፡

ከሰለጠነ የሰው ሀይል ምደባ ጋር ተያይዞ የወረዳው ትምህርት ቢሮ ራሱ በትምህርት ቤቱ ተመድበው በመስራት ላይ የሚገኙ መምህራን ብዛትና ትምህርት ቤቱ የሚያስተናግዳቸው ተማሪዎች ንጽጽር እንጂ በየትምህርት ቤቱ ያሉ የየትምህርት አይነት መምህራን እጥረት /ክፍተትን/ ለመሙላት እምብዛም አይጨነቅም የሚሉት ር/መ.ቁ.4 አያይዘውም ለምሳሌ በአንድ የትምህርት አይነት ሁለትና ሶስት መምህራን በትምህርት ቤቱ ኖረው የሌላው ትምህርት አይነት መምህራን አንድም ላይኖር ይችላል፡፡ አዳዲስ የሚመደቡ መምህራን ይህን ጉድለት መሙላትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ አይመደቡልንም ሲሉ ተችተዋል፡፡ መምህራን በሚያስተምሩበት የመማሪያ መጽሀፍት ዙሪያ በየጊዜው የተሃድሶ እድሎች አለማግኘታቸው ራሱ ከሰው ሃይል ብቃት እድገት ጋር የሚገናኝና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥን ከማዘመን /ማሻሻል/ ጋር የሚጎዳኝ ችግር እንደሆነም ር/መ.ቁ.4 አንስተዋል፡፡

ር/መ.ቁ.5 እንደሰጡት ገለጻ፤ እኔ ከመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ የተመረቅኩት ከ6 አመት በፊት ነው፡፡ ባለኝ የመማር ተሞክሮ መሰረት በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ የሚሰጡት ትምህርቶች ይዘት በአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን በመማሪያ መጻህፍት ከሚቀርቡት ይዘቶች አንጻር ሲታይ በጣም ሰፊ ወይም የተለጠጠና ጠቀሜታው ያነሰ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ሁለተኛ መምህራን በኮሌጅ በሚማሩዋቸው ኮርሶች ይዘቶችና በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ በቀረቡ ይዘቶች መካከል ስርአታዊ ቅንጅት አለመኖሩ ይሰማኛል፡፡ ሶስተኛ በኮሌጆች ደረጃ ለመምህራን ስልጠና የሚቀርቡ ኮርሶች አንዳንድ ይዘቶች በእጅጉ ውስብስብና ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መማሪያ መጻህፍት ይዘቶች ፍላጎት የማይመጥኑ ወይም ጠቀሜታ የሌላቸው ናቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች ይዘው ነው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለማስተማር የሚመጡት ብለዋል፡፡ እኒህ አስተያየት ሰጪ በተለይ ያመለከቱት በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚሰጡ ሙያዊ ኮርሶች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ዝግጅትና ለተማሪዎቹ ፍላጎት የማይመጥኑ መሆናቸውን ነው፡፡

### 4.2.4 ቁስ አካላውያን የትምህርት ግብሀቶች ስልጠና ጋር የተያያዙ ችግሮች

የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት ለመጠቀም ወደ ተግባር በሚገባበት ወቅት ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል በቋንቋው የተዘጋጁ መማሪያ መጽሀፍት፣ አጋዥ መጽሀፍትና ሌሎችም የትምህርት ቁሳቁሶችን በቀላሉ ለማሟላት መቸገር ዋነኛው ነው:: እነዚህ ችግሮች በአብዛኛው ከበጀት እጥረት፣ ከሙያተኞች አለመኖር፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን አላማ ፖለቲካዊ ብቻ አድርጎ ከመተርጎም የተነሳ የሚከሰቱ ወይም ሌሎች ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይታሰባል፡፡ ከዚህ በመነሳት በአፋን ኦሮሞ የአፍ መፍቻ የትምህርት መስጫ ቋንቋ አተገባበር ላይ እየተስተዋሉ ያሉ ቁሳቁስ /ሪሶውርስ/ ነክ ተግዳሮቶች ፍተሻ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

*ሰንጠረዥ 6፡- የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ስላሉ የሰው ሃይልና ቁሳቁሳዊ ተግዳሮቶች የሰጧቸው ምላሾች*

| | ገላጮች /አመልካቾች/ (n=502-1) | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | የመማሪያ ክፍሎቻችን ዴስኮችና ጥቁር ሰሌዳ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ተስማሚ ሁነው የተሰናዱ ናቸው፡፡ | 4.54 | .378 |
| 2 | በትምህርት ቤታችን ለምንማራቸው የትምህርት አይነቶች ሁሉ በቂ መምህራን ተመድበውልናል፡፡ | 3.78 | .407 |
| 3 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ በሁሉም የትምህርት አይነቶች የተዘጋጁ መማሪያ መጻሀፍት በየግላችን ይደርሱናል፡፡ | 3.12 | .521 |
| 4 | በቂ የሆኑ የመማሪያ መጻህፍት በትምህርት ቤታችን ቤተመጻህፍት ይገኛሉ፡፡ | 2.54 | .498 |
| 5 | በትምህርት ቤታችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መዝገበ ቃላት፣ ማገናዘቢያና አጋዥ መጻህፍት በበቂ ሁኔታ እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ | 2.12 | .418 |
| 6 | ለተማሪዎች ባህላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ትምህርታዊ ፍላጎቶች የሚመጥኑ የመማሪያ ቁሳቁሶች በትምህርት ቤታችን ተሟልተው ይገኛሉ፡፡ | 1.98 | .433 |
| | አጠቃላይ የአማካይ አማካይ | 3.61 | 0.443 |

*(ምንጭ፡- ከጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተገኘ የመስክ መረጃ፣ 2013ዓ.ም.)*

በሰንጠረዥ 6 የቀረበው መረጃ የሰው ሃይልና ቁሰቁሳዊ ተግዳሮቶችን ለማጤን የሚያግዝ ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ የሚታዩ የትምህርት መሳሪያዎችንና መርጃዎችን በተመለከተ ያሉባቸውን ችግሮች አቅርበዋል፡፡ ምላሾቻቸው በስታቲስቲካዊ ዋጋ ክብደት መሰረት በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል ከጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል ይበልጡን እጅ የያዙት 222 (44.2%) እስማማለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቆሙ 119 (23.7%) በጣም እስማማለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቆሙ፣ 107 (21.3%) መልስ ከመስጠት እታቀባለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ ያመለከቱ እና ቀሪዎቹ 54 (10.8%) አልስማማም የሚለውን አማራጭ የጠቆሙ ሲሆኑ ፈጽሞ አልስማማም የሚለውን አማራጭ ያመለከቱ የሉም፡፡

በዚሁ መሰረት የጥናቱ ተሳታፊዎች ከፍ ሲል በሰንጠረዥ 6 ለቀረቡት የመማሪያ ግብአቶች አቅርቦት ገላጮች የሰጡት ምላሽ አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ) = 3.61 ሲሆን አማካይ መደበኛ ልይይት= 0.443 ነው፡፡ አማካይ መደበኛ ልይይቱ ዝቅተኛ (ከ0.5) በታች ሆኖ መገኘቱ እያንዳንዱ ምላሽ ሰጪ የሰጠው ምላሽ ለአጠቃላይ የአማካይ አማካዩ የቀረበ መሆኑን ወይም ተጠኚዎቹ ለገላጮቹ የሰጧቸው ምላሾች ተቀራራቢነት የሚታይባቸው መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በጥናቱ ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መማሪያ አውድ በአብዛኛው የመማሪያ ቁሳቁሶች ችግሮች እንደሚታዩ ይስማማሉ ማለት ነው፡፡

በዝርዝር ሲታዩ የመማሪያ ክፍሎቻችን ዴስኮችና ጥቁር ሰሌዳ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ተስማሚ ሁነው የተሰናዱ ስለመሆናቸው የሰጡት ምላሽ በአጠቃላይ አማካይ 4.54 እና መደበኛ ልይይት 0.378 የተደገፈ ነው፡፡ ይህ የመላሾቹ ግብረ መልስ በገጠሩ በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ ለመማሪያነት ምቹ የሆኑ ክፍሎች ፣ የተማሪ ዴስኮችና ጥቁር ሰሌዳዎች በአብዛኛው ተሟልተው የሚገኙ መሆናቸውን የሚጠቁም ነው፡፡ ስለዚህ ምቹ መማሪያ ክፍል የአብዛኞቹ የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደት ጉልህ ችግር አይደለም ለማለት ይቻላል፡፡ ቀጥሎ የቀረበው በገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ የትምህርት አይነቶች ሁሉ በቂ መምህራን ስለመመደባቸው የተጠኚዎቹ ምላሽ በአጠቃላይ አማካይ 3.78 እና መደበኛ ልይይት 0.407 የተደገፈ ነው፡፡ ይህም በተለይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱን በተገቢ ሁኔታ ለማራመድ የመምህራን ምደባ ክፍተት የሚታይበት መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

በሌላ በኩል በአፍ መፍቻ ቋንቋ በሁሉም የትምህርት አይነቶች የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት በየግላችን ይደርሱናል ለሚለው ገላጭ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በአጠቃላይ አማካይ 3.12 እና መደበኛ ልይይት 0.521 ተደግፎ የቀረበ ነው፡፡ ይህም በጥናቱ ተተኳሪ የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሁሉም የትምህርት አይነቶች የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ለተማሪዎች አለመድረስ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዱ አሳሳቢ ችግር መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ቀጥሎም በቂ የሆኑ የመማሪያ መጻህፍት በየትምህርት ቤቱ ቤተመጻህፍት ተሟልተው ስለመገኘታቸው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በአጠቃላይ አማካይ 2.54 እና መደበኛ ልይይት 0.498 ተደግፎ የቀረበ ነው፡፡ ይህን መረጃ መሰረት በማድረግ መናገር የሚቻለው ተማሪዎች በነፍስ ወከፍ የማይደርሷቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ልዩ ልዩ መጻህፍት በየትምህርት ቤቱ ቤተመጻህፍት እንኳን ተደራሽ ለማድረግ አለመቻሉን ነው፡፡ ይህም የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያዳክም ተማሪዎቹ የሚሰጧቸውን ስራዎች ከመስራት የሚያግድና የትርፍ ጊዜ ንባብ ተሞክሮን የሚገታ ነው፡፡

በሌላ በኩል በጥናቱ ተተኳሪ የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መዝገበ ቃላት፣ ማገናዘቢያና አጋዥ መጻህፍት በበቂ ሁኔታ አለመኖር እና ለተማሪዎች ባህላዊ ፣ ስነልቦናዊ ፣ ትምህርታዊ ፍላጎቶች የሚመጥኑ የመማሪያ ቁሳቁሶች ተሟልተው አለመገኘት በየአንጻራቸው በአጠቃላይ አማካይ 2.12 እና መደበኛ ልይይት 0.418 እንዲሁም በአጠቃላይ አማካይ 1.98 እና መደበኛ ልይይት 0.433 ተደግፈው ቀርበዋል፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መዝገበ ቃላት ፣ ማገናዘቢያና አጋዥ መጻህፍት በበቂ ሁኔታ አለመኖር እና ለተማሪዎች ባህላዊ ፣ ስነልቦናዊ ፣ ትምህርታዊ ፍላጎቶች የሚመጥኑ የመማሪያ ቁሳቁሶች ተሟልተው አለመገኘት በተጠኚዎቹ ተማሪዎች የተጠቆሙበት መጠን ቁሳቁሳዊ ተግዳሮቶቹ የቱን ያህል አሳሳቢ እንደሆኑ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በተለይ ለተማሪዎች ባህላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ትምህርታዊ ፍላጎቶች የሚመጥኑ የመማሪያ ቁሳቁሶች በጥናቱ ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የድርቅ ያህል የሚቆጠሩ መሆናቸውን በምልከታ የተደገፉ መረጃዎችም በተጨባጭ ይጠቁማሉ፡፡

ከፍ ሲል ከቀረቡት መጠናዊ መረጃዎች በሚደጋገፍ መልኩ ከመምህራንና ርእሰመምህራን የተሰበሰቡ አይነታዊ መረጃዎች ከዚህ በታች ተተንትነዋል፡፡ ለር/መ.ቁ.1 በቀረበላቸው ጥያቄ ላይ በሰጡት ምላሽ፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ የትምህርት ቁሳቁሶችን ችግር

በተመለከተ የመማሪያ መጽሀፍት ለተማሪዎች በተገቢው መልኩ አለመዳረስ ወይም አንዳንዶቹ በትምህርት ቤት ውስጥ ከፍተኛ እጥረት ማጋጠም፤ የመምህሩ መምሪያ በአንዳንድ የትምህርት አይነቶች ጨርሶ አለመኖር፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የታተሙ የማጣቀሻ መጽሀፍት ያለመኖር ችግሮች አሉ በማለት ገልጸዋል፡፡ በተለይም አጋዥ መጽሀፍትን በሚመለከት ቋንቋውን እንደ ትምህርት ለማስተማር የተዘጋጀ ያልተሟላ መዝገበቃላት፣ የእንቆቅልሽና የምሳሌዊ ንግግር መጽሀፎች እንጅ በቋንቋው የተዘጋጁ ሌሎች አጋዥ መጽሀፍት የሉም ብለዋል፡፡

ር/መ.ቁ.2 በበኩላቸው በሰጡት አስተያየት የመምህሩ መምሪያ ተደራሽነት ያላቸው የተወሰኑ የትምህርት አይነት መማሪያ መጻህፍት ብቻ ናቸው፡፡ አንዳንድ የትምህርት አይነቶች ምንም የመምህሩ መምሪያ ሳይኖራቸው መምህራኑ እንዲያስተምሩ ይደረጋል፡፡ በመምህሩ መምሪያ ተሟልቶ አለመገኘት ዙሪያ የቃለመጠይቅ ተሳታፊ የሆኑ ሌሎች መምህራንም የሰጡት አስተያየት ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው፡፡

ሌላው አስተያየት ሰጪ ር/መ.ቁ.3 በበኩላቸው መማሪያ መጻህፍት ለተማሪዎች ተሟልተው አይደርሱም፡፡ በመማሪያ መጻህፍት እጥረት የተነሳ አንድ መማሪያ መጽሐፍ ለአራትና አምስት ተማሪዎች በጋራ እንዲገለገሉበት የምንሰጣቸው የትምህርት አይነቶች አሉ፡፡ እንደሚታወቀው በገጠር ከሚኖሩ ተማሪዎች ተራርቀው የሚኖሩ የሚበዙባቸው በመሆኑ መጻህፍትን በነፍስ ወከፍ ማዳረስ ለመማር ማስተማሩ ሂደት እንደ ትልቅ ድጋፍ የሚቆጠር ነው፡፡ ይሁንና በመማሪያ መጽሐፍ አለመዳረስ የተነሳ ወደ ቤት ይዘው የሚሄዱቸውን ስራዎች በሚገባ ማከናወናቸውን ለመቆጣጠር በመምህራኑ በኩል እንቅፋት እየገጠማቸው እንደሆነ አውቃለሁ ብለዋል፡፡

በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የተዘጋጁ የትምህርት ቁሳቁሶች ተሟልተው አለመገኘት በመምህራኑና ርእሰመምህራኑ መረጃ አቀባዮች ተደጋግሞ የቀረበ ዋንኛ ችግር ነው፡፡ የመማሪያ ቁሳቁሶች እጥረት የመማር ማስተማሩ ሂደት በሚፈለገው መልኩ እንዳይራመድ እንቅፋት የሚፈጥር ከመሆኑ ጋር በተማሪዎቹ ውጤታማነት ላይ ተጽእኖው ከፍተኛ ነው፡፡

ቤተመጻህፍትን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከማደራጀት ጋር ተያይዞ ባጋጠሙ ችግሮች ዙሪያ በተጎበኙት ትምህርት ቤቶች ከአንዳንዶቹ መምህራንና ርእሳነ መምህራን ጋር አጥኚዋ በሰፊው ለመወያየት ሞክራለች፡፡

መምህራኑም ሆኑ ርእሳነመምህራኑ ሁሉ በእርግጥ የአፍ ቋንቋ ትምህርትን ለማጎልበት በታላሚው ቋንቋ የተዘጋጁ የተማሪዎቹን የመረዳት ችሎታና ፍላጎት ያገናዘቡ ተነባቢ ክምችቶች መኖርን ያምናሉ፡፡ ነገር ግን ከመማሪያ መጻህፍት ውጪ ያሉ የማገናዘቢያ መጻህፍት፣ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የተዘጋጁ ልቦለዶችና ሌሎች እንደ ልሳነ-ክልኤ ያሉ መዝገበ ቃላትን ማግኘት የሚቻለው ከገበያ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ ስብስቦች በአንድ በኩል በበቂ ሁኔታ ከገበያ ላይ ማግኘት ያዳግታል፡፡

## 4.2.5 ከወላጆች የትምህርት ድጋፍ ጋር የተያያዙ ችግሮች

የወላጆች ድጋፍ ለትምህርት ስራ አጠቃላይ ስኬት ወሳኝ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በየትኛውም አለም ወላጆች በተማሪዎች አጠገብ የሚገኙ የቅርብ መምህራንና አማካሪዎች ናቸው፡፡ በተለይ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መስክ የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪዎቹ ወላጆች በጥልቀት በሚገነዘቡት ቋንቋ፣ ባህል፣ እሴቶችና ማህበረሰባዊ አካባቢያዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ የሚመሰረት እንደመሆኑ መጠን፣ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች በየትምህርቱ ይዘቶች ላይ ጭምር ያተኮሩ ችግሮችን ወላጆችና የቤተሰቡ ታላላቆች ሊያቃልሉላቸው ይችላሉ የሚል እሳቤ አለ፡፡ በዚሁ መሰረት ቀጥሎ በቀረበው መጠናዊ መረጃ ትንተና የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች የወላጆቻቸው ድጋፍ ምን እንደሚመስል ተቃኝቷል፡፡

*ሰንጠረዥ 7፡- የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ዙሪያ የወላጆችን ድጋፍ በተመለከተ የሰጧቸው ምላሾች*

| | ገላጮች /አመልካቾች/ (n=502-1) | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | ወላጆቼ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በአብዛኛው በቤት ውስጥ መጠቀማቸው በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ለመማር መነሳሳት ይጠቅሙኛል | 4.66 | .398 |
| 2 | ወላጆቼ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ይገልጹልኛል፡፡ | 3.82 | .477 |
| 3 | ወላጆቼ በትምህርት ጉዳይ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ሲጠሩ ለመገኘት አያመነቱም፡፡ | 2.53 | .431 |
| 4 | በቤተሰባችን ውስጥ ካሉ ታላላቆቼ ወይም ዘመዶች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቴ መጠናከር የሚረዳ ድጋፍ አገኛለሁ፡፡ | 2.42 | .518 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የተሻልኩ ሁኜ ለመገኘት የሚያስችሉ አጋዥ የንባብ መጻህፍትን ወላጆቼ እያመጡ እንዳነብ ያደርጉኛል፡፡ | 1.55 | .444 |
| | አጠቃላይ የአማካይ አማካይ | 2.99 | 0.454 |

*(ምንጭ፡- ከጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተገኘ የመስክ መረጃ፣ 2013ዓ.ም.)*

በሰንጠረዥ 7 የቀረበው መረጃ ከወላጆችና የተማሪዎች የቅርብ ዘመዶች ድጋፍ ጋር የተጎዳኙ ተግዳሮቶችን ለማጤን የሚያግዝ ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች የወላጆችን የትምህርት ተሳትፎ መጠን ለመገንዘብ የሚረዱ መረጃዎችን ሰጥተዋል፡፡ የሰጧቸው ምላሾች ባላቸው ክብደት መሰረት በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ከጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል የሚበልጡት 179 (35.7%) ፈጽሞ አልስማማም የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቆሙ፣ 158 (31.5%) አልስማማም የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቆሙ፣ 78 (15.5%) እስማማለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ ያመለከቱ፣ 46 (9.2%) በጣም እስማማለሁ እና ቀሪዎቹ 41 (8.2%) አቋም አልያዝኩም የሚለውን አማራጭ የጠቆሙ ናቸው፡፡ በአኳያው የጥናቱ ተሳታፊዎች ከላይ በሰንጠረዥ 7 ለቀረቡት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ዙሪያ የወላጆችን ድጋፍ ገላጮች የሰጡት ምላሽ አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ)=2.99 ሲሆን አማካይ መደበኛ ልይይት=0.454 ነው፡፡ አማካይ መደበኛ ልይይቱ እንደሌሎቹ የቀደሙ ትንተናዎች ዝቅተኛ (ከ0.5) በታች መሆኑ የስምምነቱ ማእቀፍ ጠባብ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

በዝርዝር ሲጤኑ የተጠኚዎቹ ከፍተኛ አዎንታዊ ስምምነት የታየው ወላጆች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በአብዛኛው በቤት ውስጥ መጠቀማቸው ለልጆቻቸው በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መማር መነሳሳት የፈጠረላቸው መሆኑ ሲሆን፤ ይህም በአጠቃላይ አማካይ 4.66 እና በመደበኛ ልይይት 0.398 ተደግፎ የቀረበ ነው፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው የአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማሪያ ቋንቋነት ጠቀሜታ ላይ መዋል ተማሪዎች አጣርተው በሚያውቁት ቋንቋ እንዲማሩ የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠሩንና ተማሪዎችም መነሳሳት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ቀጥሎም ወላጆች ለልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ስለሚያስገኘው ጠቀሜታ የሚገልጹላቸው የቱን ያህል እንደሆነ ተጠኚዎቹ የጠቆሙት በአጠቃላይ አማካይ 3.82 እና በመደበኛ ልይይት 0.477 ተደግፎ የቀረበ ነው፡፡ ይህ ልኬት ወላጆች ለልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ስለሚያስገኘው ጠቀሜታ በማስረዳት የሚያደርጉላቸው የቅርብ ድጋፍ በአስተማማኝ ደረጃ ላይ መገኘቱን የሚጠቁም አልሆነም፡፡

በእጅጉ አሳሳቢ ከሆኑት ወላጆችን የሚመለከቱ ጉዳዮች አንዱ ወላጆች በትምህርት ጉዳይ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ሲጠሩ የሚያሳዩት ፈቃደኝነት በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ ይህም በአጠቃላይ አማካይ 2.53 እና በመደበኛ ልይይት 0.431 የተጠኚዎቹ ምስክርነት ተደግፎ የቀረበ ነው፡፡ ቀጥሎ በቤተሰብ ውስጥ ካሉ ታላላቆች ወይም ዘመዶች ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መጠናከር የሚረዳ ድጋፍ በጣም ያነሰ መሆኑን በአጠቃላይ አማካይ 2.42 እና በመደበኛ ልይይት 0.518 የተጠኚዎቹ ምስክርነት ተደግፎ ቀርቧል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን ተጠኚዎቹ ተማሪዎች በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መማር የተሻለ ደረጃ ላይ እንዲገኙ አስተዋጽኦ የሚያደርጉላቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ አጋዥ የንባብ መጻህፍትንና ሌሎች ተነባቢ ነገሮችን በማግኘት በወላጆቻቸው በኩል የሚደረግላቸው ድጋፍ እጅግ በጣም ውሱን ነው፡፡ ይህ የተጠኚዎቹ ስምምነት የተገለጸበት መጠን በአጠቃላይ አማካይ 1.55 እና በመደበኛ ልይይት 0.444 የተጠኚዎቹ ምስክርነት የተደገፈ ነው፡፡

በቃለመጠይቅ ከወመህ የጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰበው መረጃም ከፍ ሲል ከቀረበው ትንተና ጋር ተደጋጋፊ ነው፡፡ አንድ የወመህ ተሳታፊ እንደጠቆሙት፤ የወላጆች የትምህርት ቤት ተሳትፎም ትርጉም ያለውና የአፍ መፍቻ  ቋንቋ ትምህርቱን ለማጠናከር የሚረዳ ነው ለማለት አያስችልም ብለዋል፡፡ ሌላኛው የወመህ የጥናቱ መረጃ አቀባይ በበኩላቸው ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተምረው ለአካባቢያቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ ለውጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ መሰረት የሚያስይዝ እገዛ ለልጆቻቸውም ለሚማሩበት ትምህርት ቤትም ሲያደርጉ አናይም፡፡ ሌላኛው ደግሞ ወላጆች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ባለቤቶች ናቸው፤ ከማለት ይልቅ የሂደቱ ተመልካቾች ወይም ታዛቢዎች ናቸው ማለት ይቀላል፤ ሲሉ ይተቻሉ፡፡ እኚሁ ተሳታፊ አክለውም እንዲያውም ጥቂት ወላጆች ልጆቻቸው ወደ ሁለተኛ ደረጃና ዩኒቨርሲቲ ሲገቡ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ይልቅ በእንግሊዝኛ ቋንቋ መማራቸው እያሳሰባቸው ይመስላል በአፍ መፍቻ ቋንቋው እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ ቢቀጥሉ ፍላጎት ሲያሳዩ የሚታዩ ወላጆች እንዳሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡

### 4.2.6 ከፖለቲካዊ እሳቤ ጋር የተያያዙ ችግሮች

በትምህርት ቤት የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት መጠቀም ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ትምህርታዊ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ታላሚውን ቋንቋ በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ሂደት የትምህርት ጥራቱን የሚፈታተኑ በርካታ ተግዳሮቶች እንደተከሰቱ የታወቀ ነው፡፡ የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሲገጥሙ የቆዩ ተግዳሮቶች ጠቅለል ብለው ስነትምህርታዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነልሳናዊና ኢኮኖሚያዊ ተብለው ሊገለጹ የሚችሉ ሲሆኑ ቁልፉ ግን የፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ማነስ ወይም አለመኖር እንደሆነ በርካታ የቃለመጠይቁ ተሳታፊዎች ይስማማሉ፡፡

ለዚህ ጥናት ሲባል የተፈተሹ ድርሳናትና ቀደምት ጥናቶች እንዳቀረቡት ፖለቲካ የትምህርት ስርአትን በማጠናከርም ሆነ በማጓተት የራሱ ተጽእኖ አለው፡፡ ምንጮች እንደሚጠቁሙት፤ ልሳነ ብዙ በሆነ ሀገር ውስጥ ከሀገረኛ ቋንቋዎች ይልቅ የቅኝ ገዥዎችን ቋንቋ ለትምህርት መስጫነት የመጠቀም ውሳኔ ከሚደረሰባቸው ፖለቲካዊ ምክንያቶች መካከል አንዱ ብሄረሰብ ሌላውን ወይም ሌሎችን ጨቁኗል የሚል አተያይ በሚኖርበት ወቅት እንደሆነ Ramachandran and Rauh (2016) ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ አንጻር የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለትምህርት መስጫነት የመጠቀም ተነሳሽነት አንዳንድ ጊዜ ተጨቁነን ቆይተናል በሚሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ከጭቆናቸው የሚላቀቁበት ፖለቲካዊ መሳሪያ አድርገው ያስቡታል፡፡ የቃለመጠይቁ ተሳታፊ ርእሳነመ ምህራን በአጠቃላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ሂደት ላይ የተመለከቷቸው ተግዳሮቶች ምን ምን እንደሆኑ እንዲገልጹ ተጠይቀው ከፖለቲካ ጋር በተገናኘ የሚከተለውን ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ መምህራን በቂ የሆነ ስልጠና ሳያገኙ፤ የማስተማሪያ መጽሀፍት በቋንቋው ተዘጋጅተው ለተማሪዎች በበቂ ሁኔታ ሳይዳረሱና በቋንቋው የተዘጋጁ አጋዥ መጽሀፍት በሌሉበት በቋንቋው ትምህርት እንዲሰጥ መደረጉ፤ በሌላ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ቋንቋውን ሳይችሉ በቋንቋው እንዲማሩ መደረጉ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ችግር ፈጥሯል ብለዋል፡፡

አንድ ሌላ የቃለመጠይቁ ተሳታፊ ርእሰመምህር ደግሞ እንዲህ ሲሉ አስተያየት ሰጥተዋል፡ በግልጽ ለመናገር ልጆቻችን አማርኛ ቋንቋ እንደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ከአንደኛ ክፍል ጀምረው ቢማሩና በሁለተኛ ቋንቋ ተግባቦታዊ ብቃት እንዳያዳብሩ ቢደረግ ጥሩ ነው፡፡ እስቲ 9ኛ ክፍል ላይ ለሁለተኛ ቋንቋ በመርሃ ትምህርት ደረጃ የተመደበውን ክፍለ ጊዜ ሂደሽ ተመልከቺ፡፡ በአንድ ክፍለ ጊዜ ሳምንታዊ ድልድል ቋንቋን እንዴት መማር ይቻላል? የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እንዲማሩ ሲደረግ ሁለተኛ

ቋንቋቸውን ከ5ኛ ክፍል እንዲጀምሩ እየተደረገ መቆየቱ የትምህርት ፖሊሲውን እና የፖለቲካውን ተጽእኖ መጠን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ በስርአተ ትምህርት ቀረጻ ላይ የተንጸባረቀ ፖለቲካዊ ገጽታ ያለው አካሄድ ተማሪዎችን ተፎካካሪ አያደርግም፡፡ ተማሪዎች ከትምህርት መጀመሪያ እድሜያቸው ጀምሮ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጎን ለጎን ሁለተኛ ቋንቋቸውን መማር ቢጀምሩ የተሻለ የሁለተኛ ቋንቋ ተጋልጦ እድል ይኖራቸው ነበር ሲሉ ተችተዋል፡፡

## 4.2.7 ከክፍል ምልከታዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ጥናት ተተኳሪ በማና ወረዳ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሰሞዶ ፣ ሳረዶ ፣ ቢሊዳ፣ ገሩኬ ጅማቴ፣ ቡጡሬ እና ቡሩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በክፍል ምልከታዎች የተደገፉ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በነሲብ በተመረጡ 2 /ሁለት/ የስድስተኛ መማሪያ ክፍሎች ለ2 /ሁለት/ ዙር ምልከታ በማካሄድ በ12 የምልከታ ዙሮች መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በጊዜ እጥረት ምክንያት ሁለት ሁለት ዙር የክፍል ምልከታዎች በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ የተቻለው ከ6ቱ የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በ3ቱ - ገሩኬ ጅማቴ፣ ሰሞዶና ሳረዶ ትምህርት ቤቶች ብቻ ነው፡፡ የመጀመሪያውን ዙር የክፍል ምልከታዎች በሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ማካሄድ የተቻለ ሲሆን፤ ሁለተኛውን ዙር የክፍል ምልከታ በቢሊዳ፣ ቡሩና ቡጡሬ ትምህርት ቤቶች ለማካሄድ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ከዚህ በታች ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ቀርቧል፡፡ ሁሉም የክፍል ምልከታዎች በተለይ በቃለመጠይቁ የተሳተፉ የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መምህራንን በመከተል የተከናወኑ ናቸው፡፡ ይህም መምህራኑ በቃለመጠይቅ መረጃ የሰጧቸውን አስተያየቶች በክፍል ውስጥ ከሚያካሂዷቸው ተግባራት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ለማጤን እንደሚረዳ ታሳቢ በማድረግ የተከናወነ ነው፡፡ የክፍል ምልከታ መቃኛ ነጥቦች (Observation Check-List) የክፍል ምልከታዎቹን ወጥነት ለመጠበቅ ረድቷል፡፡

### ምልከታ 1፡- ገሩኬ ጅማቴ

በገሩኬ ጅማቴ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያው የምልከታ ዙር በቀን 28/3/2013 ከ5፡10–5፡45 ሰአት የተካሄደ ሲሆን በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቹ ተደሳችነት፣ መምህሩ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት እንዲያካሂዱ የሚያደርጉት ጥረት፣ በቀረበው

ትምህርት ላይ ግብረ-መልስ በማቅረብ ትምህርቱን ለማስረጽ የሰጡት ትኩረት አጥጋቢ መሆናቸውን አጥኚዋ ተገንዝባለች፡፡

በሌላ በኩል፤ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያሳዩት ተሳትፎ፣ መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ አቅደውና አደራጅተው ማቅረባቸው፣ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል መምህሩ የሚያደርጉት ጥረት ተደራሽነት፣ ተማሪዎቹ በሚማሩት ይዘት ዙሪያ የእርስ በርስ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ እንዲያበለጽጉ የሚያደርጉት ግፊት ጉልህነት፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የትምህርቱ ማእከል አድርገው ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት አነቃቂነት፣ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚነት አጥጋቢ እንዳልሆኑ አጥኚዋ ተገንዝባለች፡ ከዚህም በተጨማሪ ከመማሪያ ክፍል ውጪ በትምህርት ቤቱ ቤተመጻህፍት በቂ የተጨማሪ ንባብ አጋዥ መጻህፍት ተሟልተው መገኘት ጉልህ ችግር የሚታይበትና የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር የሚረዱ የቤተመጻህፍት ስብስቦች አለመኖራቸውን አጥኚዋ ቃኝታለች፡፡

## ምልከታ 2፡- ሳረዶ

በሳረዶ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያው የምልከታ ዙር በቀን 9/3/2013 ከ9፡30–10፡00 ሰአት የተካሄደ ሲሆን፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቹ ተደሳችነት፣ መምህሩ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት እንዲያካሂዱ የሚያደርጉት ጥረት፣ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያሳዩት ተሳትፎ፣ ተማሪዎቹ በሚማሩት ይዘት ዙሪያ የእርስ በርስ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ እንዲያበለጽጉ የሚያደርጉት ግፊት ጉልህነት፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የትምህርቱ ማእከል አድርገው ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት አነቃቂነት አጥጋቢ መሆናቸውን አጥኚዋ ቃኝታለች፡፡

በሌላ በኩል፤ መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ አቅደውና አደራጅተው ማቅረባቸው፣ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል መምህሩ የሚያደርጉት ጥረት ተደራሽነት፣ በቀረበው ትምህርት ላይ ግብረ-መልስ በማቅረብ ትምህርቱን ለማስረጽ የሰጡት ትኩረት፣ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚነት በአጥጋቢ ሁኔታ ላይ እንደማይገኙ አጥኚዋ ቃኝታለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከመማሪያ ክፍል ውጪ በትምህርት ቤቱ ቤተመጻህፍት በቂ የተጨማሪ

ንባብ አጋዥ መጻህፍት ተሟልተው መገኘት ጉልህ ችግር የሚታይበትና የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር የሚረዱ የቤተመጻህፍት ስብስቦች አለመኖራቸውን አጥኚዋ ለመረዳት ችላለች፡፡

## ምልከታ 3፡- ቡጡሬ

በቡጡሬ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያው የምልከታ ዙር በቀን 7/3/2013 ከ4፡ 15–4፡50 ሰአት የተካሄደ ሲሆን፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቹ ተደሳችነት ተማሪ፣ ዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያሳዩት ተሳትፎ፣ መምህሩ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት እንዲያካሂዱ የሚያደርጉት ጥረት እና ተማሪዎቹ በሚማሩት ይዘት ዙሪያ የእርስ በርስ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ እንዲያበለጽጉ የሚያደርጉት ግፊት ጉልህነት በአጥጋቢነታቸው የታዩ ክንዋኔዎች ናቸው፡፡

በአንጻሩ መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ አቅደውና አደራጅተው ማቅረባቸው ፣ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል መምህሩ የሚያደርጉት ጥረት ተደራሽነት፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የትምህርቱ ማእከል አድርገው ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት አነቃቂነት፣ በቀረበው ትምህርት ላይ ግብረ-መልስ በማቅረብ ትምህርቱን ለማስረጽ የሰጡት ትኩረትና ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚነት በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ መሆናቸውን አጥኚዋ ተመልክታለች፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከመማሪያ ክፍል ውጪ በትምህርት ቤቱ ቤተመጻህፍት በቂ የተጨማሪ ንባብ አጋዥ መጻህፍት ተሟልተው አለመገኘት ጉልህ ችግር የሚታይበትና የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር የሚረዱ የቤተመጻህፍት ስብስቦች አለመኖራቸውን አጥኚዋ አጢናለች፡፡

## ምልከታ 4፡- ሰሞዶ

በሰሞዶ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያው የምልከታ ዙር በቀን 23/3/2013 ከ8፡ 30–9፡10 ሰአት የተካሄደ ሲሆን፤ በዚህ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርት አተገባበር በአንጻራዊ የተሻለ መሆኑን አጥኚዋ ተመልክታለች፡፡ በዚሁ መሰረት በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቹ ተደሳችነት፣ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያሳዩት ተሳትፎ፣መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ አቅደውና

አደራጅተው ማቅረባቸው፣ መምህሩ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት እንዲያካሂዱ የሚያደርጉት ጥረት፣ ተማሪዎቹ በሚማሩት ይዘት ዙሪያ የእርስ በርስ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ እንዲያበለጽጉ የሚያደርጉት ግፊት ጉልህነት፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የትምህርቱ ማእከል አድርገው ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት አነቃቂነት እና በቀረበው ትምህርት ላይ ግብረ-መልስ በማቅረብ ትምህርቱን ለማስረጽ የሰጡት ትኩረት አጥጋቢ መሆናቸውን አጥኚዋ ተመልክታለች፡፡

በሌላ በኩል ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል መምህሩ የሚያደርጉት ጥረት ተደራሽነት እና ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ክንውኖች መሆናቸውን አጢናለች፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከመማሪያ ክፍል ውጪ በትምህርት ቤቱ ቤተመጻህፍት በቂ የተጨማሪ ንባብ አጋዥ መጻህፍት ተሟልተው መገኘት ጉልህ ችግር የሚታይበትና የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር የሚረዱ በቂ የቤተመጻህፍት ስብስቦች አለመኖራቸውን አጥኚዋ ተመልክታለች፡፡

## ምልከታ 5፡- ቢሊዳ

በቢሊዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያው የምልከታ ዙር በቀን 6/4/2013 ከ3፡10–3፡50 ሰአት የተካሄደ ሲሆን፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቹ ተደሳችነት፣ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያሳዩት ተሳትፎ፣ መምህሩ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት እንዲያካሂዱ የሚያደርጉት ጥረት፣ ተማሪዎቹ በሚማሩት ይዘት ዙሪያ የእርስ በርስ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ እንዲያበለጽጉ የሚያደርጉት ግፊት ጉልህነት እና በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የትምህርቱ ማእከል አድርገው ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት አነቃቂነት አጥጋቢ ሆነው አግኝታቸዋለች፡፡

በሌላ በኩል መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ አቅደውና አደራጅተው ማቅረባቸው፣ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል የሚያደርጉት ጥረት ተደራሽነት፣ በቀረበው ትምህርት ላይ ግብረ-መልስ በማቅረብ ትምህርቱን ለማስረጽ የሰጡት ትኩረት እና ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ክንውኖች መሆናቸውን አጥኚዋ ለማጤን ችላለች፡፡

ከዚህም ጋር ከመማሪያ ክፍል ውጪ በትምህርት ቤቱ ቤተመጻህፍት በቂ የተጨማሪ ንባብ አጋዥ መጻህፍት ተሟልተው መገኘት ጉልህ ችግር የሚታይበትና የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር የሚረዱ የቤተመጻህፍት ስብስቦች አለመኖራቸውን አጥኚዋ ቃኝታለች፡፡

## ምልከታ 6፡- ቡሩ

በቡሩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያው የምልከታ ዙር በቀን 3/4/2013 ከ10፡ 00–10፡40 ሰአት የተካሄደ ሲሆን፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቹ ተደሳችነት፣ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያሳዩት ተሳትፎ፣ መምህሩ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት እንዲያካሂዱ የሚያደርጉት ጥረት እና በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የትምህርቱ ማእከል አድርገው ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት አነቃቂነት አጥኚዋ አጥጋቢ ሆነው ያገኘቻቸው ክንዋኔዎች ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ አቅደውና አደራጅተው ማቅረባቸው፣ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል የሚያደርጉት ጥረት ተደራሽነት፣ ተማሪዎቹ በሚማሩት ይዘት ዙሪያ የእርስ በርስ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ እንዲያበለጽጉ የሚያደርጉት ግፊት ጉልህነት፣ በቀረበው ትምህርት ላይ ግብረ-መልስ በማቅረብ ትምህርቱን ለማስረጽ የሰጡት ትኩረት እና ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚነት አጥጋቢ እንዳልሆኑ አጥኚዋ ተመልክታለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከመማሪያ ክፍል ውጪ በትምህርት ቤቱ ቤተመጻህፍት በቂ የተጨማሪ ንባብ አጋዥ መጻህፍት ተሟልተው መገኘት ጉልህ ችግር የሚታይበትና የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር የሚረዱ የቤተመጻህፍት ስብስቦች አለመኖራቸውንም አጥኚዋ የተገነዘበችው ጉዳይ ነው፡፡

## ምልከታ 7፡- ገሩኬ ጅማቴ (ሁለተኛ ዙር)

በገሩኬ ጅማቴ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለተኛው ዙር ምልከታ በቀን 3/5/2013 ከ7፡ 05–7፡40 ሰአት የተካሄደ ሲሆን፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቹ ተደሳችነት፣ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያሳዩት ተሳትፎ፣ መምህሩ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት እንዲያካሂዱ የሚያደርጉት

ጥረት፣ ተማሪዎቹ በሚማሩት ይዘት ዙሪያ የእርስ በርስ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ እንዲያበለጽጉ የሚያደርጉት ግፊት ጉልህነት፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የትምህርቱ ማእከል አድርገው ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት አነቃቂነት እና በቀረበው ትምህርት ላይ ግብረ-መልስ በማቅረብ ትምህርቱን ለማስረጽ የሰጡት ትኩረት አጥጋቢ መሆናቸውን አጥኚዋ ተመልክታለች፡፡

ይሁን እንጂ በዚህም ዙር ምልከታ መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ አቅደውና አደራጅተው አላቀረቡም፡፡ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል የሚያደርጉት ጥረትም ተደራሽነት የሌለው ነው፡፡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚነት አጥጋቢ አይደለም፡፡

## ምልከታ 8፡- ሳረዶ (ሁለተኛ ዙር)

በሳረዶ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለተኛው ዙር ምልከታ በቀን 5/5/2013 ከ3፡20–4፡00 ሰአት የተካሄደ ሲሆን፤ የሁለተኛው ዙር የምልከታ ውጤት ከመጀመሪያው ዙር ምልከታ ውጤት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት  በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎቹ ተደሳችነት ይታይባቸዋል፡፡ መምህሩ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት እንዲያካሂዱ የሚያደርጉት ጥረት አጥጋቢ ነበር፡፡ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያሳዩት ተሳትፎ የተበረታታ ነበር፡ ተማሪዎቹ በሚማሩት ይዘት ዙሪያ የእርስ በርስ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ እንዲያበለጽጉ የሚያደርጉት ግፊት ጉልህነት ታይቶበታል፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የትምህርቱ ማእከል አድርገው ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት አነቃቂነት አጥጋቢ መሆኑንም አጥኚዋ ቃኝታለች፡፡

ነገር ግን መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ አቅደውና አደራጅተው አለማቅረባቸው፣ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል መምህሩ የሚያደርጉት ጥረት ተደራሽነት ያልነበረው በቀረበው ትምህርት ላይ ግብረ-መልስ በማቅረብ ትምህርቱን ለማስረጽ የሰጡት ትኩረት አለመኖሩ፣ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚነት በአጥጋቢ ሁኔታ ላይ እንደማይገኙ አጥኚዋ በድጋሚ ቃኝታለች፡፡

## ምልከታ 9፡- ሰሞዶ (ሁለተኛ ዙር)

በሰሞዶ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለተኛው ዙር ምልከታ በቀን 13/5/2013 ከ9፡00–9፡35 ሰአት የተካሄደ ሲሆን፤ በዚህ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርት አተገባበር በአንጻራዊ ከሌሎቹ የተጎበኙ ትምህርት ቤቶች የተሻለ መሆኑን አጥኚዋ በድጋሚ ቃኝታለች፡፡ በዚሁ መሰረት በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቹ ተደሳችነት፣ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያሳዩት ተሳትፎ፣ መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ አቅደውና አደራጅተው ማቅረባቸው፣ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት እንዲያካሂዱ የሚያደርጉት ጥረት፣ ተማሪዎቹ በሚማሩት ይዘት ዙሪያ የእርስ በርስ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ እንዲያበለጽጉ የሚያደርጉት ግፊት ጉልህነት፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን ማእከል አድርገው ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት አነቃቂነት እና በቀረበው ትምህርት ላይ ግብረ-መልስ በማቅረብ ትምህርቱን ለማስረጽ የሰጡት ትኩረት አጥጋቢ መሆናቸው የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መምህሩን ከፍ ያለ የማስተማር ተነሳሽነት የሚያመለክት መሆኑን አጥኚዋ ተገንዝባለች፡፡

በሌላ በኩል ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል መምህሩ የሚያደርጉት ጥረት ተደራሽነት እና ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ክንውኖች መሆናቸውን አጥኚዋ ገምግማለች፡፡

## 4.2.7.1 የክፍል ምልከታ ውጤቶች ማብራሪያና ማጠቃለያ

በምልከታ ከተገኙት መረጃዎች ማጤን እንደተቻለው አንዳንዶቹ የአንደኛ ደረጃ መምህራን ከልማዳዊው የማስተማር ዘዴ ያልተላቀቁና ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴን የሚተገብሩ እንዳልሆኑ አጥኚዋ ተገንዝባለች፡፡ በዚሁ መሰረት ምንም እንኳን በተጎበኙት መማሪያ ክፍሎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቹ ተደሳችነት እና ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያሳዩት ተሳትፎ በአብዛኛው አበረታችነት የሚታይባቸው ሆነው ቢስተዋሉም በመምህራኑ የማስተማር ዘዴ አዋጭነት ላይ የተመሰረቱ ውጤቶች ሳይሆኑ በሚያውቁት የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማራቸው በፈጠረው የመማር መነቃቃት የታዩ ክስተቶች መሆናቸውን አጥኚዋ ተገንዝባለች፡፡

ይህም ከተጎበኙት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንዳንዶቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የትምህርቱ ማእከል አድርገው ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት አነቃቂነት ገድቦታል፡፡

የምልከታ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ አጥኚዋ እንደተረዳችው በተጎበኙት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መምህራኑ ሙሉ በሙሉ ለማለት ይቻላል ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት እንዲያካሂዱ የሚያደርጉት ጥረት በጉልህ የሚስተዋል ነው፡፡ ይህም የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መምህራኑ ራሳቸው አፍ በፈቱበት ቋንቋ የሚያስተምሩና ምናልባትም በሚገባ አጣርተው የሚያውቁት ቋንቋ ይኸው በመሆኑ የተፈጠረ የተግባቦት ዝንባሌ መሆኑን አጥኚዋ ተረድታለች፡፡ ይህም መምህራኑ በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ማስተማራቸው በቋንቋው ለማስተማር ካላቸው አዎንታዊ አመለካከት እና/ወይም ተነሳሽነት ጋር የሚገናዘብ ነው፡፡

በሌላም በኩል ተማሪዎቹ በሚማሩት ይዘት ዙሪያ የእርስ በርስ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ እንዲያበለጽጉ የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መምህራኑ የሚያደርጉት ግፊት ጉልህነት ብሎም በቀረቡት የትምህርት ይዘቶች ላይ ያተኮሩ የግብረ-መልስ ስልቶችን በመተግበር ትምህርቱን ማስረጽ በከፊሎቹ የተጎበኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ገደብ ያጠላባቸው፣ ነገር ግን በጣም አስፈላጊ ተግባራት ናቸው፡፡ ይህም መምህራኑ ስለ ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ያሏቸው ግንዛቤዎች ውሱንነት የመነጨ ችግር እንደሆነ አጥኚዋ ተገንዝባለች፡፡ አስቀድመን በቃለመጠይቅ በተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ወቅት እንደተመለከትነው፣ መምህራኑን ዘመኑ ከደረሰባቸው አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ለማስተዋወቅ የሚረዱ የተሃድሶ መርሃ ግብሮች ዎርክሾፖች፣ ሴሚናሮች፣ ወዘተ-- የተሰጠው ትኩረት አለመኖር ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ችግር እንደሆነ የአጥኚዋ እምነት ነው፡፡ ከስልጠና እና ተሃድሶ መርሃ ግብሮች አለመጎልበት ጋር የሚገናኙና በሁሉም በተጎበኙት አንደኛ ደረጃ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደቶች የተንጸባረቁ ጉልህ ችግሮች መካከል ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል መምህሩ የሚያደርጉት ጥረት ተደራሽነት አለመኖር ቁልፍ ችግር ነው፡

ምንም እንኳን በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቹ ተደሳችነት በሚገባ በሚያውቁት ቋንቋ የመማራቸው ነጸብራቅ መሆኑ ባይካድም፣ በቋንቋቸው ስለሚማሩ ብቻ በመማሪያ አውዶቹ ችግሮች አያጋጥሟቸውም ማለት

አይቻልም፡፡ አስቀድመን በተማሪዎቹ ግላዊ መረጃ እና በቃለመጠይቅ መረጃ ትንተናዎች ወቅት ለመቃኘት እንደሞከርነው ከመናገርና ከማዳመጥ ክሂሎች ብቃታቸው ይልቅ በቅደም ተከተል የመጻፍ እና የማንበብ ክሂሎች የብዙ ተማሪዎች ችግሮች ናቸው፡፡ ከሁሉም በላይ የመጻፍ ክሂል ለአብዛኞቹ ተማሪዎች ውስብስብ ክሂል ነው፡፡ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል መምህራኑ የሚያደርጉት ጥረት ተደራሽነት ቁልፍ ችግር የሆነውም በዚህ የተነሳ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቹን የመረዳት ችግሮች ለማቃለል የሚረዱ ብልሃቶችን በሚገባ መታጠቅ ይኖርባቸዋል፡፡

ይህም በስነዘዴ ስልጠናና በአጫጭር የተሃድሶ መርሃግብሮች የመምህራኑን የማስተማር አቅም ማጎልበትን የግድ ይላል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራኑ በአብዛኛው የሚያስተምሩትን ትምህርት በሚገባ አቅደውና አደራጅተው ማቅረባቸው የብዙ ተማሪዎች ችግሮች የሆኑትን የመጻፍ እና የማንበብ ክሂሎች ለማቃለልና ተማሪዎቹን የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋንኛ አካል ለማድረግ የሚረዳ ቢሆንም በምልከታ የተደገፈው የመምህራኑ ተሞክሮ ግን ይህን በጉልህ የሚያስገነዝብ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል በጣም አሳሳቢ የሆነው የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዶቹ ችግር ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ  ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ በተጎበኙት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰጧቸውን በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ተግባራትና መልመጃዎች መምህራኑ ከነምሳሌያቸው በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፈው ማቅረብ አይጠበቅባቸውም ነበር፡፡ ነገር ግን በተጎበኙት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በየመማሪያ ክፍሉ ዝቅተኛ 22 ከፍተኛ 29 ተማሪዎች ሲማሩ የነበሩ ቢሆንም የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይዘው የተገኙ በአማካይ 4 ወይም 5 ተማሪዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ይህም ቀደም ሲል ከመምህራኑና ርእሰመምህራኑ ጋር በተደረጉ ቃለመጠይቆች ከተተነተኑት የትምህርት ቁሳቁስ ተግዳሮት መረጃዎች ጋር የሚዛመድና የመማሪያ መጻህፍት እጥረት ችግርን በተጨባጭ የሚያመለክት ክስተት ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በተጎበኙት በሁሉም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተደራጁ ቤተመጻህፍት አለመኖርም የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዶቹ አሳሳቢ ችግር ነው፡፡ ይህ የምልከታ መረጃም ቀደም ሲል ከመምህራንና ርእሰመምህራን ተሰብስቦ

ከተተነተነው የቃለመጠይቅ መረጃ ጋር የሚደጋገፍና የማገናዘቢያ፣ የተጨማሪ ንባብ አጋዥ መጻህፍትና የአፍ መፍቻ ቋንቋ መዝገበ-ቃላት አለመኖርን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የቤተመጻህፍት ስብስቦች አለመኖራቸውም በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶችን በጉልህ ያሳያል፡፡

## 4.3 በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ የሚታዩ የመማር ማስተማር ሂደት ችግሮች መንስኤ ምክንያቶች

በመቀጠል በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ ዙሪያ ለሚስተዋሉ አበይት ችግሮች መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ምክንያቶችን ለማወቅ ለጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች መምህራን፣ ርእሰመምህራንና የወመህ ተወካዮች ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል፡፡ የጥናቱ መረጃ አቀባዮች በአብዛኛው የሚስማሙባቸው ጉዳዮችን ጠቅለል በማድረግ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 4.3.1 ከመምህራን አሰራር ጋር የተገናኙ ተግዳሮቶች መንስኤዎች

እንደ መምህራኑ፣ ርእሳነመምህራኑና የወመህ ተሳታፊዎች ጥቆማዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አተገባበር ዙሪያ የሚስተዋሉ ዋንኛ ተግዳሮቶች መንስኤዎች፡-

- የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ለማጎልበት የሚረዱ የተሃድሶ መርሃ-ግብሮችን አለመቀየስና አለመተግበር
- የመምህራን የልምድ ልውውጥና እርስ በርስ የመማማሪያ መድረኮች አለመጎልበትና ጠንካራ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አበረታች ተሞክሮዎችን ለማስፋፋት የሚደረግ ሙከራ አለመለመድ
- መምህራንን በሙያቸው እንዲበረታቱ የሚያደርግ የሞራልና የቁሳዊ /ማቴሪያል/ ማበረታቻ ስልት ጨርሶ አለመኖር
- ጥቂት ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የተገናኙ የስልጠና እና/ወይም ተሃድሶ እንዲሁም የሙያ ማሻሻያ ኮርሶች እድሎች ሲገኙ የወረዳ የትምህርቱ ስራ ሃላፊዎች በቀጥታ ለሚመለከተው መምህር እድሉን ከመስጠት ይልቅ በቅርበት፣ በዝምድና ፣ በጓደኝነት ላይ በተመሰረተ መልኩ ለሌላ ለማይመለከተው ሰው አሳልፈው በመስጠት የሚያካሂዱት አድሎ ለስራ ተነሳሽነት መላላት ያለው አሉታዊ ድርሻ፣

- በማትጊያ ስልቶችና ምቹ የስራ አካባቢ አለመፈጠር ወይም ጨርሶ አለመኖር የተነሳ የመምህራን አልፎ አልፎ ስራ መልቀቅ /ፍልሰት/፣

- በትምህርት ግብአቶች (የመምህር መምሪያ ፣ ማገናዘቢያ መጻህፍት…) አለመሟላት ጋር ተያይዞ የመምህራን በበቂ የማስተማር ዝግጅት አለመደገፍ
- በትምህርት ቤቶች ለመምህራን የሚሆኑ የመዝናኛ አገልግሎቶች፣ የትምህርታዊ መረጃ ድጋፍ ምንጮች ጨርሶ አለመኖር፤

- መምህራን በአካባቢያቸው ባሉ ግብአቶች ላይ ተመርኩዘው የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያ ለማዘጋጀት የሚያስችሏቸው ብልሃቶች በስልጠና አለመደገፍና አለመለመድ ፤ ፍላጎት ማጣት፤

ከመምህራን ሙያዊ ክንዋኔ ጋር በቀጥታ የተያያዙና የማስተማር ተነሳሽነትና ፍላጎትን የሚያጓድሉ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውጤታማነት ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽእኖ የሚያሳድሩ መንስኤዎች መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 4.3.2 ከተማሪዎች ባህሪ ጋር የተገናኙ ችግሮች መንስኤዎች

በተጎበኙት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከመምህራኑና ከርእሰ መምህራኑ ጋር በተካሄደው ቃለመጠይቅ መሰረት ከተማሪዎች ባህሪ ጋር የተገናኙ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የማደናቀፍ አዝማሚያ ያላቸው መንስኤዎች ደግሞ ከዚህ በታች ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

- የአንዳንድ ተማሪዎች ችላ ባይነት /የምማረው በአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ስለሆነ ትምህርቱ አይከብደኝም ከሚል የተሳሳተ ማጠቃለያ በመነሳት ለሚማሯቸው ትምህርቶች ተገቢ ትኩረት አለመስጠት

- የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ሚናና ጠቀሜታን የሚያውቁና አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ቢሆኑም፤በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ ያላቸው ተነሳሽነትና የክፍል ተሳትፎ ገደቦች የሚታዩባቸውና በምክርም መታገዝ አለመቻላቸው

- በቁጥር የሚበዙ ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ስለ ማንበብና መጻፍ መሰረታዊ ክሂሎች (literacy skills) ክትትልና ድጋፍ ሳያገኙ የሚማሩ መሆናቸው፤

- በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ የብዙ ተማሪዎች ተነሳሽነትና ንቁ ተሳትፎ በመቀዛቀዙ ምክንያት መምህራን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱን ተማሪ ተኮር ከማድረግ ይልቅ በአብዛኛው በነባሩ መምህር መራሽ ዘዴ ለማስተማር መገደድ፤

- ከቡና ምርት መድረስ ጋር ተያይዞ በርከት ያሉ ተማሪዎች ለወራት ከትምህርት ቤት መቅረትና በፈተና ወቅት መገኘት፤

- በርካታ ተማሪዎች መብቶችን እንጂ ግዴታዎችን ጠንቅቆ አለመገንዘብ፣ በትምህርትና የፖለቲካ አመራሮች በኩል በአብዛኛው የሚሰበከው የተማሪዎች መብት እንጂ ግዴታ አለመሆኑ፤

- የሚሰጡ ልዩ ልዩ ክንውኖችን በራስ ተነሳሽነት አውቆ ከመገኘት ይልቅ ከሌሎች ተማሪዎች ገልብጦ ማቅረብ፣ የቤት ስራና ፈተና መኮረጅ ባህል መሆኑ፤

- ተማሪዎችን ለመቆጣጠር፣ የቤት ስራ የማይሰሩትን ለመገሰጽና ወደ ተገቢ የመማር ባህሪ እንዲመለሱ ለማድረግ የሚያስችል ምቹና ጠንካራ የተማሪ--ወላጅ--ትምህርት ቤት ግንኙነት አለመኖር፤

- በተለምዶ ከ1ኛ–4ኛ ክፍል መድገም ስለሌለ ተማሪዎች ተገቢ የክፍል ማለፊያ መስፈርቶችን ሳያሟሉ አምስተኛ ክፍል የሚደርሱበት ሁኔታ መኖሩ በተማሪዎች የአፍ መፍቻ እውቀትና ክህሎት ጨባጭነት ልምድ ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተጽእኖ፤

- ወላጆች የልጆቻቸውን ከመማር ባህሪ ጋር የተያያዙ ስህተቶች ላይ ለመምከር በመምህራን ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ሲጠሩ አለመምጣት፤ የሚመጡትም የልጆቻቸውን ስህተት ተቀብለው ለማረም ከመሞከር ይልቅ ከመምህራን ጋር ሰጣ ገባ መፍጠር

በርካታ የጥናቱ የቃለመጠይቅ መረጃ አቀባዮች የሚስማሙባቸው ከተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ተሳትፎ ጋር የተያያዙ አሉታዊ ባህሪያትና ልምዶች የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን በተገቢ ሁኔታ ለማራመድ የሚያጋጥሙ መንስኤዎች እንደሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡

### 4.3.3. ከሌሎች የትምህርት ባለድርሻዎች ጋር የተገናኙ ችግሮች መንስኤዎች

ከጥናቱ ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መረጃ አቀባዮች ጋር በተካሄዱ ቃለመጠይቆች የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ሌሎች የትምህርቱ ስራ ባለድርሻዎችም በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትም ህርት ትግበራ ዙሪያ ለሚስተዋሉ አበይት ችግሮች የየራሳቸው አሉታዊ ድርሻ እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ እነዚህ ባለድርሻ አካላት የትምህርቱን ስራ የሚመሩ በየደረጃው ያሉ የትምህርት አመራር ኃላፊዎች ፣ የተማሪዎች ወላጆች ድጋፍ፣ ሰጪ አካላትና የየአካባቢዎቹ ማህበረሰቦች ናቸው፡፡በዚሁ መሰረት የትምህርቱን ስራ የሚመሩ የወረዳ ትምህርት ቢሮ ሃላፊዎች መምህራንን በአግባቡ በመመደብ፣ የትምህርት ቁሳቁሶችን በትምህርት ቤቶች ፍላጎት ላይ ተመስርተው በወቅቱ ማሰራጨት፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ አውድ የሚከሰቱ ችግሮችን መከታተል፣ መገምገምና ምክረ-ሐሳቦችን ማንሸራሸር፣ መምህራን በስራቸው ለማበረታታትና ለማገዝ የሚያስችሉ ስልቶችን መቀየስና በስራ ላይ ማዋል፣ የልምድ ልውውጥ፣ የመልካም ተሞክሮና የመምህራን ሙያዊ ተሃድሶ ፕሮግራሞችን መቀየስ፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት አርአያነት ያላቸውን ተሞክሮዎች በመምረጥ እውቅና መስጠት ወዘተ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱን ለማጠናከርና መምህራንንም በስራቸው ለማበረታታት የሚረዱ እሳቤዎች እንደሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የወረዳ ትምህርት ቢሮ ሃላፊዎች የሰለጠነ የሰው ሃይል ምደባን በበቂ ጥናት ላይ ተመርኩዘው በየትምህርት ቤቱ እጥረት የሚታይባቸውን የትምህርት አይነቶች መምህራን ከመመደብ ይልቅ በግድ የለሽነት በየትምህርት ቤቱ ያለውን መምህር አልፎ አልፎ በተጨማሪ የሚልኩበት ሁኔታ አለ፡፡ በዚህ የተነሳ ብዙ ጊዜ በተወሰነ የትምህርት መስክ የሰለጠነውን መምህር በሌላ ባልሰለጠነበት የትምህርት መስክ እንዲያስተምር ይገደዳል፡፡ ይህም የተዛባ አሰራር በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራና የተማሪዎች ውጤታማነት ላይ ተጽእኖው በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡በሌላ በኩል የትምህርት ቁሳቁሶች መማሪያ መጻህፍት፣ የመምህሩ መምሪያ እጥረቶችን ለማቃለል የሚያስችሉ መፍትሂዎች በወቅቱ አይቀየሱም፡፡

ለምሳሌ፡- በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የአንድ አፍ መፍቻ ቋንቋ የትምህርት አይነት መማሪያ መጽሐፍ እና/ወይም የመምህሩ መምሪያ ክምችት ሲኖር በሌሎችትምህርት ቤቶች ግን አሳሳቢ የሆኑ እጥረቶች ያጋጥማሉ፡፡ ይህን የክምችትና እጥረት ችግር

ለማቃለል የሚረዳው በሕጋዊ ሰነድ የተደገፈ ልውውጥ ማካሄድ እንደሆነ በተለይ የቃለመጠይቅ መረጃ አቀባዮቹ ርእሳነመምህራን በአጽንኦት ይጠቁማሉ፡፡

እንደ አንዳንድ መምህራን ትችት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር የሚረዱ መምህራንን የማጠናከርያ ስልቶችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ከማካሄድ ይልቅ በቅርበት ፣ በዝምድናና በግል ግንኙነት ላይ በመመስረት የሚፈልጉትን ሰው መርጠው የሚልኩባቸው ወቅቶች አሉ፡፡ ለትምህርት ቤቶች በሚሰጡ የሙያ ማሻሻያ በጣም ውሱን የክረምት ኮርሶች የሚፈልጓቸውን ሰዎች መርጠው ይልካሉ፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ መምህር ሳይሆኑ ቢሮ ላይ ያሉ ሰዎችን የሚልኩበት ጊዜም አለ ይላሉ፡፡ እንደ መምህራኑና ርእሳነመምህራኑ የቃለመጠይቅ መረጃዎች በእነዚህና በሌሎችም ችግሮች የተነሳ በርካታ መምህራን በገጠር በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በመስራት ከመቆየት ይልቅ በግል ጥረት በትርፍ ጊዜና በተልእኮ ትምህርታቸውን በማሻሻል ወደ ሌላ ቦታ ይሄዳሉ፡፡ ምትክ ቶሎ ስለማይገኝ በተጓደሉ መምህራን ቦታ ከትምህርት አይነቱ ጋር የተያያዘ ስልጠና የሌላቸው መምህራን በተጨማሪ ክፍለ ጊዜ ወይም በሽግሽግ መመደብ ግድ ይላል ባይ ናቸው፡፡

አንድ የወመህ የቃለመጠይቁ ተሳታፊ፤ የወረዳ ትምህርት ቢሮ አካላት ትምህርት ቤቶች ሲከፈቱ አንዴ ብቅ ብለው ጎብኝተው ሲያበቁ ከዚያ በኋላ ትምህርት ቤት ቅጽር ግቢ ውስጥ አናገኛቸውም፡፡ በተለያዩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጉዳዮች የማህበረሰባችንን ግንዛቤ ለማስፋት የሚረዱ ስልቶችን መቀየስና መተግበር አብረን ልንወጣው የሚገባን ስራ ነበር፡፡ እየተደጋገፍን እየሰራን እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ በሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ዘንድ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር የሚረዳ ትብብር ትኩረት የተሰጠው አይደለም ሲሉ ተችተዋል፡፡

ሌላኛው የወመህ መረጃ አቀባይ በሰጡት አስተያየት፤ የወላጅ መምህር ህብረት ውስጥ ተሳትፎ ሳደርግ ቆይቻለሁ፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ላይ ጉልህ የሆነ የአመለካከት ችግር በማህበረሰባችን ዘንድ እንደሌለ አውቃለሁ፡፡ ይሁንና በወላጆች በኩል ወደ ትምህርት ቤት መጥተው ስለልጆቻቸው የትምህርት ጉዳይ መከታተል እምብዛም አይፈልጉም፡፡ ትምህርት ቤቱ የማህበረሰቡ መሆኑን ብዙ ወላጆች አይረዱትም፡፡ የትምህርቱ ስራ የመንግስትና የመምህራን ድርሻ ብቻ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ ሌላው ችግር በቂ የሆኑ የመምህራን መኖሪያ ቤቶች በትምህርት ቤት አካባቢ ባለመዘጋጀቱ ፣ ትምህርት ቤቶቹ ለጅማ ያለውን ቅርበት በመጠቀም ብዙ መምህራን በየቀኑ ከጅማ

እየተመላለሱ ያስተምራሉ፡፡ ይህም ለትምህርት ክፍለ ጊዜያት ብክነትና መምህራን ተረጋግተው ስራቸውን እንዳይሰሩ፣ በስራቸው ደስተኛነት እንዲያጡ የራሱ አሉታዊ አስተዋጽኦ እንዳደረገ አውቃለሁ ሲሉ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

እንደ ርእሰመመህራን መረጃ አቀባዮች ጥቆማ፤ ወላጆች የልጆቻቸውን የመማር ሂደት የቅርብ አጋሮች እንደሆኑ ይታሰባል፡፡ ነገር ግን በተጨባጭ እንደሚታየው ይህን የድጋፍ መንገድ የሚከተሉ በጣም ጥቂት የተማሩ ወላጆች ወይም በቤት ውስጥ የተማሩ ዘመዶች ያሏቸው ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡ ካልተማረ ቤተሰብ የሚመጡ ተማሪዎች በአመዛኙ ስለ ትምህርት ጥቅም የሚያገኙት መረጃ በትምህርት ቤት የተወሰነ ነው፡፡ በእርግጥ በትምህርት ቤት ደረጃ በተለያዩ አጋጣሚዎች ስለ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲያገኙ እናደርጋለን፡፡ ሆኖም ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚቆዩት ለአራት ሰአታት ያህል ብቻ ነው፡፡ በቤት በሚቆዩባቸው ሰፊ ጊዜያት በሚገባ የሚታገዙበት ሁኔታ ቢኖርና በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የማንበብ፣ የመጻፍ ልምምዶች እንዲያካሂዱ ግፊት ቢደረግ የተሻለ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ ችግሩ ይህን ጥረት በዘላቂ ሁኔታ የሚያካሂዱ ወላጆች የተማሩት ብቻና በጣም ጥቂት ናቸው ብለዋል፡፡

የወላጆችና የገጠሩ ማህበረሰብ ጠንካራ ተሳትፎ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማሩ ሂደት እንደምሰሶ የሚቆጠር ቢሆንም የወላጆችና ማህበረሰቡ ትብብርና ድጋፍ በዳር ቆሞ ተመልካችነት የተገደበ ነው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን እንደግፋለን የሚሉ ባለሃብቶችና አንዳንድ የሲቪክ ድርጅቶችም በወሬ እንጅ በተግባር የሚገለጽ ድጋፍ አያደርጉም፡፡ በየጊዜው ይህን ያህል መጽሀፍ ለትምህርት ቤቶች ገቢ እናደርጋለን ሲሉ በአንዳንድ ህዝባዊ መድረኮች ቃል ሲገቡ ይስተዋሉ እንጅ በተግባር የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድን ችግሮች ለመለወጥ የሚረዳ አስተዋጽኦ አይታይም በማለት ገልጸዋል፡፡
አብዛኛውን ጊዜ በመንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚያደርጉ ድጋፎችና ክትትሎች ለይስሙላና ለጊዜው እንጅ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የሚደረጉ አይደሉም፡፡ ለሪፖርት ሲባል ብቻ እንጅ ከልብ በመነጨ ተነሳሽነት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱን አወድ ለዘለቄታው ለማጠናከር የሚደረጉ እንዳልሆኑ መረጃ አቀባዮቹ የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡

አያይዘውም ለተማሪዎች መማሪያ መጻህፍት ዝግጅት ተመጣጣኝ ትኩረት አለመሰጠቱ ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ መማሪያ መጻህፍት የተካተቱ ተግባራትና መልመጃዎች የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂል ደረጃ በደረጃ ማሳደግን ታሳቢ አድርገው አለመዘጋጀታቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱን ለተማሪዎች ችሎታ አዳጋች ከማድረግ ጎን ለጎን፤ በተለያዩ ጊዜያት የታተሙ መማሪያ መጻህፍትን በየጊዜው ከአገልግሎት ውጭ መደረጋቸው መስተዋሉና ይህም ለመንግስት ሃብት ኪሳራ፣ ለትምህርት ቤቶች የመማሪያ መጻህፍትና የመምህር መምሪያ እጥረት መጋለጥ የራሱ አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ጠቁመዋል፡፡

### 4.3.4 ኢኮኖሚያዊ መንስኤ ምክንያቶች

ኢኮኖሚ አብዛኛውን ጊዜ ለታዳጊ ሀገሮች የትምህርት ስራ አለመጎልበት ቁልፍ መንስኤ ነው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋው መማሪያ አውድ ግብአቶች /ሪሶውርስ/ እጥረት የመማር ማስተማሩ ሂደት ቁልፍ ችግሮች መንስኤ ምክንያቶች መሆናቸውን ተሳታፊዎቹ በአጽንኦት ያመላከቱ ሲሆን፤ ተግዳሮቶቹ በዋንኛነት ከበጀት /ኢኮኖሚ/ ጋር የተያያዙ ስለመሆናቸው ይስማማሉ፡፡ ከዚህም ጋር የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመማሪያ መጻህፍትና በመምህሩ መምሪያዎች ችግሮች እየታዩ በዞንና በወረዳ ትምህርት ቢሮዎች መጋዘኖች የስርጭት ትኩረት ተነፍጓቸው ተከማችተው የተቀመጡ ግብአቶች እንዳሉ አንዳንድ ርእሰመምህራን ይጠቁማሉ፡፡

ከመምህራንና ርእስመምህራን በቃለመጠይቅ እንዲሁም በምልከታ ጭምር ከተሰበሰቡት ልዩ ልዩ መረጃዎች መገንዘብ እንደተቻለው በተጎበኙት ትምህርት ቤቶች በአብዛኛዎቹ ማለት ይቻላል የተደራጁ ቤተመጻህፍት እጥረት ፣ እንዲሁም የተለያዩ አጋዥና ማገናዘቢያ መጻህፍት አለመኖር ጉልህ ችግር ነው፡፡ በተጎበኙት አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች ከቤተመጻህፍት አለመደራጀት ጋር በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ መጻህፍት ስብስብ የትምህርት መርጃዎች አለመኖር ትልቅ ችግር ሲሆን፤ በተጎበኙት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁሉ በታላሚው ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት፣ የማገናዘቢያ መጻህፍት፣ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የተጻፉ ልቦለድ መጻህፍት፣ የተረት መጻህፍት፣ የእንግሊዝኛ፣ አማርኛና አፋን ኦሮሞ ቋንቋን በአንድነት የሚያቀርቡ መዝገበ-ቃላት ጨርሶ አለመኖራቸውን በምልከታ ጭምር ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነዚህ የቤተመጻህፍት ክምችቶች የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ተማሪዎችን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ለማሟላት በሚያስችል መልኩ ለተማሪዎች ተደራሽ ማድረግ ተገቢ ነበር፡፡

ቤተመጻህፍትን በማቋቋም በአፋን ኦሮሞ እና ሌሎችም ቋንቋዎች የማገናዘቢያና አጋዥ መጻህፍት እንዲሁም የተለያዩ አገልግሎቶች ያሏቸው መዝገበቃላትና ሌሎች ተነባቢ ጽሁፎችን በቤተመጻህፍት ለማኖርና አገልግሎት እንዲያበረክቱ ለማድረግ ካለው ከገበያ በግዢ የማሟላት የኢኮኖሚ አቅም ውስንነቶች ጎን መነሻ የሚሆን የማህበረሰብ ንቅናቄም የለም፡፡ ከቤተመጻህፍት ማቋቋምና ክምችቶች ማሰባሰብ ጋር ተያይዞ ሊጤን የሚገባው ጉዳይም ስብስቦቹ የተማሪዎቹን የተለያየ የክፍል ደረጃና የማንበብ ችሎታ ታሳቢ ያደረጉና በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የማንበብ ፍላጎትን ለማሳደግ የሚረዱ እንዲሆኑ ትኩረት መደረግ የነበረበት ቢሆንም ለዚህ የሚረዳ ኢኮኖሚና የፖለቲካ ቁርጠኝነት ማነሱ እንደ መንስኤ ምክንያት የሚቆጠር ነው፡፡

እንደ ርእሰ መምህራኑ መረጃ አቀባዮች ስምምነት ከመምህራን ፍልሰትና በገጠር ትምህርት ቤቶች የማስተማር ፍላጎት መቀዛቀዝ፣ የቋንቋው ተናጋሪ በመሆናቸው ብቻ የአፍ መፍቻ ቋንቋንም ሆነ ሌሎች የትምህርት አይነቶችን የሚያስተምሩ መምህራን መኖራቸው ፣እንዲሁም የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያሳልጡ በቂና ተደራሽ የትምህርት መሳሪያዎች እጥረት ተጽእኖዎች ከሁሉም የጎላ እንደሆነ በርካታ የጥናቱ መረጃ አቀባዮች የሚስማሙባቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ በተለይ በቤተመጻህፍት አፋን ኦሮሞ ቋንቋን የሚመለከቱ አጋዥ መጻህፍትን በግዢና በሌሎች መንገዶች እንዳናሰባስብ እንቅፋት የሆነብን ብለው ርእሳነመምህራኑ የጠቀሷቸው ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ሲጠቃለሉ፡-

1. ማገናዘቢያዎችን (references) ለማሟላት በቂ የበጀት አቅም አለመኖር፣
2. በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚያስፈልጉ በቂ የቤተመጻህፍት ስብስቦችን ለማሟላት በሚመለከታቸው የትምህርት ድጋፍ ሰጪና አጋር አካላት ዘንድ በቂ ትኩረትና ቁርጠኝነት አለመኖር፣
3. ለትምህርቱ ስራ ጠቀሜታ ያላቸውን ሐብቶች --መማሪያ መጻህፍት፣ የመምህር መምሪያዎች ፣ አጋዥና ማገናዘቢያ መጻህፍት እንዲሁም መዝገበቃላት -- በመምረጥ ፣ በማዘጋጀትና በአግባቡ በማሰራጨት ግልጽ የሆነ የባለቤትነት ተግባር አለመለመዱ፣
4. የየአካባቢውን ማህበረሰብ ንቅናቄ በማቀጣጠልና የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማቀናጀት አካባቢያዊ ወይም ባህላዊ ሐብቶችን (local resources) ተጠቅሞ ተነባቢ

ነገሮችን --ቃላዊ ልማዶችንና ስነቃሎችን፣ ባህላዊ ትርክቶችንና እውቀቶችን ወዘተ -- ለማዘጋጀት የሚረዱ ብልሃቶችን አለመጠቀም ወዘተ ምክንያቶችን ጠቅሰዋል፡፡

## 4.4 ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ወላጆች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት

በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ወላጆችና ማህበረሰቡ የያዙት አመለካከት ለመማር ማስተማሩ ሂደት ስኬታማነት ጉልህ ድርሻ እንዳለው ይታመናል፡፡ በመሆኑም በአጠቃላይ ለትምህርት ያለ ማህበራዊ አመለካከትና በተለይ ደግሞ አፍ መፍቻ ቋንቋን የመማሪያ ቋንቋ አድርጎ ከመጠቀም አኳያ የተያዘው አጠቃላይ አመለካከት ለተማሪዎቹ የመመር ፍላጎትና ተነሳሽነት ብሎም ለትምህርት ባለድርሻ አካላት የስራ ትብብርና ድጋፍ መነልበት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመለካከት ራሱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዱ ተግዳሮት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጉዳይ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመደገፍ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

*ሰንጠረዥ 8፡- የጥናቱ ተሳታፊዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ሰላላቸው አመለካከት የሰጧቸው ምላሾች*

| | ገላጮች /አመልካቾች/ (n=502-1) | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ በሚገባ በማውቀው ቋንቋ የሚሰጥ በመሆኑ የምማራቸውን ትምህርቶች ሁሉ በይበልጥ ለመረዳት [illegible] | 4.74 | .322 |
| 2 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማር ያለኝ አመለካከት አዎንታዊ ነው፡፡ | 4.69 | .407 |
| 3 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ለኔ የትምህርት ቤት ቆይታ አስደሳች ክንዋኔ ነው፡፡ | 4.57 | .521 |
| 4 | የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ ባህልን ለማወቅ፣ ሰብዕና ለመገንባትና ለስነልቦና እድገት ጠቅሞኛል፡፡ | 4. 44 | .445 |
| 5 | በትምህርት ቤት ቆይታዬ ከመምህራንና ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመግባባት ትኩረት እሰጣለሁ፡፡ | 4.37 | .550 |
| 6 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር በምኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ጥሩ የተግባቦት ችሎታ እንዳዳብር ረድቶኛል፡፡ | 4.28 | .557 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ለይቼ አውቃለሁ፡፡ | 4.15 | .545 |
| 8 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ እወዳለሁ፡፡ | 3.41 | .501 |
| 9 | ሁሉንም የትምህርት አይነቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማር አጥጋቢ ውጤት ለማምጣት እተጋለሁ፡፡ | 3.36 | .555 |
| 10 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ የምንማር ተማሪዎች በሌሎች ቋንቋዎች (ለምሳሌ፡- አማርኛ፣ እንግሊዝኛ) እንደሚማሩት ተማሪዎች እኩል ላናውቅ ወይም በስራ እኩል መወዳደር አንችል ይሆናል የሚል | 3.11 | .513 |
| | አጠቃላይ የአማካይ አማካይ | 4.112 | 0.492 |

*(ምንጭ፡- ከጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተገኘ የመስክ መረጃ፣ 2013ዓ.ም.)*

ከፍ ሲል በቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው የቀረበው መረጃ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ዙሪያ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ለማጤን የሚያግዝ ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች የተለያዩ የአመለካከት ገላጮችን ሁኔታ ለመገንዘብ የሚረዱ መረጃዎች በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ከጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል የሚበልጡት 201 (40.0%) በጣም እስማማለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቀሙ፣ 162 (32.3%) እስማማለሁ የሚለውን የመልስ አማራጭ የጠቀሙ ሲሆኑ፣ 87 (17.3%) አቋም አልያዝኩም የሚለውን የመልስ አማራጭ ያመለከቱ፣ 52 (10.4%) አልስማማም የሚለውን መልስ የጠቀሙ ናቸው፡፡ ፈጽሞ አልስማማም የሚለውን አሉታዊ አማራጭ የጠቀሙ የሉም፡፡ በሌላ በኩል የጥናቱ ተሳታፊዎች ከላይ በሰንጠረዥ 8 ለቀረቡት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማር አመለካከት ገላጮች የሰጡት ምላሽ አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ)= 4.112 ሲሆን አማካይ መደበኛ ልይይት=0.492 ነው፡፡ አማካይ መደበኛ ልይይቱ እንደሌሎቹ የቀደሙ ትንተናዎች ዝቅተኛ (ከ0.5) በላይ መሆኑ የስምምነቱ ማእቀፍ በመጠኑ ሰፊ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ይሁንና ከቀረቡት ስታቲስቲካዊ ገላጮች ሁሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማር ጠንካራ አዎንታዊ አመለካከት በተማሪዎች ዘንድ መኖሩን አጠቃላይ የአማካይ አማካይ በሌሎቹ ስታቲስቲካዊ ትንተና ከቀረቡት አንጻር ከፍተኛ መሆኑ አመላካች ነው፡፡

በዝርዝር ሲጤን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ በሚገባ በሚያውቁት ቋንቋ የሚሰጥ በመሆኑ የሚማሯቸውን ትምህርቶች ሁሉ በይበልጥ ለመረዳት ጠቃሚ ሆኖ እንዳገኙት ተጠኚዎቹ

የገለጹት በአጠቃላይ አማካይ 4.74 እና በመደበኛ ልይይት 0.322 ተደግፎ ቀርቧል፡፡ ቀጥሎም በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማር ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ መሆኑን በአጠቃላይ አማካይ 4.69 እና በመደበኛ ልይይት 0.407 እንዲሁም በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ለኛ የትምህርት ቤት ቆይታ አስደሳች ክንዋኔ ነው ያሉ በአጠቃላይ አማካይ 4.57 እና በመደበኛ ልይይት 0.521 ተደግፈው የቀረቡ ስምምነቶች ናቸው፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ ባህልን ለማወቅ፣ ሰብዕና ለመገንባትና ለስነልቦና እድገት የጠቀማቸው መሆኑን በአጠቃላይ አማካይ 4.44 እና በመደበኛ ልይይት 0.445 እንዲሁም በትምህርት ቤት ቆይታቸው ከመምህራንና ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመግባባት ትኩረት የሚሰጡ መሆናቸውን በአጠቃላይ አማካይ 4.37 እና በመደበኛ ልይይት 0.550 ተደግፈው የቀረቡ ስምምነቶች ሲሆኑ፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ጥሩ የተግባቦት ችሎታ እንዲያዳብሩ የረዳቸው መሆኑን በአጠቃላይ አማካይ 4.28 እና በመደበኛ ልይይት 0.557 የተደገፈ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ቀጥሎም በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ለይተው የሚያውቁ መሆናቸውን በአጠቃላይ አማካይ 4.15 እና በመደበኛ ልይይት 0.545 በተደገፈ ምላሽ ገልጸዋል፡፡

ከአፍ መፍቻ ቋንቋ የትምህርት ቋንቋነት አመለካከት ጋር ተያይዘው ከቀረቡት ገላጮች አንጻራዊ ዝቅተኛ ምላሾች የታየባቸው ደግሞ በቅደም ተከተል በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ እወዳለሁ ለሚለው ገላጭ በአጠቃላይ አማካይ 3.41 እና በመደበኛ ልይይት 0.501 የተደገፈ፣ ሁሉንም የትምህርት አይነቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማር አጥጋቢ ውጤት ለማምጣት እተጋለሁ ለሚለው ገላጭ በአጠቃላይ አማካይ 3.36 እና በመደበኛ ልይይት 0.555 የተደገፈ እንዲሁም በአፍ መፍቻ ቋንቋ የምንማር ተማሪዎች በሌሎች ቋንቋዎች (ለምሳሌ፡- አማርኛ፣ እንግሊዝኛ) እንደሚማሩት ተማሪዎች እኩል ላናውቅ ወይም በስራ እኩል መወዳደር አንችል ይሆናል የሚል ስሜት በበኩሌ አይጫነኝም ለሚለው ገላጭ የሰጡት በአጠቃላይ አማካይ 3.11 እና በመደበኛ ልይይት 0.492 የተደገፈ ምላሽ አቅርበዋል፡፡

በአጠቃላይ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከአፍ መፍቻ ቋንቋ የትምህርት ቋንቋነት አመለካከት ጋር ተጠኚዎቹ የሚገኙበት አቋም ከአሉታዊነት የጸዳና የሚበረታታ ነው፡፡ ለተማሪዎቹ የቀረቡ የአመለካከት ገላጮች የተመዘኑበት መጠን በአጠቃላይ

የአማካይ አማካይ (ẍ)=4.112 መሆኑ በባለቤቶቹ ዘንድ አፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመማሪያ ቋንቋ መሆኑ ለፍላጎታቸው የሚስማማ መሆኑን እንደሚያምኑ የሚያመለክት መሆኑን ጥናቱ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በጥቂት የክፍል ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አተገባበር ጋር በተያያዙ ለምሳሌ፡- በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ ስለመውደዳቸው፣ ሁሉንም የትምህርት አይነቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማር አጥጋቢ ውጤት ለማምጣት ስለሚያሳዩት የትጋት መጠን እንዲሁም በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በሌሎች ቋንቋዎች (ለምሳሌ፡- አማርኛ፣ እንግሊዝኛ) እንደሚማሩት ተማሪዎች እኩል ላናውቅ ወይም በስራ እኩል መወዳደር አንችል ይሆናል የሚል ጥርጣሬ የማይሰማቸው ስለመሆኑ የሰጧቸው ምላሾች አንጻራዊ ዝቅተኝነት የሚታይባቸው ገላጮች መሆናቸውን ጥናቱ ተመልክቷል፡፡

በተመሳሳይ መምህራን፣ ርእሰመምህራንና የወመህ ተሳታፊዎች በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፖሊሲና አተገባበር ዙሪያ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል በቃለመጠይቅ የተደገፈ መረጃም ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፖሊሲና አተገባበር ዙሪያ በተለይ በመምህራን የተያዘ አመለካከት ለአፋን ኦሮሞ ትምህርት አጠቃላይ ስኬታማነት የራሱ ተጽእኖ እንዳለው የታወቀ ነው፡፡ መ.ቁ.1 ከዚህ ጋር አያይዘው በሰጡት ምላሽ እንዲህ ብለዋል፡በእርግጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ አስፈላጊነት ላይ በግሌ ጥያቄ የለብኝም፡፡ ፖሊሲው በብዙ ብዝሃ ቋንቋ ተጠቃሚ ሀገሮች በተግባር የተፈተነና ለህጻናት ሁለንተናዊ የሰብእና እድገት አስተዋጽኦው ከፍ ያለ መሆኑንም እረዳለሁ፡፡ ነገር ግን ወርዶ በስራ ላይ ሲውል ሌሎች ቋንቋዎችን (ሁለተኛና የውጪ ቋንቋ) ያለመቀበል ወይም የማጥፋት አካሄድ እስኪመስል ድረስ ተማሪዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውጪ በሌሎች ቋንቋዎች ላይ እንዳያተኩሩ የሚያስገድዱ ግፊቶች እንደነበሩ አውቃለሁ፡፡ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ የሚሰጠው ትኩረት የሚማሯቸውን ትምህርቶች የበለጠ ተረድተው በትምህርታቸው ጥሩ ተፎካካሪዎች እንዲሆኑ፣ ማህበራዊ አካባቢያቸውን በሚገባ እንዲገልጹና የተግባቦት ችሎታ እንዲያዳብሩ ለማስቻል ያለውን ጠቀሜታ አምናለሁ ብለዋል፡፡

መ.ቁ.2 በበኩላቸው በእኔ እምነት ፖሊሲውና አተገባበሩ ይጣረሳሉ፡፡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማራቸው በራሳቸው ባህልና ማህበራዊ አካባቢ ላይ ተመስርተው ትምህርቱን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ማገዝ ነው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋን የመማሪያ ቋንቋ የማድረግ ፖሊሲ በብሄርተኛ አመለካከት ባይመራ እመርጣለሁ፡፡ የመማር ማስተማሩ

ሂደት ላይ የሚታዩ ችግሮች ስፋት አሳሳቢ ከመሆኑ በቀር በእኔም ሆነ በተማሪዎቼ ዘንድ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማር አሉታዊ አመለካከት አለ ብዬ አልጠራጠርም ብለዋል፡፡

መ.ቁ.3 እንደገለጹት አንዳንድ ከገጠሩ ማህበረሰብ የወጡ ተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን ላይ ሲደርሱ ትምህርት ያቋርጣሉ፡፡ ከጊዜያቸው በፊት ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎች ባህሪያቸው በአግባቡ ቢጠና 8ኛ ክፍልን እስኪጨርሱ ድረስ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ ብቻ ያተኮረ አጽንኦት ተሰጥቶ እንዲማሩ ‹መመሪያ ያልሆነ ነገር ግን መመሪያ የሚመስል› ጉልህ ትኩረት አለ፡፡ ለሌሎች ቋንቋዎች ተመጣጣኝ ትኩረት አይሰጥም፡፡ ይህ ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን በተፎካካሪነት ለመቀጠል የሚያስችል ብቃት እንዲያጡ ያደርጋቸዋል፡፡ ልጆቹ በተቀሩት ቋንቋዎች ብቃት እንደሌላቸው ሲያስቡ ትምህርት የመቀጠል ተነሳሽነትም ያጣሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎችን አውቃለሁ፡፡ እርስ በርሱ የተደጋገፈና ለሁለተኛ ቋንቋ ተመጣጣኝ ትኩረት አለመስጠት እንጂ የአፍ መፍቻ ቋንቋን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማቅረቢያ ቋንቋ መሆኑ ላይ አሉታዊ አመለካከት የለኝም፡፡ እኔ ራሴ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ተምሬ ነው አሁን ያለሁበት ቦታ ያለሁት፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ችሎታዬ እምብዛም ተግባቦት የሚያደፋፍር አለመሆኑ ቅር ይለኛል ብለዋል፡፡

መ.ቁ.4 በበኩላቸው ፖሊሲውና አተገባበሩ በጣም ይለያያል፡፡ ፖሊሲው ሲዋቀር ተማሪዎቻችን ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ ከወላጆቻቸው በወረሱት፣ በሚያውቁት፣ በሚረዱት፣ በሚግባቡበት፣ በሚጠይቁበትና በሚመልሱበት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማራቸው ያለውን ሁለንተናዊ ጠቀሜታ እግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ነገር ግን ከአተገባበር አንጻር በተጨባጭ የሚታዩ ተግዳሮቶች እንዳሉ ይሰማኛል፡፡ ከመምህራን ስልጠና ጀምሮ ከትምህርት ባለድርሻዎች በሚጠበቁ ልዩ ልዩ ሚናዎች ዙሪያ ክፍተቶች አሉ፡፡ አልፎ አልፎ እንዳስተዋልኩት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ስንደርስ በእንግሊዝኛ ስለምንማር አሁን በምናውቀው የራሳችን ቋንቋ መማራችን አይጠቅመንም ብለው የሚያስቡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ላይ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ጥቂት ተማሪዎች አጋጥመውኛል ብለዋል፡፡

በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፖሊሲና ትግበራ ዙሪያ መ.ቁ.5 እና መ.ቁ.6 ያላቸውን ምልከታ ሲገልጹም፤ በአብዛኛው በተማሪዎች ዘንድ ስለ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማር የተያዘው አመለካከት በጣም አዎንታዊና የሚበረታታ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ግን በወላጆችና

በተማሪዎች ዘንድ የምናውቀውንና የራሳችንን ቋንቋ መማር ለምን ያስፈልገናል? የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ የተማሪዎችን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ብቃት የሚጎትት አሉታዊ አስተሳብ አለ፡፡ እንዲህ ያለ አስተሳሰብ የያዙ ተማሪዎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ወይም ዩኒቨርሲቲ ስንገባ ከሌሎች ክልሎች ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለን በእንግሊዝኛ ስለምንማር ተፎካካሪ መሆን አንችልም የሚል አስተሳሰብ የያዙ ናቸው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል የቃለመጠይቅ ተሳታፊ ርእሳነመምህራን ከፍ ሲል በመምህራኑ የቃለመጠይቅ ተሳታፊዎች ለመቀበል ከተሞከሩት መረጃዎች ባልተለየ መልኩ የአፍ መፍቻ ቋንቋው ፖሊሲና አፈጻጸሙ ሰፊ ልዩነት እንደሚታይበት የመሰከሩ ሲሆን ይህም የሆነበት ምክንያት ፖሊሲ ቀረጻ ላይ ያሉት ባለሙያዎች ታች /Grassroot level/ ያሉትን ተጨባጭ ሁኔታዎች የተገነዘቡ አይመስሉም ሲሉ ይተቻሉ፡፡ ፖሊሲው ፖለቲካዊ ድጋፍ ያለው ከመሆን በዘለለ በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰቦች ውይይት፣ ግንዛቤና የድጋፍ መሰረቶች ላይ የተገነባ አለመሆኑ ላይ ሁሉም የቃለመጠይቁ ተሳታፊ ርእሰመምህራን የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡

ይሁን እንጂ እንደነዚህ መረጃ አቀባዮች ስምምነት በርካታ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ወላጆች በገጠሩ ክፍል የሚገኙ በመሆናቸው የልጆቻቸውን የአፋን ኦሮሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመደገፍና ለማበረታታት የሚችሉ አይደሉም፡፡ ጥቂት ትምህርት የቀመሱ ወይም በትምህርት የዘለቁ ወላጆች የልጆቻቸውን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የማበረታታት ድርሻ እንዳላቸው እናውቃለን፡፡ ነገር ግን እንዲህ አይነት ወላጆች በተለይ በገጠር ከተሞች የሚገኙና ልጆቻቸው በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማራቸው ያለውን ጠቀሜታ ተገንዝበው ለማበረታታት ጥረት የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ልጆችን በማስጠናትና ወደ ቤት ይዘው በሚሄዱቸው ስራዎች በማስጠናት ረገድ ተሳትፎ ያላቸው የተማሩ አባቶች፣ ወንድሞች፣ እህቶች ባይበዙም እንዳሉ እናውቃለን፡፡

ከመምህራንና ርእሰመምህራን የተሰበሰቡት መረጃዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች ተነሳሽነት ከአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ተማሪዎች ይልቅ በታችኛው የመጀመሪያ ሳይክል የሚማሩ ተማሪዎች ተነሳሽነት ከፍ ያለ ነው፡፡ በክፍል ደረጃ ከፍ እያሉ ሲሄዱ ሁሉም በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት ያጣሉ ባይባልም፤ ተነሳሽነት የሚጎድላቸው መሆናቸውን የሚጠቁሙ ባህርያትን የሚያንጸባርቁ ተማሪዎች በየክፍሉ ማግኘት የተለመደ ነው፡፡

በተለይ መምህራኑ እንደሰጡት መረጃ ትምህርቱን ተማሪ ተኮር ማድረግ በተማሪዎች ተነሳሽነት፣ ፍላጎትና ንቁ ተሳትፎ መደገፍን የሚጠይቅ ቢሆንም በተሳትፎ የሚገለጽ ተነሳሽነት የማይታከይባቸው ብዙ ተማሪዎችን እናገኛለን ብለዋል፡፡

አንዳንድ የቃለመጠይቁ ተሳታፊ መምህራን ስለተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አመለካከት የሰጡት ለየት ያለ ምላሽም የተለየ ትኩረት የሚስብ ነው፡፡ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚበዙት ህጻናት በመሆናቸው ትክክለኛ ስሜታቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ ይከብዳል፡፡ ነገር ግን በእኛ ምልከታ አዎንታዊም አሉታዊም አመለካከት አላቸው ብሎ ለመናገር ይቻላል ብለዋል፡፡ አዎንታዊ በማለት የመለሱት መምህራን ምክንያታቸውን ሲገልጹ፣ ሲማሩ ሀሳባቸውን እንደ ፈለጉ ስለሚገልጹና ትምህርቱ ስለሚቀላቸው ይወዱታል በማለት ሲገልጹ፤ አሉታዊ በማለት የመለሱት አንድ የቃለመጠይቁ ተሳታፊ ምክንያታቸውን ሲገልጹ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውና እንግሊዝኛ ተመሳሳይ ፊደልን ስለሚጠቀሙ ሁለቱን ቋንቋዎች በሚማሩበት ወቅት እየተምታታባቸው ስለሚቸገሩና ይመስለኛል ብለዋል፡፡ ይህም የመጨረሻው ሀሳብ በተለይ ቀደም ሲል በተማሪዎቹ ስታቲስቲካዊ መረጃ ከተተነተነው በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ ስለመውደድ ከተጠቀሰው የአመለካከት ውሱንነት ጋር የሚዛመድ አስተያየት ነው፡፡

በሌላም በኩል ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ከመማር አመለካከት ጋር በተገናኘ ር/መ.ቁ.2 በተለይ እንደገለጹት ልጆች ሁለት አይነት ስሜት ያንጸባርቃሉ፡፡ አፋቸውን በፈቱበት ቋንቋ ሲማሩ ትምህርቱ ስለሚገባቸው ደስ ይላቸዋል፡፡ ነገር ግን አማርኛ ለማወቅ ባላቸው ፍላጎት የተነሳ ከኦሮምኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ አማርኛንም መማር የሚመርጡ ተማሪዎች በጥቂቱም ቢሆን አሉ ብለዋል፡፡ በር/መ.ቁ.3 ገለጻ መሰረት ግን፤ እንደ አጠቃላይ በታችኞቹ መማሪያ ክፍሎች ያሉ ተማሪዎች በአፍ መፍቻቸው በመማራቸው ደስተኞች ናቸው፡፡

በተለይ ከወላጅ መምህራን ህብረት (ወመህ) ተሳታፊዎች የተሰበሰቡት የቃለመጠይቅ መረጃዎች በወላጆችና የየአካባቢዎቹ ማህበረሰቦች ዘንድ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የተያዘ አመለካከት ለማጠቃለል የረዳ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ወመህ ቁ.1 እንደገለጹት፤ እኛ ልጆቻችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማራቸው በጣም ደስተኞች ነን፡፡ ከበፊት እኛ ይህን እድል አግኝተን ቢሆን ኖሮ እንዴት ጥሩ ነበር! እንደኔ አስተያየት በጅማሮው ወቅት ብዙም አልተዋጠልኝም ነበር፡፡

ምክንያቱም የሆነ የፖለቲካ ወረርሽኝ ነበር የመሰለኝ፡፡ አሁን ግን በሚገባ ደስተኛ ሆኛለሁ፡፡ ልጆቻችንም በአፍ መፍቻ ቋንቋችን ተምረው ስራ እየያዙ ነው ብለዋል፡፡ ወመህ ቁ.2 በበኩላቸው ልጆቻችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲማሩ የተቀረጸው ፖሊሲ ጥሩ ነው፡፡ ምክንያቱም አጣርተው በሚያውቁት ቋንቋ በመማራቸው ብዙ ነገሮችን እየተረዱና እያወቁ መሄዳቸው ደስተኞች ያደርጋቸዋል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

## 4.5 የጥናቱ ውጤቶች ማብራሪያ

በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች ተሰብስበው የተተነቱት የጥናቱ መረጃዎች እርስ በርስ ተደጋጋፊ በሆነ መልኩ በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመማሪያ ቋንቋነት በመካሄድ ላይ ባለው ትግበራ ዙሪያ የሚታዩ ተግዳሮቶችን ተያያዥ መንስኤዎችንና በአፍ መፍቻ ቋንቋው ፖሊሲና የመማሪያ አውዱ ያሉ ማህበራዊ አመለካከቶችን ለማብራራት አስችለዋል፡፡ በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትግበራ የሚታዩ ችግሮችን በስፋትና በጥልቀት ለመዳሰስና የጥናት ውጤት ላይ ለመድረስም የረዱ ናቸው፡፡ በመጠናዊና አይነታዊ ስልት የተተነተኑት መረጃዎች አንዱ ሌላውን የሚያጠናክሩ እና ተደጋጋፊነት ያላቸው ናቸው፡፡

ተማሪዎች በቤታቸው የሚጠቀሙበትን የአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማሪያ ቋንቋ ማድረግ ከሰብአዊ ህጋዊ መብት አንጻር የሚታይና ከህጻናት የሚማሩትን የትምህርት ይዘት በተሻለ መረዳት ባህሪ ጽንሰሃሳባዊ መሰረት ጋር የሚገናኝ እሳቤ ነው፡፡ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያካሂዷቸውን መስተጋብሮች ያለ ቋንቋ መሰናክል ተግባቦት ለማድረግና የሚማሩትን የትምህርት ይዘት በቀላሉ ለመገንዘብ፣ የሚማሩትን ትምህርት እንዲወዱት ለማድረግ፣ በራስ መተማመን መንፈስ የመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማገዝ ጠቀሜታው ሰፊ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር የራስን ማንነት እና የራስ ቋንቋን አጠቃቀም፣ ባህልና ታሪክ ግንዛቤዎችን ለማዳበር ይረዳል፡፡

ከዚህ አጠቃላይ እሳቤ በመነሳት ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ መጠናዊና አይነታዊ መረጃዎች በየርዕሰጉዳያቸው ስር እየተደራጁ በስታትስቲክሳዊ ስሌትና በገለጻ ተተንትነዋል፡፡ እነዚህ ትንታኔዎች ማብራሪያና ትርጓሜ ስለሚያስፈልጋቸው በዚህ ክፍል የማብራራቱና የመተርጎሙ ስራ ተከናውኗል፡፡ የጥናቱን ንዑሳን አላማዎች መሰረት በማድረግ ትርጓሜዎችና ማብራሪያዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የተማሪዎች አእምሯዊና ስነስሜታዊ እድገት በተጨባጭ እውን የሚሆነው በዋንኛነት ተማሪው አስቀድሞ በሚያውቀው ቋንቋ እንዲማር ሲደረግ ነው፡፡ ተማሪዎች እንዲማሩበት ፣መምህራንም እንዲያስተምሩበት በሚፈለገው ቋንቋ አስቀድሞ የሰረጸ ግንዛቤ ያላቸው ከሆነ ለትምህርቱ ጥራት አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ የቋንቋ ክህሎታቸውንና እውቀታቸውን ያሳድጋል፡፡ ከዚህም በላይ ተማሪዎች ከፍ ያለ በራስ የመተማመን ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡ የሚማሩትን ትምህርት ጽንሰሃሳብም በበለጠ ይገነዘባሉ፡፡ በመሆኑም ስርጸት ባለው መንገድ የተደራጀ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ ለሆነ የመማር ማስተማር ሂደት ብሎም ለተሻለ ክህሎትና ግንዛቤ እንደ አዋጭና ምቹ ቅድመ ሁኔታ ሊወሰድ የሚገባው ነው ሲሉ (Khejeri 2014፣ Kroskrity 2010) ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጂ በአጠቃላይ በጥናቱ በተሳተፉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዶች የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ለጽሁፍ የሚያገለግሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላት ስያሜዎችን ለመረዳት ተማሪዎቹ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ጉልህ ናቸው፡፡ ይህም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላት እንዲሁም ጽንሰ-ሃሳቦችን የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ሊረዷቸው በሚያስችሏቸው ቀለል ያሉ መበየኛዎች ተደግፈው በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ካለመቅረብ ብሎም በሙዳዬ ቃላት ገጾች ሳይንሳዊ ፣ ቴክኖሎጂያዊ ቃላትንና ውስብስብነት ያላቸው ጽንሰሃሳቦች ለመፍታት የሚያስችሉ አምዶች አለመካተት ትኩረት የሚሻ ችግር ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ተማሪዎቹ የተለያዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላትን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ አቻ ትርጉም አሟልቶ የያዘ መዝገበ ቃላት በቤተመጻህፍት በበቂ አለማግኘታቸውም አሳሳቢ ችግር ነው፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሁለተኛው ሳይክል የሚማሩ ተማሪዎች ምናልባትም በባህላቸው ውስጥ በሰፊው ከማይታወቁ እንግዳ ጽንሰሃሳቦችና አዳዲስ ሳይንሳዊ ቃላት ጋር የሚተዋወቁበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ይታሰባል፡፡ በክልል ደረጃ የሚገኙ የየትምህርት አይነቱ ባለሙያዎችና የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች ከመማሪያ መጻህፍት መሰናዶ ጋር የተለያዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላትን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ አቻ ትርጉም አሟልቶ የያዘ መዝገበ ቃላት በበቂ አዘጋጅተው ለትምህርት ቤቶች ማደል ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተጨባጭ እገዛ እንደሚኖረው ቢታሰብም፤ የእነዚህ ድጋፎች አለመኖር ችግሩን አጉልቶታል፡፡

በሌላ በኩል የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለትምህርት መስጫነት ማዋል ጋር እንቅፋት ከሚሆኑ ጉዳዮች አንዱ ስነልሳናዊ ተግዳሮት ነው፡፡ ከስነልሳናዊ ተግዳሮቶች መካከል በቃል ሲነገር

የቆየን ቋንቋ በጽሁፍ የማዋል ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ቋንቋው የጽሁፍ ቋንቋ ከመሆኑ በፊት መደበኛ ሰዋስዋዊ ስርዓቱን መለየት፣ ለጽሁፍ የሚያገለግሉ ቃላትን መምረጥ ፣ በቋንቋው ውስጥ ለሚገኙ ድምጾች ተስማሚ ሆሄያትን መፍጠር፣ ሳይንሳዊና ሙያዊ ስያሜዎችን የሚተኩ ቃላት የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህም ጋር በቋንቋው ውስጥ የዘዬዎች መብዛትና መራራቅ ሲያጋጥምም የጽህፈት ስርዓቱን በቀላሉ ለማዘጋጀት ያስቸግራል፡፡ በዚህም የተነሳ አብዛኞቹ የአፍሪካ ቋንቋዎች በጽህፈት ቀረጻ ፣ በመዝገበ ቃላት ዝግጅት፣ በቋንቋ መደበኛነት እና በትምህርት ቁሳቁሶች ዝግጅት ያልተሟሉና ያልበለጸጉ በመሆናቸው ለማስተማሪያነት ለመጠቀም ጥረት በሚደረግበት ወቅት ችግር ይፈጠራል (Birgit

ሌላው የመጻፍ ክንዋኔ ውስብስብነት ባህሪ በሁሉም የቋንቋ መማሪያ አውዶች የበርካታ ተማሪዎች የጭንቀት ምንጭ እንደሆነ ይይቷለል፡፡ የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የላቲን አጻጻፍ ስርአትን የሚከተል በመሆኑ ጠብቀው የሚነበቡ ቃላትን በአናባቢም በተነባቢም መደጋገምን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በእርግጥ ተማሪዎቹ በራሳቸው ቋንቋና በባህላቸው ከሚነገሩ ቃላት የትኞቹ ጠብቀው ወይም ላልተው እንደሚጠሩ ለይቶ የማወቅ ችግር እምብዛም አያጋጥማቸውም ይሆናል፡፡ ነገር ግን ብዙ ፊደላትን የሚፈጁ ቃላትን አብዛኛውን ጊዜ በርካታ ተማሪዎች አስተካክለውና አርመው ለመጻፍ እንደሚቸገሩና የጥናቱ መረጃዎች እማኝ ናቸው፡፡ ቃላቱን በሚጠሩበት መንገድ በጽህፈት ማቅረብ በሰፊ የመጻፍ ተሞክሮና ደጋግሞ በመጻፍ ልምምድ የሚሰርጽ ነው፡፡ የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን በቅድመ ስራና የስራ ላይ ስልጠና ከልዩ ልዩ የመጻፍ ክሂል ብልሃቶች ስልጠናዎች ጋር በማስተዋወቅ ተማሪዎቻቸውን እንዲያግዙ ማድረግ አስፈላጊ የሚሆነውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

በጥናቱ አካባቢ አንዳንድ ስነትምህርታዊ ተግዳሮቶች መኖራቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡ ከነዚህ አንዱ ከቋንቋ መደበኛነት ጋር ተያይዞ ያለው ችግር ነው፡፡ አንድን የአፍ መፍቻ ቋንቋ የትምህርት ቋንቋ ከማድረግ ጋር ሞዴል የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ስርአት /standard/ መኖር አብሮ የሚታሰብ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ለአንድ ቁስ ወይም ሐሳብ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የዚያው ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦች በተለያዩ ቃላዊ ስያሜዎች መጠራታቸውን ተከትሎ ያለው ስነትምህርታዊ ተግዳሮት ተጠቃሽ ነው፡፡ በክልል ደረጃ ሁሉም የታላሚው ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦች ሊጠቀሙበት የሚችሉት አንድ መደበኛ /ስታንዳርድ/ መጠሪያ መስጠት አስፈላጊ ቢሆንም፤ የመማሪያ

መጻህፍት አዘጋጆች በክልል ደረጃ አንድ መደበኛ ቃል ያለመጠቀም ጉዳይ ችግር ሆኖ ይታያል፡፡ የአንድ ቁስ ወይም ሀሳብ መጠሪያ እንደ አዘጋጆቹ የቋንቋ ዳራ ልምድ በመጽሐፎች ዝግጅት ውስጥ የሚቀርብበት ሁኔታ አረዳድን ያስተጓጉላል፡፡ በመሆኑም በስታንዳርዳይዜሽን መርህ በመደገፍ ዘዬዎችን በመቀነስ ለቃላት መደበኛ የሆኑ ፍቺዎችን በኦሮምኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት እና ትምህርታዊ መዝገበ ቃላት ውስጥ ትኩረት ሰጥቶ ማቅረብ ተገቢ ይሆናል፡፡

እነዚህ ተግዳሮቶች፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች በትምህርት መስጫነት ጥቅም ላይ ሲውሉ ከሚታዩት ስነትምህርታዊ ተግዳሮቶች መካከል ከቋንቋ መደበኛነት፣ከመምህራን ስልጠና ከማስተማሪያ፣መሳሪያዎች ዝግጅት፣ ከጽህፈት ስርዓትና የትምህርት ይዘቶችን በትክክል ወደ ቋንቋዎች የሚተረጉሙ ባለሞያዎች አለመኖር (Hirut, 2008) ካሉት ጋር የሚገናዘቡ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ተጠኚዎቹ ተግዳራቶቹን ተቋቁመው በክፍል ውስጥ እውቀት የሚተላለፍበት መንገድ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምዳቸው ጋር የተገናዘበ በመሆኑ ለሚበዙት የአንደኛ ደረጃ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች የመማር ሂደት አስደሳች መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም ትምህርቱ በሚያውቁት፣ በሚናገሩበት፣  አጣርተው በሚያዳምጡበት፣ ስሜታቸውን ለመግለጽም ሆነ ለመጠየቅ በሚቀላቸው የወላጆቻቸው ቋንቋ ከመማራቸው ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው፡፡ Dumatog & Dekker (2013) እንዳቀረቡት ገለጻ፤ በቋንቋና በባህል መካከል ያለው ጠንካራ ትስስር ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አይነተኛ የመነቃቃት ምንጭ ነው፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ ተተኳሪ የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ ከርእሰ መምህራንና መምህራን የሚያገኟቸው ድጋፎች በአጠቃላይ የአማካይ አማካይ 3.67 ስታቲስቲካዊ ልኬት የተመዘኑ መሆናቸው የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደትን በእጅጉ ለማጠናከር ከፍ ያለ ተነሳሽነት መኖሩን አመላካች አይደለም፡፡ በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች ድጋፎቹ ውሱንነቶች የሚታይባቸው ቢሆንም ጥረቶቹ እጅግ በጣም የተቀዛቀዙ ናቸው ለማለት ግን አይቻልም፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስተዳደሮች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርን በሚገባ ስለማበረታታት ከሌሎች ባለድርሻዎች በተሻለ ቁርጠኝነት የሚያሳዩ መሆናቸው

ከመሪነትና ከትምህርቱ ስራ አስተባባሪነት ሚናቸው የሚመነጭ እንደመሆኑ ይበልጥ አበረታች ጥረቶችን ማካሄድ እንዳለባቸው የአጥኚዋ እምነት ነው፡፡

የተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀም ግንዛቤ እድገት በትምህርት ላይ የሚመሰረትና በቋንቋ መማሪያ ክፍል በተደጋጋሚ በሚደረጉ ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ሞዴል ልምምዶች የሚሰርጽ ነው (Andrews 2007)፡፡ በዚህ መሰረት የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋን መሰረት ባደረገው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተከታታይ ቆይታቸው ለአቅምና ችሎታቸው የተመጠኑ ግንዛቤዎችን ፣ ተሞክሮዎችን እውቀትና ክህሎቶችን በመቅሰም ተበረታችነት እንዲያሳዩ ከርእሰመምህራንና መምህራን ድጋፍና እገዛ ማግኘታቸው የመማር ማስተማሩን ሂደት ስኬታማ ለማድረግ ያለው ጠቀሜታ ከፍ ያለ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጪ ማህበራዊ ፣ ባህላዊ እና ስነልቦናዊ ግንዛቤዎቻቸው እንዲጎለብት፣ በማህበራዊ አካባቢያቸው በብቃት ተግባቦቶች እንዲያካሂዱና በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመጠቀም በራስ ተነሳሽነትና በራስ መተማመን መንፈስ የእድሜ ልክ ተማሪዎች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ተብሎም ይታሰባል፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር ተጓዳኝ የትምህርት ቤት ውስጥ አደረጃጀቶችና አሳታፊ እድሎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስተዳደሮችና መምህራን የቋንቋና የባህል ክበባት በማደራጀት ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማድረግ ተማሪዎችን የማበረታታት አስተዋጽኦው ከፍ ያለ ነው፡፡ ይሁንና በተጎበኙት አንደኛ ደረጃ የማና ወረዳ ገጠር ትምህርት ቤቶች አስተዳደሮችና መምህራን አሳታፊና አነቃቂ የቋንቋና የባህል ክበባት በማደራጀት የሚያሳዩት ንቅናቄ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ባይባልም በሚፈለገው ልክ የጎለበተና ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎቹ ፍላጎቶች ተደራሽነት ያለው እንዳልሆነ አጥኚዋ ተገንዝባለች፡፡ በመሆኑም የቋንቋና የባህል ክበባት በማደራጀት ባህልን የሚገልጹ፣ እሴቶችን የሚያጠናክሩ፣ ማህበራዊ ተግባቦትን የሚያሳልጡ ልዩ ልዩ የግንዛቤ መድረኮችን መፍጠር ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መጠናከር ያለው ስራ ተነሳሽነት የሚያስፈልገው ነው፡፡

ከዚህም ጎን ለጎን በጥናቱ ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስተዳደሮችና መምህራን ተማሪዎቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋ አጠቃቀም አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው በየጊዜው ለእድሜያቸውና ብስለታቸው የተመጠነ ግንዛቤ መስጠት ተገቢ ቢሆንም መረጃዎች የሚያመለክቱት ጥረቱ በሚፈለገው ልክ የዳበረ አለመሆኑን ነው፡፡

ከሁሉም እጅግ አሳሳቢ ችግር ሆኖ የተመለከተው ደግሞ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመማር ያገኙትን እድል ሌሎች ሁለተኛ ቋንቋዎችን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ያደረገላቸው አስተዋጽኦ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡

ሌላው የመምህራን ስልጠና፣ ምደባና ሙያዊ ተበረታችነት በአጠቃላይ የተሰበሰቡት እስታቲስቲካዊ መረጃዎች ትንተና እንደሚያመለክተው በጥናቱ ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ተበረታችነት የራሱ ገደቦች የሚታዩበት መሆኑን አጠቃላይ የአማካይ አማካይ 3.88 አመላካች ነው፡፡ ሁሉንም የትምህርት አይነቶች የሚያስተምሩ መምህራን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ በሚገባ የመናገርና የመጻፍ ችሎታ ያላቸው መሆናቸው ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ይህ መሰረታዊ የመምህራኑ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ችሎታ የመማር ማስተማሩን ሂደት ተስማሚ ማድረግና ለተማሪዎቹ እርካታ መስጠት ይኖርበታል፡፡ መምህራኑ በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች ሁሉ ተማሪዎቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት እንዲበረታቱ፣ መነቃቃት እንዲያሳዩና ተሳትፏቸው እንዲጎለብት የሚያደርጉላቸው ተከታታይ እገዛ አመርቂ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ መምህራኑ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎቻቸው የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በማቃለል የሚያደርጉላቸው የድጋፍ መጠንም ገደቦች የሚታዩበት መሆኑን ጥናቱ ቃኝቷል፡፡

የመስክ ምልከታ መረጃዎች ጭምር እንደሚያመለክቱት በኦሮምኛ አፍ መፍቻ ቋንቋ በየትምህርት አይነት ተኮር (subject specific) የሰለጠኑ መምህራን እጥረት የኦሮምኛ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን በሚገባ ከመተግበር ጋር ተያይዞ የሚታይ ችግር ነው፡፡ ስልጠና ከተለያዩ የትምህርት አይነቶች ጋር ተያይዞ የሚታሰብና ከአፍ መፍቻ ቋንቋው እውቀት ጎን ለጎን ተገቢ የማስተማሪያ ስልቶችና ብልሃቶች ግንዛቤ ላይ የሚያተኮር፣ በቅድመ-ሥራ ስልጠናና በሥራ ላይ ተሁኖ የሚቀሰም የግንዛቤና የልምድ ቋት ነው፡፡ ምን እሰራለሁ? እንዴት እሰራለሁ? በምን እታገዛለሁ? ምን አይነት ተጨማሪ የድጋፍ ስልቶች ላይ ማተኮር አለብኝ? የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዱን አስደሳችና አነቃቂ ከማድረግ አንጻር ከኔም ከተማሪዎቼም የሚጠበቁ ሚናዎች እንዴት ያሉ ናቸው? ወዘተ. መሰረታዊ የማስተማር ስነዘዴ ጥያቄዎች የሚመለሱት በበቂና ተከታታይ ስልጠናና ተሃድሶ መርሃ-ግብሮች በመደገፍ ነው፡፡

የአይነታዊ መረጃዎችን ትንተና መሰረት በማድረግ ለማብራራት እንደሚቻለው፤ ከመምህራን ስልጠና፣ ሙያዊ ብቃት የስራ ልምድ፣ የመምህራን ምደባ፣ የመስራት ፍላጎት፣ የስራ ሞራልና ተነሳሽነት ጋር ተያይዘው የሚገኙ ሁኔታዎች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መጎልበት የራሳቸው ተጽእኖ ያላቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ በመፍጠር የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት፣ የትምህርት አቀባበልና ውጤታማነት ይወስናሉ፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በሚያስተምሩበት የትምህርት መስክ በሚገባ የሰለጠኑ፣ የማስተማር ፍላጎት ያላቸውና ከተለያየ ማህበራዊ ዳራ ተውጣጥተው፣ የተለያየ ፍላጎት፣ ልምድ፣ እውቀትና የመማር ተሞክሮ ይዘው የተሰባሰቡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎችን የመቆጣጠርና የማሰልጠንና የማገዝ ሃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት የተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ይህን ተልእኮ ለማሳካት በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን በቅድመ ስራ እና በስራ ላይ ስልጠና በተደገፈ መልኩ በየትምህርት አይነቱ የተዘጋጁትን መማሪያ መጻህፍት ይዘቶች እንዴት ማስተማር እንደሚገባቸው ማወቅ እንዲሁም በተሃድሶ ዎርክሾፖች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር በሰፊው እንዲተዋወቁ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህም በStubbs (2008) ገለጻ መሰረት ለውጤታማ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የመምህራን ዝግጅት ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በስልጠና ብቃት የታገዙ መምህራን ተማሪዎቹን ከቋንቋ ፖሊሲ ግቦች አኳያ ለማብቃትና የትምህርት ተሃድሶን ወደ መማሪያ ክፍል ለማምጣት ተነሳሽ እንደሚያደርጋቸው ይታመናል ካሉት ጋር በቀጥታ የሚዛመድ ነው፡፡

በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በተጨማሪ እንዳመለከቱት በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ የሚሰጡት ትምህርቶች ይዘት በአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን በመማሪያ መጻህፍት ከሚቀርቡት ይዘቶች አንጻር ሲታይ በጣም ሰፊ ወይም የተለጠጠና ጠቀሜታው ያነሰ መሆኑ፣ በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ በሚማሩዋቸው ኮርሶች ይዘቶችና በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ በቀረቡ ይዘቶች መካከል ስርአታዊ ቅንጅት አለመኖሩ እና በኮሌጆች ደረጃ ለመምህራን ስልጠና የሚቀርቡ ኮርሶች አንዳንድ ይዘቶች በእጅጉ ውስብስብና ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መማሪያ መጻህፍት ይዘቶች ፍላጎት የማይመጥኑ ወይም ጠቀሜታ የሌላቸው መሆናቸውንም ጥናቱ ዳስሷል፡፡

በዚሁ መሰረት በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚሰጡ ሙያዊ ኮርሶች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ዝግጅትና ለተማሪዎቹ ፍላጎት በሚስማማ መልኩ አለመሆኑም አሳሳቢ ችግር እንደሆነ ጥናቱ ፈትሿል፡፡ Benson (2004) እንደገለጹት፣ የመምህራን ሙያዊ ብቃትና በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ዝግጅት በትምህርት ቤት ቆይታቸው ለተማሪዎች ሞዴል በመሆን መገለጽ መቻል ይኖርበታል፡፡ በትምህርት ቤት ቆይታ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ በግቢ ውስጥ በታላሚው ቋንቋ ከተማሪዎቻቸው ጋር ተግባቦቶችን ለማካሄድ ፍላጎትና ተነሳሽነት ያላቸው ብሎም የታላሚው ቋንቋ እውቀትና ክህሎት ያላቸው መምህራን ተመርጠው መሰልጠናቸው ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራና ግባዊነት መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎችን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ተነሳሽነት፣ መነቃቃት ቀልጣፋ የክፍል ተሳትፎ ይወስነዋል፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መሳሪያዎችና መርጃዎች አለመሟላት ብዝሃ ቋንቋ በሚኖርበት ህብረተሰብ ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫ ቋንቋነት ለመወሰን የሚደረገው ምርጫ ካሉበት ችግሮች ዋንኛው ለትምህርት መርጃነት የሚውሉ ጥሬ ሀብቶች (resources) በበቂ ሁኔታ አለመኖር መሆኑን Baker (1988)፣ Cohen (2000)፣ Seyoum (2009) ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በጥናቱ ተተኳሪ የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ስላሉ ቁሳቁሳዊ ተግዳሮቶች የተሰበሰቡ መጠናዊና አይነታዊ መረጃዎች እንዳመለከቱት ቁሳቁሳዊ ተግዳሮት የአውዱ ቁልፍ ችግር የሚታይበት ነው፡፡በእርግጥ በመንግስትና በአንዳንድ የትምህርት ስራ ላይ ባተኮሩ ግብረሰናያን ብርቱ ተሳትፎ ላለፉት በርካታ አመታት በገጠር ትምህርት ቤቶችን የማነጽ ትኩረት የተነሳ በየቀበሌ ገበሬ ማህበራቱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን የማቋቋምና ፈርኒቸሮችን የማሟላት እንቅስቃሴ ተከናውኗል፡፡ ይህ በትምህርት ተደራሽነት ላይ ያተኮረ እንቅስቃሴ በአንድ በኩል የሚበረታታ ገጽታ ያለው መሆኑ ባይካድም፣ ብቻውን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር አያግዝም፡፡

ትምህርትን ለየገጠሩ ማህበረሰብ ከማዳረስ እሳቤ ጋር አብሮ መታሰብ ያለባቸው መምህራንን በበቂ ሁኔታ ማሰልጠንና እንደ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፍላጎት መመደብ፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ በሁሉም የትምህርት አይነቶች የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍትን ተደራሽነት ማረጋገጥ፣ የትምህርት ቤት ቤተመጻህፍትን ማቋቋምና

በየትምህርት ቤቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መዝገበ ቃላት፣ ማገናዘቢያና አጋዥ መጻህፍት በበቂ ሁኔታ ማዘጋጀትና ማሰራጨት እንዲሁም ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ባህላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ትምህርታዊ ፍላጎቶች የሚመጥኑ የመማሪያ ቁሳቁሶች በየትምህርት ቤቶቹ እንዲሟሉ ማድረግ ተገቢ ትኩረት የተነፈጋቸው ነገር ግን ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መጠናከር በእጅጉ አስፈላጊ ጉዳዮች የነበሩ መሆናቸውን ጥናቱ ፈትሿል፡፡

በሌላ በኩል የወላጆች የትምህርት አጋርነት እጅግ አሳሳቢ ችግር መሆኑን ጥናቱ ተመልክቷል፡፡ የወላጆችና የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ግንኙነት ጠንካራ መሰረት ያለው ነው ሊባል የሚችለው ወላጆች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በአብዛኛው በቤት ውስጥ መጠቀማቸው ለልጆቻቸው በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መማር መነሳሳት የፈጠረላቸው በመሆኑ ብቻ ሊገለጽ የሚችል ነው፡፡ በተረፈ ወላጆች በተማሪዎች አጠገብ የሚገኙ የቅርብ መምህራንና አማካሪዎች ናቸው የሚለው መሰረተ ሃሳብ በተተኳሪዎቹ የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች ተሞክሮ በተግባር የማይታይና ተጨባጭ ያልሆነ፣ ነገር ግን በጣም አስፈላጊ የድጋፍ ምንጭ የነበረ ጉዳይ ነው፡፡ አጠቃላይ የአማካይ አማካይ 2.99 ስታቲስቲካዊ ማጠቃለያ የወላጆች--ትምህርት ቤት--ተማሪዎች የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የድጋፍ ግንኙነት በብዙ ገላጮች ከሚጠበቀው በታች የወረደ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

በገጠር የሚገኙ በርካታ ወላጆች ለራሳቸው ትምህርት የቀመሱና ማንበብና መጻፍ የሚችሉ እንዳልሆኑ በዚህ የትንተና ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ስለተጠኚዎቹ ተማሪዎች ወላጆች የትምህርት ዳራ ከተተነተነው ግላዊ መረጃ ጋር የሚገናዘብ ነው፡፡ በዚህና በሌሎችም የወላጆች የግል ምክንያቶች የተነሳ የገጠር አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማር ከወላጆቻቸው የሚደረግላቸው የድጋፍና ማበረታታት መጠን የተገደበ ነው፡፡ ከዚህም ጋር የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከወላጆቻቸውም ሆነ ከቅርብ ዘመዶቻቸው የመማር ተሞክሯቸውን የሚያበረታታም ሆነ የትምህርት ችግሮቻቸውን ለማቃለል የሚረዳ ድጋፍ የማግኘት እድላቸው በጣም ውሱን ነው፡፡

በጣም አሳሳቢ የሆነው የወላጆችና የትምህርት ቤቶች የቅርብ ግንኙነት ችግር ነው፡፡ በእርግጥ ወላጆችና ትምህርት ቤቶች በተማሪዎች የመማር ባህሪ ጠንካራ የመረጃ ግንኙነት መፍጠር ለተማሪዎች የትምህርት ክትትልና ድጋፍ መጠነ ሰፊ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ወላጆች ከልጆቻቸው የትምህርት ገበታ ያላቸው ርቀት በኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ እንደ

ልማድ የሚታይ እውነታ መሆኑ የትምህርት ስርአቱን የትምህርት መርሆዎች መሬት ያልቆነጠጡ መሆን የሚያመለክት ነው፡፡ ትምህርት ቤቶች ወላጆችን በተማሪዎቻቸው የትምህርት ተሳትፎ ለማመስገንም ሆነ በችግሮቻቸው ዙሪያ ለማወያየት ጥሪ ማድረጋቸው የተለመደና ለመማር ማስተማሩ ሂደት ስኬታማነት ቁልፍ እገዛ ያለው ተግባር ነው፡፡ በዚህ የወላጅ--ትምህርት ቤት ግንኙነት ዙሪያ የመረጃ አቀባዮች አጠቃላይ ምላሽ ግን የወላጆችን ትብብር አሳሳቢነት በጉልህ የሚያሳይ ነው፡፡

ቀደም ሲል በመማሪያ ቁሳቁሶች ተግዳሮቶች አምድ በጥናቱ ተተኳሪ የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር ማስተማሩ ሂደት ቀጥተኛ ግብአት የሆኑ የመማሪያ መጻህፍትና የተወሰኑ የትምህርት አይነቶች መምህር መምሪያዎች አሳሳቢ እጥረቶች እንዳሉ ተቃኝቷል፡፡ አጋዥና ማገናዘቢያ መጻህፍትም የተማሪዎች የትምህርት ፍላጎቶች ለማሟላት በሚረዳ መልኩ አለመሟላት የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዱ ቁልፍ ችግርነት ተወስቷል፡፡ የተማሪዎች ወላጆች እነዚህን ጉድለቶች ለመሙላት ምን ማድረግ እንዳለባቸው አይገነዘቡም አለያም አቅም የላቸውም፡፡ በዚህ የተነሳ በጥናቱ ተተኳሪ የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወላጆች ለተማሪዎቹ ልጆቻቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ የትምህርት ቁሳቁሶች ችግር የሚያደርጉላቸው አካካሽ ብልሃት እና/ወይም የአጋዥ ንባብ ፍላጎቶች የሚሆኑ ምንም ድጋፎች የሉም ለማለት የሚያስደፍር ነው፡፡ በተለይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መሰረቱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እርከን ሆኖ ሳለ በተጨባጭ ግን ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ባህላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ትምህርታዊ ፍላጎቶች የሚመጥኑ የመማሪያ ቁሳቁሶች ተሟልተው አለመገኘት ያለውን ችግር በጉልህ የሚያመለክት ነው፡፡

የፖለቲካ ቁርጠኝነት ለትምህርት ዘርፍ ስኬታማነት እጅግ በጣም ወሳኝ ጉዳይ የሚሆነው ለሌሎች የማህበራዊ ኢኮ፣ ኖሚያዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ባህላዊ፣ ስነትምህርታዊ ሁኔታዎች እድገትም ሆነ ለሙያ ዘርፎች /ሴክተሮች/ የተሰጠውን ድርሻ በትምህርቱ ሴክተር መጠናከር የሚገለጽ ወይም ዋስትናው የሚረጋገጥ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የትኛውም የፖለቲካ ስርአት ጥንካሬ መገለጫው ለትምህርት ስኬታማነት በሚያሳየው ቁርጠኝነት የሚገለጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባለፉት ከ25 በላይ አመታት ትምህርት ቤቶችን በገጠር ለማስፋፋት እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን በየክልሎች ለማካሄድ ፖሊሲ መቀረጹ

አበረታች ቢሆንም፣ ትምህርትን ተደራሽ ከማድረግና የአፍ መፍቻ ቋንቋን በአንደኛ ደረጃ ከመተግበር ጋር የተያያዙ ጉልህና አሳሳቢ ችግሮች እንዳሉ ጥናቱ ፈትሿል፡፡

ፖለቲካዊ አላማውም በተግባር የሚገለጽ የፖለቲካ ቁርጠኝነት የማያገኝበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህንን ሀሳብ Ball (2011) ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አተገባበር ስኬትና ውድቀት ዋናው ነገር ሀገራዊ ወይም አካባቢያዊ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ነው ይላሉ፡፡ ምክንያቱም የፖለቲካ ቁርጠኝነት በቂ በጀት ከመመደብ፣ ጠንካራና ግልጽ የሆነ ፖሊሲ ከማዘጋጀት፣ ህዝብን ከመቀስቀስና ከማስተባበር፣ ከትምህርት አስተዳደር ወዘተ ጋር ጥብቅ የሆነ ቁርኝነት አለው፡፡ በጥናቱ አካባቢም ብዙ ጊዜ ከፖለቲካዊ አመለካከት ጋር የተቆራኙ ትርክቶች ከአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማር ጋር ተቆራኝተው ይቀርባሉ፡፡

በሌላ በኩል የቁሳቁሳዊ ግብዓቶችና የሰው ኃይል መሟላት ብቁ መምህራንን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ማሰልጠንና ለተማሪዎቹ ባህላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ስነትምህርታዊ ፍላጎቶች የሚመጥኑ የማስተማሪያ ግብአቶችን ማቀድ፣ መምረጥ፣ ማዘጋጀትና በበቂ ሁኔታ ማዳረስ ሰፊ መዋእለ ንዋይ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የመዋእለ ንዋይ ጥያቄ ተሟልቶ በተገኘበት ሌላው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ከመተግበር በፊት የሚነሳ ቁልፍ ጥያቄ የቋንቋ ምሁራን፣ የትምህርት ባለሙያዎች ፣ የፖለቲካ መሪዎችና የማህበረሰብ አዋቂዎችን ቁልፍ ባለድርሻነት የሚጠይቀው ጉዳይ ታላሚው የአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማሪያ ቋንቋነት እንዲቀርብ የሚያስፈልግ የመማሪያ ቁሳቁስ ዝግጅት ጉዳይ ነው፡፡ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ ትግበራ የሚያስፈልጉ መርሃ-ትምህርቶችን ማቀድ፣ ከሚገኙበት ምንጭ በተገቢ መስፈርቶች ተደግፎ መምረጥ፣ ወደ ታላሚው ቋንቋ በቋንቋ ምሁራን አማካኝነት በመተርጎም ማዘጋጀትና በበቂ መጠን ማሰራጨት ትልቅ ትኩረትና ዝግጁነት እንዲሁም የኢኮኖሚ ድጋፍ ይጠይቃል (Benson, 2004)፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ የአፍ መፍቻ ቋንቋውን በተሟላ መልኩ የሚወክሉ ፊደላት ዝግጅት እንዲሁም ከልዩ ልዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላት ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ አቻ ፍቺ በመስጠት የማስተማሪያ ግብአቶችን ማዘጋጀት መሆኑን (Wolff, 2006፣ Benson, 2004) ይጠቁማሉ፡፡

ይሁንና የሰው ኃይልና የቁሳቁሳዊ ግብአቶች ተግዳሮት የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራን በማሳለጥ ረገድ ያላቸው ድርሻ እጅግ ዝቅተኛና ትኩረት የሚጠይቅ ነው፡፡ በታላሚው አፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት ማካሄድ ስለቻሉ ብቻ መምህራን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ያለምንም ስልጠና እንዲያካሂዱ ማድረግ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ

ያመዝናል፡፡ Cohen (2000)ና Seyoum (2009) እንደገለጹት፤ በዋንኛነት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ክሂሎች የሰለጠነ መምህር ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በተገቢ ሁኔታ መመደብ አለመቻል በተማሪዎቹ ፍላጎት ፣ ውጤታማነት ፣ አመለካከት ወዘተ ዙሪያ ታላላቅ እንቅፋቶችን ይደቅናል፡፡ የመምህራን ስልጠና የቋንቋ ክሂሎችን ተፈላጊውን ግብ ለማቀዳጀት ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በቋንቋም ማስተማር ዙሪያ ተፈላጊውን ሙያዊ ብቃት ያልያዙ መምህራንን በዘፈቀደ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አውድ ማሰማራት ለትምህርቱ ጥራት፣ ለተማሪዎቹ ተፎካካሪነትና መነሳሳት፣ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት እቅድ አለመሳካት አሉታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ የትምህርት ስርአቱ እነዚህን አጠቃላይ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መጠናከር ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮች ለማቃለል ብሎም የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚፈለገው አቅጣጫ ለመምራት የሚያሳየው ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት በእጅጉ መሻሻል እንዳለበት ጥናቱ ፈትሿል፡፡

በሌላ በኩል ከተማሪዎች አጠቃላይ የመማር ተነሳሽነት፣ የትምህርት ክትትልና የክፍል ተሳትፎ እንደሚጠበቀው አለመሆን፣ ከአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መምህራን ስልጠና፣ ምደባና የማበረታቻ ስልቶች አለመጠናከር ጋር የተያያዙ ጉድለቶች ጉልህነት እንዲሁም የትምህርቱን ስራ ከሚመሩ አካላት፣ የተማሪዎች ወላጆች እና ሌሎች የትምህርት ባለድርሻዎች የሚጠበቅ ተሳትፎና ድጋፍ ዝቅተኛነት ወይማ አለመኖር የሚነሱ በርካታ ተግዳሮቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ በሚፈለገው መልኩ አለመጠናከር አበይት ምክንያቶች ናቸው፡፡

ከባለድርሻዎች ተነሳሽነት ማነስ ፣ ከትምህርት አመራር አለመጠናከርና ከኢኮኖሚ እጥረት መንስኤዎች ጋር የተያያዙ፤ (1) ማገናዘቢያዎችን (references) ለማሟላት በቂ የበጀት አቅም አለመኖር፣ (2) በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚያስፈልጉ የቤተመጻህፍት ስብስቦችን ለማሟላት በሚመለከታቸው የትምህርት ድጋፍ ሰጪና አጋር አካላት ዘንድ በቂ ትኩረትና ቁርጠኝነት አለመኖር፣ (3) ለትምህርቱ ስራ ጠቀሜታ ያላቸውን ሐብቶች መማሪያ መጻህፍት፣ የመምህር መምሪያዎች፣ አጋዥና ማገናዘቢያ መጻህፍት እንዲሁም መዝገበቃላት በመምረጥ፣ በማዘጋጀትና በአግባቡ በማሰራጨት ግልጽ የሆነ የባለቤትነት ተግባር እጥረት (4) የየአካባቢውን ማህበረሰብ ንቅናቄ በመፍጠር የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማቀናጀት አካባቢያዊ ወይም ባህላዊ ሐብቶችን ተጠቅሞ ተነባቢ ነገሮችን (ቃላዊ ልማዶችንና ስነቃሎችን፣ ባህላዊ ትርክቶችንና እውቀቶችን፣ ወዘተ) ለማዘጋጀት የሚረዱ

ብልሃቶችን አለመጠቀም፣ እና በኦሮሚያ ባህል ቢሮ፣ በትምህርት ቢሮና በትምህርት ቤቶች መካከል በመርህ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ ልምድ ውሱንነት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ በሚፈለገው መልኩ እንዳይጠናከር ዋንኛ መንስኤዎች እንደሆኑ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በመጨረሻም የተለያዩ መረጃዎች በተደጋጋፊነት እንደሚያመለክቱት ከአፍ መፍቻ ቋንቋ የትምህርት ቋንቋነት አመለካከት ጋር ተጠኚዎቹ ተማሪዎች የሚገኙበት አቋም ከአሉታዊነት የጸዳና የሚበረታታ ነው፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች ተነሳሽነት ከአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ተማሪዎች ይልቅ በታችኛው የመጀመሪያ ሳይክል የሚማሩ ተማሪዎች ተነሳሽነት ከፍ ያለ ነው፡፡ እርስ በርሱ የተደጋገፈና ለሁለተኛና ለሶስተኛ ቋንቋዎች ተመጣጣኝ ትኩረት አለመስጠት እንጂ የአፍ መፍቻ ቋንቋን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማቅረቢያ  ቋንቋ በመሆኑ ላይ መምህራንም አሉታዊ አመለካከት የላቸውም፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንዳመለከቱት ወላጆችም ልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስለመማራቸውን በብዙ መልኩ እውቅና የሰጡ ናቸው፡፡ ይሁንና አንዳንድ ወላጆች በአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን ብቻ ልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማራቸው ጥርጣሬ አላቸው፡፡

የዚህ ስጋት መንስኤ ተከታታይነት ላይ ያተኮረ ሲሆን የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን የተገደበና በሁለተኛ ደረጃና በዩኒቨርሲቲ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር የማይቀጥል ወይም የትምህርት ማቅረቢያ ስልቱ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ የሚለወጥ በመሆኑ አንዳንድ ወላጆች የተማሪዎች ልጆቻቸው የመማር ተሞክሮ ተነሳሽነት፣ ተፎካካሪነትና ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሳይፈጥር አይቀርም የሚል ስጋት ያላቸው መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

በአንጻሩ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ የትምህርት ቋንቋነት አመለካከት ጋር ተያይዞ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ ስለመውደዳቸው፣ ሁሉንም የትምህርት አይነቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማር አጥጋቢ ውጤት ለማምጣት ስለሚያሳዩት የትጋት መጠን የሰጧቸው ምላሾች አንጻራዊ ዝቅተኛነት አስቀድሞ በስነ-ትምህርታዊ እና ቁሳቁሳዊ ተግዳሮትነት ከተገለጹት የአፍ መፍቻ ቋንቋ የጽህፈት ስርአት፣ የመማሪያ መጻህፍትና ሌሎች ድጋፎች ጉድለቶች ወዘተ የተዋረሱ ችግሮች ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡

ማንበብና መጻፍ በልምምድ የሚዳብሩ፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማር አጥጋቢ ውጤት ለማምጣት የሚደረግ ጥረትም በሰፊ ድጋፍና ጥረት የሚታገዙ እንጂ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ አመለካከት ጋር በቀጥታ የሚገናኙ አለመሆናቸውንም በሌሎች መስቀለኛ ጥያቄ ከተገኙ የአመለካከት ምላሾች ከፍተኛ አዎንታዊነት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁንና በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በሌሎች ቋንቋዎች (ለምሳሌ፡- አማርኛ፣ እንግሊዝኛ) እንደሚማሩት ተማሪዎች እኩል ላናውቅ ወይም በስራ እኩል መወዳደር አንችል ይሆናል የሚል ጥርጣሬ የሚሰማቸው ስላለመሆኑ ተጠኚዎቹ የገለጹበት መጠን አሳሳቢነት የሚታይበት የተጠኚዎቹ አመለካከት ገላጭ ነው፡፡

ይህም ቀደም ሲል ከተተነተኑት የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዱ ልዩ ልዩ ግብአቶችና ድጋፎች ውሱንነትና ከመምህራን ዝግጁነት እሳቤዎች የመነጨ ስጋት ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል፡፡ በአጠቃላይ የጥናቱ መረጃ አቀባይ ተማሪዎች አፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን መማሪያ ቋንቋ ስለመሆኑ በአብዛኛው እውቅና የሚሰጡ ወይም ደስተኞች መሆናቸውን የአመለካከት መረጃዎችን መሰረት በማድረግ መናገር ይቻላል፡፡

በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፖሊሲና አተገባበር ዙሪያ ያለው ማህበራዊ አመለካከት በከፍተኛ ደረጃ አዎንታዊ መሆኑንም መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይሁን እንጂ የተለያዩ ተጽእኖዎች የእስካሁኑን የመማር ማስተማር ሂደት ጤናማነትና ውጤታማነት እየተፈታተኑት እንደሚገኙ መረዳት ይቻላል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ህጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማራቸው ያለውን ትርፋማነት ታሳቢ ያደረገና ጽንሰሃሳባዊ መሰረት ያለው ነው (Cohen 2000፣ Seyoum 2009)፡፡ በእርግጥ የቃለመጠይቅ መረጃ አቀባዮቹ ሙሉ በሙሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፖሊሲው ጠቀሜታ ላይ አሉታዊ አመለካከት የላቸውም፡፡ ይሁንና በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትና በፖለቲካ እሳቤ መካከል ያሉትን ድንበሮች ባለመለየት ተማሪዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በቀር ለሌሎች ሁለተኛ እና የውጪ ቋንቋዎች ትኩረት እንዳያደርጉ በአብዛኛው በስውር የሚካሄድ ግፊት የተሳሳተ ማህበራዊ አዝማሚያ መፈጠርና አዝማሚያው በተማሪዎች የመማር ባህሪ ላይ አሉታዊ ውጤቶች እንዲታዩ መንስኤ ሆኗል፡፡

ከአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ በቀር ለሌሎች ቋንቋዎች (አማርኛ፣ እንግሊዝኛ) በቂና ተገቢ ትኩረት ባለመደረጉ በብዛት ተማሪዎቹ 8ኛ ክፍልን አጠናቀው ሁለተኛ ደረጃ ሲደርሱ ተፎካካሪነት እንዳይኖራቸው አግዷል፡፡ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲያጡ ተጽእኖ አድርጎ መገኘቱም ተጠቁሟል፡፡ 10ኛ ና 12ኛ ክፍልን ጨርሰው ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውጪ በሆኑት ቋንቋዎች በተሻለ ሁኔታ ተግባቦት ማድረግ እንዳይችሉ አስተዋጽኦው ቀላል አለመሆኑንም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አተገባበርን ከፖሊሲ ማእቀፍ አንስቶ እንደገና የማጤንን አስፈላጊነት የሚጋብዝና የተማሪዎች ባለ ብዙ ቋንቋነት እሳቤ ከፖለቲካ ትርክቶች መነጠል አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማር አዎንታዊ አመለካከትን የሚያንጸባርቁ መምህራን በምክንያትነት የሚያነሱት ተማሪዎች ትምህርቱ በቀላሉ ይገባቸዋል ፤ የአካባቢው ባህል ያድጋል ፤ እኛም በምናውቀውና ተማሪዎች በሚያውቁት ቋንቋ ስለምናስተምር ጊዜ ይቆጥብልናል ፤ ብዙ ሳንደክም ተማሪዎች ይረዱልናል የሚል አስተሳሰብ አላቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## የጥናቱ ግኝቶች፣ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳቦች ጥቆማ

የዚህ ጥናት አላማ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በማና ወረዳ በተመረጡ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አፋን ኦሮሞን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ረገድ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች መተንተን ነው፡፡ በጅማ ዞን በማና ወረዳ የሚገኙ በአመቺ ናሙና ዘዴ ከተመረጡ ስድስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች -ሰሞዶ፣ ሳረዶ፣ ቢሊዳ፣ ገሩኬ ጅማቴ፣ ቡጡሬ እና ቡሩ በተማሪዎች መጠይቅ፣ በመምህራን፣ ርእሰመምህራንና የወላጅ- መምህራን ህብረት (ወመህ) ቃለመጠይቅና የክፍል ምልከታ አስፈላጊ የጥናቱ መረጃዎች ተሰብስበው በበቂ ሁኔታ ተተንትነዋል፡፡ እርስ በርስ ተደጋጋፊ በሆነ አኳኋን የችግሩን ስፋት ለማጤንም አስችለዋል፡፡ በዚሁ መሰረት (1) በማና ወረዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አፋን ኦሮሞን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በትምህርት መስጫነት በመጠቀም ረገድ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች ምንድናቸው? (2) በማና ወረዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ የሚታዩ የመማር ማስተማር ሂደት ተግዳሮቶች መንስኤ ምክንያቶች ምን ይመስላሉ? (3) በማና ወረዳ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ወላጆች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ጥናቱ መልሷል፡፡ ጥናቱ የደረሰባቸው ግኝቶችና ማጠቃለያ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

### 5.1 የጥናቱ ግኝቶችና ማጠቃለያ

የትኛውም ቋንቋ ከሌሎች ቋንቋዎች በበለጠ ሁኔታ የራሱን ባህል በብቃት ይገልጻል፡፡ በዚህም የተነሳ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማራቸው የተለየ አድናቆት ያሳድርባቸዋል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቻቸውን ለመግለጽ በእጅ እንዳለ መሳሪያ የሚቆጠር ነው፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት እርከን ተማሪዎች በአፍ መፍቻ  ቋንቋቸው እንዲማሩ ማድረግ ከፍ ያለ ማህበራዊ ክብር እየተሰማቸው እንዲማሩ ለማድረግ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ጥናቶች እንዳመላከቱት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ የተማሪዎችን አእምሮአዊና ስነልቦናዊ እድገት ከፍ ከማድረግ ጎን የተማሪዎችን ውጤታማነት ለማሻሻል በሌላ ቋንቋ ከመማሪያ አውድ በላቀ መልኩ አይነተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል፡፡ ይህ በራሱ

እንደ አንድ ማህበራዊ ግብ የሚወሰድ ስኬት ነው (Kroskrity 2010)፡፡ ይሁንና በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መስጠት ከተጀመረ የአንድ ትውልድ እድሜ ያስቆጠረ ቢሆንም በርካታ ተግዳሮቶች እንዳሉበት ጥናቱ ቃኝቷል፡፡

በዚሁ መሰረት ምንም እንኳን በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማር የተያዘው ማህበራዊ አመለካከት በአብዛኛው አዎንታዊና የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚፈለገው መልኩ ለማራመድ ለም መስክ (fertile ground) መሆኑን የጥናቱ ውጤቶች የሚያመላክቱ ቢሆንም፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውዱ አሳሳቢ የሆኑ የትግበራ ጉድለቶችና ተግዳሮቶች ያሉበት መሆኑን ፍተሻው አረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ የአዳዲስ ትምህርታዊ ቃላት ሁነኛ ፍቺ (terminology) የመደበኛነት ባህሪ ጉድለት፣ ለሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ ቃላት እንዲሁም ልዩ ልዩ ጽንሰሃሳቦች በቋንቋውና በባህሉ ተመጣጣኝ ብያኔ ሰጥቶ የማቅረብ ተነሳሽነት፣ ለልዩ ልዩ ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ ቃላት እንዲሁም በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ የአካባቢ ዘዬዎችን ያማከሉ ልሳነ ዋህድና ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት በማዘጋጀት የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማሩ ሂደት እንዲደገፍ የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛነት፣ የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ የጽህፈት ስርአት የላቲን /ቁቤ/ የአጻጻፍ ስርአት የሚከተል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአናባቢና ተነባቢ የሚደጋገሙ ፊደላት ከቃላት ድምጾች አንጻር በጣም የሚረዝሙ መሆን የተማሪዎችን የመጻፍ ሂደት ውስብስብ ማድረጉና የላቲን ፊደላት በቅርጽ ከእንግሊዝኛ ፊደላት ጋር አንድ ሆነው በአወቃቀር መለያየታቸው አልፎ አልፎ በተማሪዎቹ የመጻፍ ተሞክሮ ላይ ያሳደረው ጫና በስነልሳናዊና ስነትምህርታዊ ተግዳሮትነታቸው ተጠንተዋል፡፡ ይህም በአንድ የተወሰነ ባህል ውስጥ የሚገኙ ትምህርታዊ ይዘቶችን በሌሎች ቋንቋዎች ተርጉሞና አጣጥሞ ለማስተማሪያነት ማቅረብ ያን ያህል ቀላል ክንዋኔ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል የመማር ማስተማሩን ሂደት በተሻለ ሁኔታ ለማካሄድ በሚገባ የሰለጠነ የሰው ኃይል መኖር ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ አውድ ካሉበት ውስብስብ ችግሮች መካከል የመምህራን ስልጠናና ምደባ እንዲሁም ሙያዊ ተበረታችነት በተግዳሮት ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን በሚገባ ለማስተማር የየትምህርት አይነት ተኮር (subject specific) ስልጠና

ላይ መመርኮዝ አስፈላጊ ነው፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ያተኮረ ተሃድሶ መስጠትና የማስተማሪያ መጽሐፉን እንዴት እንደሚጠቀሙበት እንዲያውቁ ማድረግም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ አጋዥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በመምህራን ስልጠናና ምደባ እንዲሁም የሰለጠነ የሰው ሃይልን በገጠሩ ተንከባክቦ ለማቆየት የሚያስችሉ የማበረታቻ ስልቶች ባለመኖራቸው የተነሳ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ አውድ በአንዳንድ የትምህርት አይነቶች በተገቢ መምህራን እየተደገፈ አለመገኘቱን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በተጨማሪም የፖለቲካውን ጠፍ ምህዳር በሰው ሃይል ለማልማት ሰው በአብዛኛው እንዲፈልስ የሚደረገው ከትምህርት ቤትና ከመምህራን ነው፡፡ መምህራን ደግሞ ታላሚውን ቋንቋ የሚያቀላጥፉ በመሆናቸው ይሳባሉ፡፡ መምህራን በገጠር በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እያስተማሩ ለመቆየት ካሉባቸው ስነልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ አውዱ ጉልህ ተግዳሮቶች መሆናቸውን ጥናቱ ደርሶበታል፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ እያስተማሩ ያሉት አንዳንዶቹ መምህራን አፋን ኦሮሞ ቋንቋን አጣርተው የሚናገሩ ይሁኑ እንጂ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የሰለጠኑ አለመሆናቸውንና በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማር ስልጠና ያገኙትም ቢሆን በመምህራን እጥረት የተነሳ የሰለጠኑበትን ትምህርት ብቻ የሚያስተምሩ እንዳይደሉ የጥናቱ ግኝቶች ያረጋግጣሉ፡፡

በሌላ በኩል በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ የሚሰጡት ትምህርቶች ይዘት በአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን በመማሪያ መጻህፍት ከሚቀርቡት ይዘቶች አንጻር ሲታይ በጣም ሰፊ ወይም የተለጠጠና ጠቀሜታው ያነሰ መሆኑ ፣ መምህራን በኮሌጅ በሚማሩዋቸው ኮርሶች ይዘቶችና በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ በቀረቡ ይዘቶች መካከል ስርአታዊ ቅንጅት አለመኖሩ እንዲሁም በኮሌጆች ደረጃ ለመምህራን ስልጠና የሚቀርቡ ኮርሶች አንዳንድ ይዘቶች በእጅጉ ውስብስብና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መማሪያ መጻህፍት ይዘቶች ፍላጎት የማይመጥኑ ወይም ጠቀሜታቸው ያነሱ መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

መምህራን በሚያስተምሩበት የመማሪያ መጽሀፍት ዙሪያ በየጊዜው የተሃድሶ እድሎች አለማግኘታቸው ራሱ ከሰው ሃይል ብቃት እድገት ጋር የሚገናኝና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥን ከማዘመን /ከማሻሻል/ ጋር የሚጎዳኝ ተግዳሮት መሆኑን የጥናቱ ግኝቶች ይጠቁማሉ፡፡

በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት እጥረት፣ የመምህር መምሪያዎች በአንዳንድ የትምህርት አይነቶች አለመኖር(አለመሟላት)፣ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የተሰናዱ የማገናዘቢያ ምንጮች እጥረት፣ አጋዥ መጻህፍትና መዝገበ ቃላት በሚፈለገው ደረጃ አለመኖር፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተለያዩ የትምህርት አይነቶች ጤናማ ሂደት ላይ የተደቀኑ አሳሳቢ እና የተማሪዎቹን ብቃትና ውጤታማነት ሊፈታተኑ የሚችሉ ዋንኛ ተግዳሮቶች መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ከዚህም ጋር በማና ወረዳ ገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቤተ-መጻህፍት እጥረት መኖሩ የአፋን ኦሮሞ ቋንቋን ትምህርትበሚፈለገው ደረጃ ለማጠናከርም ሆነ የተማሪዎችን የማንበብ ልምድ ለማገዝ አለማስቻሉን ጥናቱ ፈትሿል፡፡ የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ በክልሉ መተግበር ከጀመረ የአንድ ትውልድ እድሜ ያህል ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ መሆኑ ቢታወቅም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ከማነጽ ያለፈ የትምህርቱን ሂደት ለማበልጸግ የሚረዱ ግብአቶችን አሟልቶ የመማር ማስተማሩን ሂደት በማጠናከር ረገድ የሚታዩት የሐብት /resource/ ማሰባሰብ ችግሮች በስፋት እየተቃለሉ አለመምጣታቸው አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑንም ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል ወላጆችም ልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስለመማራቸውን በብዙ መልኩ እውቅና የሰጡ ወይም በጎ አመለካከት ያላቸው ከመሆን የዘለለ የተሳትፎና ድጋፍ ሚና የላቸውም፡፡ የጥናቱ ግኝቶች እንደሚያረጋግጡት ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተምረው ለአካባቢያቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ ለውጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ መሰረት የሚያስይዝ እገዛ ለልጆቻቸውም ለሚማሩበት ትምህርት ቤትም ሲያደርጉ አለመታየታቸው አሳሳቢ ተግዳሮት ነው፡፡ ይህም በአንድ በኩል በገጠሩ ህብረተሰብ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ ወላጆች ለራሳቸው የተማሩ ባለመሆናቸው፣ በብዛት በአካባቢያቸው ትምህርት ጨርሰው ወደቤት የተመለሱ ትምህርት ለልጆቻቸው አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርታዊ ድጋፍ ለማድረግ እንዳላስቻላቸው ፤ በሌላ በኩል ወላጆች ለትምህርት ቤቶች መሻሻል ሊያድርጉ በሚችሏቸው አስተዋጽኦዎች ላይ የማህበረሰብ ንቅናቄን የሚየጠናክር ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት አለመኖር ጋር የሚያያዝ ተግዳሮት እንደሆነ የጥናቱ ግኝቶች አመላክተዋል፡፡

በዚህ መሰረት ወላጆች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ባለቤቶች ናቸው ከማለት ይልቅ የሂደቱ ተመልካቾች ወይም ታዛቢዎች ናቸው ማለት ይቀላል፡፡ ወላጆች የተማሪዎች ልጆቻቸው የመማር ሂደት የቅርብ ድጋፍ ሰጪዎችና አማካሪዎች እንደሆኑ ይታሰባል፡፡

ነገር ግን መረጃዎች እንደሚያሳዩት ይህን የድጋፍ መንገድ የሚከተሉ እጅግ በጣም ጥቂት የተማሩ ወላጆች ወይም በቤት ውስጥ የተማሩ ዘመዶች ያሏቸው ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡ ካልተማረ ቤተሰብ የሚመጡ ተማሪዎች በአመዛኙ ስለ ትምህርት ጥቅም የሚያገኙት መረጃ በትምህርት ቤትና በመምህራን ብቻ የተወሰነ በመሆኑ ለተማሪዎቹ የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት፣ ትጋትና ውጤታማነት እንደሚፈለገው አለመሆን ያለውን አሉታዊ አስተዋጽኦ ጥናቱ ቃኝቷል፡፡

ከዚህም ጋር ከሚመለከታቸው የትምህርት ባለድርሻ አካላት ማለትም ባለሃብቶች፣ የቀዬ ተወላጆችና የሲቪክ ማህበራት በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር ማስተማርን ሂደት ለማጠናከር የሚያስችል በመርህ የተደገፈ ተነሳሽነትና ድጋፍ አለመታየት፣ ለትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደት መሻሻል የሚያግዝ የማህበረሰብ ንቅናቄ ደካማነት ለተግዳሮቶቹ መባባስ ጉልህ ድርሻ እንዳበረከተ ጥናቱ ቃኝቷል፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋን የትምህርት ቋንቋ የማድረግ ምርጫ ካሉበት ችግሮች ዋንኛው ለትምህርት መርጃነት የሚውሉ ጥሬ ሀብቶች በበቂ ሁኔታ መኖር ነው፡፡ ከአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ከማድረግ ጎን ለጎን የሚታሰቡ ልዩ ልዩ ግብአቶች በመዋእለ ንዋይ ድልድል የሚሳለጡና ከፍተኛ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነትን የሚጠይቁ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርአተ ትምህርት ታሳቢ የሚያደርጋቸው የስርአተ ትምህርት ንድፍ፣ የመርሃ-ትምህርቶች ዝግጅት፣ በታላሚው ቋንቋ ማስተማሪያና መማሪያ መጻህፍት ትርጉምና ዝግጅት፣ የተለያዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላትን በታላሚው ቋንቋ አቻ ትርጉም አሚልቶ ማቅረብ፣ ልሳነ-ዋህድና ልሳነ-ክልኤ መዝገበ ቃላትን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አዘጋጅቶ በአጋዥነት ስራ ላይ ማዋል የአፍ፣ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መምህራን ስልጠና ሰፊ የሀብት ግብአትን ለሚጠይቁ ጉዳዮች የባለድርሻዎች ሚና ወሳኝ ቢሆንም ትኩረት ማጣት የተግዳሮቶቹ መንስኤ ነው፡፡ በአጠቃላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋው መማሪያ አውድ ግብአቶች /ሪሶውርስ/ እጥረት የመማር ማስተማሩ ሂደት ቁልፍ ችግሮች መንስኤ ምክንያቶች መሆናቸውንና ተግዳሮቶቹ በዋንኛነት ከበጀት /ኢኮኖሚ/ እና የፖለቲካ ቁርጠኝነት ጋር የተያያዙ ስለመሆናቸው የጥናቱ ግኝቶች ያመላክታሉ፡፡

የፖለቲካ ቁርጠኝነት በቂ በጀት ከመመደብ፣ ጠንካራና ግልጽ የሆነ ፖሊሲ ከማዘጋጀት፣ ህዝብን ከመቀስቀስና ከማስተባበር፣ ከትምህርት አስተዳደር ወዘተ ጋር ጥብቅ የሆነ ቁርኝነት አለው፡፡ ይሁንና በጥናቱ አካባቢ ብዙ ጊዜ በተቃራኒው ከፖለቲካዊ አመለካከት ጋር የተቆራኙ ትርክቶች ከአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማር ጋር ተቆራኝተው በመቅረባቸው፣ በፖለቲካ አስፈጻሚ አካላትና ብሄርተኛ አመለካከት ባላቸው አንዳንድ ወገኖች ወላጆችና የየአካባቢው ማህበረሰብ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ውጪ ሌላ እንዳይጠቀሙ የሚደረጉ አሉታዊ ግፊቶች በርከት ያሉ የገጠር አንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት ብቻ ተገድበው እንዲቀሩና በሁለተኛ ቋንቋ ተግባቦታዊ ብቃት እንዳያዳብሩ ተጽእኖ ማድረጉንም የጥናቱ ግኝቶች አረጋግጠዋል፡፡

በአጠቃላይ በተተኳሪዎቹ የገጠር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ተግዳሮቶች ከአመለካከት ጋር የተያያዙ ሳይሆኑ፤ ከትግበራ አውድ ጋር የተያያዙ ስነልሳናዊና ስነትምህርታዊ፣ ቁሳቁሳዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ድጋፎች ጋር የተያያዙ ሲሆኑ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ሁሉንም በአፍ መፍቻ ቋንቋ አውዱ ያሉ ተግዳሮቶች ለመቀነስ /ለማስወገድ/ ቁልፍ ሚና ያለው መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሃሳቦች ጥቆማ

ከፍ ሲል የቀረቡትን የጥናቱ ግኝቶችና ማጠቃለያ መሰረት በማድረግ አጥኚዋ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሃሳቦች በመጠቆም ጥናቱን ለማጠቃለል ትወዳለች፡፡

1. የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋን የመማሪያ ቋንቋ እንዲሆን የማቀድ ቁርጠኝነት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ በመሬት ላይ በተግባር የሚታዩትን ስነልሳናዊና ስነትምህርታዊ ተግዳሮቶች በማስወገድ የመማር ማስተማሩ ክንዋኔ የአንደኛ ደረጃ የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት፣ የክፍል ተሳትፎና ውጤታማነት እንዲያረጋግጥ ማድረግ ከሁሉም ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት በክልል ደረጃ የሚገኙ የመርሃ-ትምህርት አቃጆችና የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች በመርሃ-ትምህርት ክለሳ ዙሪያ በተነሳሽነት መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ከመማሪያ መጻህፍት ዝግጅት ጋር አያይዘውም የቃላት መደበኛ ፍቺ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ጽንሰሃሳቦችን ብያኔ የሚያቃልሉ ብልሃቶችን አስሰው ስራ ላይ ቢያውሉ፤ በተለይ ደግሞ የአፋን ኦሮሞ ዘዬያዊ ቃላትን ትርጉም ለማወቅ

የሚረዱ ሙዳየ ቃላት ላይ ቢያተኩሩና የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችግሮችን ለመቀነስ በሚረዱ ቴክኒካዊ ስልቶች ተደግፈው መልመጃዎችን ቢያሰናዱ መልካም ይሆናል፡፡

2. የአፍ መፍቻ ቋንቋን የትምህርት ቋንቋ ከማድረግ ጋር አብሮ መታሰብ የሚገባው የተማሪዎችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ችግሮች ለማቃለል የሚረዱ ልሳነ ዋህድና ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት አብሮ በማሰናዳት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዘንድ ለመምህራንና ተማሪዎች ፍላጎት ተደራሽ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመማሪያ መጻህፍትና የመምህር መምሪያዎች እጥረት፣ በማገናዘቢያና አጋዥ መጻህፍትና ተነባቢ ጽሁፎች አለመሟላት የሚታዩ ክፍተቶች የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዳይጠናከር ተጽእኗቸው ቀላል አይደለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ መንግስትና በየእርከኑ ያሉ የትምህርት ስራ ሃላፊዎች ለመማሪያ መጻህፍትና የትምህርት ቁሳቁሶች ዝግጅትና ስርጭት የየራሳቸውን ሃላፊነት በመወጣት ቁርጠኝነታቸውን ቢያሳዩ መልካም ነው፡፡

3. በቂ የሰው ኃይል ስልጠና፣ ምደባ፣ ሙያዊ ተበረታችነትና የመምህራን ጥራት የአፍ መፍቻ ቋንቋ አውዱ ቁልፍ ችግሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በመምህርነት ሙያ በቂ የሰው ሃይል ማሰልጠን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር አጋዥ መሆኑን ታሳቢ ያደረገ የስልጠናና የተሃድሶ ስርአት መዘርጋት፣ መምህራን በሙያቸው ተበረታች እንዲሆኑ የሚያግዙ የማነቃቂያ ስልቶችን ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ ማስፈን፣ አርአያነት ላላቸው የመምህራን ተሞክሮዎች እውቅና መስጠትና የመማር ማስተማሩን ሂደት በቅርበት እየተገኙ በመገምገም ስለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ ጥራትና የተጠቃሚዎች እርካታ በቂ ግብረመልስ ማግኘት በየደረጃው የሚገኙ የክልል፣ የዞን ፣ የወረዳ ትምህርት ቢሮ ሃላፊዎች ቁልፍ ተግባር መሆን ይኖርበታል፡፡

4. በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የመስጠት እሳቤ ተማሪዎቹ በሁለተኛና የውጪ ቋንቋ የመማርን ሂደት ቀላል ያደርግላቸዋል የሚል ነው፡፡ ይሁንና በሁለተኛ /በአማርኛ/ ቋንቋ ላይ የትምህርት ስርአቱ በጎደለው ጤናማ እይታ የተነሳ የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በበቂ ተነሳሽነት እንዳይማሩት ተጋልጠ ነፍጓቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ስርአቱ ውስጥ የሚያልፉትን ተማሪዎች ልሳነ ብዙ የቋንቋ እውቀት የሚጎዳ በመሆኑ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ከመማር መብት ጋር የሁለተኛ ቋንቋ ግንዛቤ አብሮ እንዲያድግ ለማድረግ የሚያስችል መርህን

የትምህርት ስርአቱ ፖሊሲ አውጪዎችና አስፈጻሚዎች ብርቱ ትኩረት ማድረግ ብሎም ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ፍላጎት መጣጣል ፈጽሞ መቅረት ይኖርበታል፡፡

5. ከ1ኛ–4ኛ ክፍል መድገም በፖሊሲ ደረጃ የተከለከለ በመሆኑ ተማሪዎች ተገቢ የክፍል ማለፊያ መስፈርቶችን ሳያሟሉ አምስተኛ ክፍል የሚደርሱበት ሁኔታ መኖሩ በተማሪዎች የአፍ መፍቻ እውቀትና ክህሎት ጨባጭነት ልምድ ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተጽእኖ ቀላል አይደለም፡፡ የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ አውድ ቆይታ በተገቢ የተማሪዎቹ ግንዛቤ፣ እውቀት፣ ልምድና የባህሪ ለውጥ መደገፉን በሚያረጋግጡ በቂ የምዘና እና የክትትል ስልቶች ተደግፎ ተማሪዎችን ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ የማሳለፍ አስፈላጊነት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱን ጥራት ማረጋገጥ ያስችላል፡፡ በመሆኑም ከፖሊሲ አውጪዎች ጀምሮ የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋንኛ ባለቤት መምህራን ድረስ ተማሪዎች በተገቢ የምዘና ስርአት ውስጥ ደረጃ በደረጃ እንዲያልፉ ክትትልና ትኩረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

6. የወላጆችና የገጠሩ ማህበረሰብ ጠንካራ ተሳትፎ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማሩ ሂደት እንደምሰሶ የሚቆጠር ቢሆንም የወላጆችና ማህበረሰቡ ትብብርና ድጋፍ በዳር ቆሞ ተመልካችነት የተገደበ ነው፡፡ ይህን ሁኔታ ከአስተሳሰብ ለውጥ በመነሳት የሁሉንም የትምህርት ባለድርሻዎች ዘላቂ አስተዋጽኦ ማደላደል ያስፈልጋል፡፡ የተማረና ሀገር ተረካቢ ትውልድ የመፍጠር ማህበራዊ ንቅናቄ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ወላጆች፣ ባለሀብቶች፣ የአካባቢ ተወላጆችና አጠቃላዩ የገጠሩ ማህበረሰብ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለማሻሻል በሚረዱ ጉዳዮች ተሳትፎ አጋርነታቸውን በተጨባጭ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የማህበረሰብ ውይይቶችንን ፣ ቅናቄዎችንና ቁሳዊ ድጋፎችን ማጠናከር፤ የምሁራን ፣ የሕብረተሰቡ አስተዳዳሪዎች ፣ የትምህርቱ ስራ መሪዎች፣ የባለሃብቶች፣ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶችና የሚዲያዎች ድርሻ ይሆናል፡፡

7. መምህራን ፣ ተማሪዎችና ወላጆች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ የሚኖራቸው አመለካከት ለመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት የራሱ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚኖረው የሚታመን ነው፡፡

በመሆኑም ለመምህራንና ወላጆች ስለ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጠቀሜታ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋጀት ፣ የተለያዩ የትምህርት ባለ ድርሻዎችን በመጋበዝ

ትምህርት የሚሆኑ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን ማስፋፋት ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መጎልበት በጣም ጠቃሚ ድርሻ እንደሚያበረክት ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ የወረዳ አስተዳዳሪዎች፣ የትምህርቱን ዘርፍ የሚመሩ የቢሮ ኃላፊዎች፣ የትምህርት ባለሙያዎችና ሱፐርቫይዘሮች፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎችና የወላጅ መምህራን ህብረት (ወመህ) አባላት ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ ማህበረሰባዊ አመለካከት መስረጽና ለመማር ማስተማሩ ሂደት መጎልበት ከፍ ያለ ሚና አላቸው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለማቃለል የሚረዱ አካባቢያዊ መፍትሄዎችን መቀየስና በአግባቡ የሚተገበሩበትን ሁኔታ ማመቻቸትም የሁሉም የትምህርት ባለድርሻ አካላት ተግባር መሆን ይኖርበታል፡፡

8. በአጠቃላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት መጠቀም በአመለካከት ደረጃ የተያዘ ጉልህ ችግር ባይታይበትም በትምህርት ቤቶችና በትምህርት ባለድርሻዎች መካከል የጠበቀ ግንኙነት እንዲፈጠር ለማድረግ የሚረዱ ስልቶችና ብልሃቶች ባለመጠናከራቸው የተነሳ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ድጋፍ ያጡ መሆናቸው አሳሳቢ የችግር መንስኤ ነው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በተሳካ ሁኔታ እንዲሰጥ በየአካባቢው በሚታዩት ተግዳሮቶች ዙሪያ አትኩሮ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በተለይ በመንግስት ደረጃ በትምህርቱ መስክ ያልተሟሉ የትምህርት ቁሳቁሶች ማለትም የተማሪ መማሪያ መጻህፍትና የመምህሩ መምሪያ፣ የትምህርት መርጃ መሳርያዎች፣ ማገናዘቢያና አጋዥ መጽሀፎች ወዘተ. ቢሟሉ፤ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለቋንቋው እድገት ትኩረት ቢሰጡ፤ የማህበረሰቡ ተወላጅ የሆነ ሁሉ ያሰተምራል የሚለው አመለካከት ቢቀየር፤ የክልሉ መንግስት ከፖለቲካ አጀንዳ ማስፈጸሚያነት በጸዳ መልኩ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት መጠናከር በጥናት ላይ የተመረኮዘና በተግባር የሚገለጽ ትኩረት ቢሰጥ፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚገዛበትና ተማሪዎች የሚመሩበት ህግጋት በክልል ደረጃ ተዘጋጅተው በማህበረሰብ ውይይቶች ዳብረው አገልግሎት ላይ ቢውሉ፣ የመምህራን በሙያቸው ደስተኝነት ማጣትና ፍልሰትን ለመቀነስ የሚረዱ ስልቶች ተቀይሰው በስራ ላይ ቢውሉ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ለማጠናከር ገንቢ እርምጃ መሆኑን በመጠቆም ጥናቴን አጠቃልያለሁ፡፡

# ዋቢ መጻህፍትና ጽሑፎች


በኀሰው የሺዋስ፡፡ (2010 ዓ.ም)፡፡ "የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት የመጠቀም አመለካከቶችና ተግዳሮቶች፤ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በከምባታና በወላይታ ቋንቋዎች ተተኳሪነት"፤ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሶስተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ (1994 ዓ.ም)፡፡ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ አተገባበር፡፡ አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፡፡

Alemayehu Dogamo. (2005). The Challenges of Mother Tongue Education: The case of Wolayta. A Thesis Submitted to the School of Graduate Studies Addis Ababa University.

Alexander, N. (2003). The African Renaissance and the Use of African Languages in Tertiary Education. *PRAESA Occasional Papers* No. 13. Cape Town: PRAESA.

Alidou, et al. (2006). *Optimizing learning and education in Africa-the language factor: A stock-taking research on mother tongue and bilingual education in sub-saharan Africa*: UNESCO Institute for Education.

Altaye Ayele. (2001). "The Use of the Wolaytta Language as the Language of Learning in Primary School". MA Thesis. Addis Ababa: Addis Ababa University.

Antone Woods. A. (1958). *Language Function and Language Impire*. Oxford. Black well publishers.

Baker, C. (1998). *Foundations of Bilingual Education and Bilingualism*. Third edition. Clevedon: Multilingual Matters.

Ball, J. (2011). *Enhancing learning of children from diverse language backgrounds:* Mother tongue-based bilingual or multilingual education in early childhood and early primary school years. UNESCO: University of Victoria.

Beeckman, A. (2005). *Mother tongue Instruction in Africa: Human rights treaty bodies and the language problem in education*. Netherlands, African Foundation for International Law.

Birgit, B. (2010). Education for all in whose language. *Oxford review of education,* 27, 1.

Brown, D. (2007). *Principles of language learning and teaching*. USA, Longman Publishing.

Calvet, Louis Jean. (2006). *Towards an Ecology of World Languages*. Polity Press.

Cohen, L. (2000). Minimum competency standards for LOTE teaching. Brisbane: NLLIA Language and Testing and Curriculum Centre, Griffith University.

Cook, J. L., & Cook, G. (2005). *Child development: Principles and perspectives*. NJ: Pearson Education.

Council of Europe. (2011). *Common European framework of reference for languages: Learning, teaching, assessment*. Cambridge: Cambridge University Press.

Cummins, C. A. (2000). Preparing mainstream teachers for English language learners:Is being a good teacher good enough? *Teacher Education Quarterly*, 32(2).

Daniel Alemu & Abebayehu, Tekleselassie. (2006). Instructional language policy in Ethiopia: Motivated by politics or the education needs of children? *Planning and Changing*.

Day, R. R., & Conklin, G. (2012). The knowledge base in ESL/EFL teacher education. Paper presented at the TESOL Conference, Vancouver, British Columbia, Canada.

Dornyei, Z. (1998). Motivation in second and foreign language learning. *Cambridge Journals*, 31, 3.

Dumatog, R. & Dekker, J. (2013). Portraits in mother tongue education: Teacher diaries as a starting point for comparative research into standard Language teaching in Europe. Enschede: *TESOL Quarterly*.

Elisabeh, G. (1999). Language equality: Multilingual issues in education. SNNP REB, Awassa.

Elliot, A. J. (2003). *Child language*. Cambridge: Cambridge University Press.

Fasold, R. (1984). *The socio-linguistics of society*. Oxford: Blackwell publishers.

Ferguson, G. (2006). *Language planning and education*. Great Britain: Edinburgh University Press Ltd.

Fromkin and others. (2001). *An introduction to Language*. Canada. Thomson limited.

Gardner, R. (1985). *Social psychology and second language learning*: The role of attitudes and motivation. Great Britain: Edward Arnold Ltd.

Halliday, M. A. K. (1993). Towards a Language-Based Theory of Learning. *Journal of Lingustics and Education*, 5(1).

Heugh, K. et al. (2007). Final report study on medium of instruction in primary school in Ethiopia. (Research Report). Addis Ababa: Commissioned by the Ministry of Education.

Hirut Woldemariam. (2008). The challenges of mother-tongue education in Ethiopia: The case of north Omo area, language matters. *Studies in the Languages of Africa*, 38.

Hoben, J. S. (1994). The Language of Education in Ethiopia: Empowerment or Imposition? In: Harold, M. and Hudson, G. (Eds.) New Trends in Ethiopian Studies, Papers of the 12th International Conference of Ethiopian Studies. New Jersey: The Red sea Press.

Jacob, J. et al. (2015). *Policy debates and indigenous education*: The trialectic of language, culture and identity. USA: University of Pittsburgh.

Jeilan Aman Gobana. (2013). Challenges of Mother-Tongue Education in Primary Schools: The Case of Afan Oromo in the East Hararge Zone, Oromia Regional State, Ethiopia. Submitted in accordance with the requirements for the degree of Doctor of Literature and Philosophy in the Subject African Languages at the University of South Africa.

Khejeri, Mary. (2014). Teachers' Attitudes towards the Use of Mother Tongue as a Language of Instruction in Lower Primary Schools in Hamisi District, Kenya Mount Kenya University, Kenya. *International Journal of Humanities and Social Science, Vol. 4 No. 1.*

Krashen, S. (1981). *Second language acquisition and second language learning*. Great Britain: Wheaton co. Ltd.

Kroskrity, P.V. (2010). Language ideologies- Evolving perspectives. *Society and Language Use,* 7 (7).

MOE (1994). *Education and Training policy, Addis Ababa*; MOE/NOE (National Organization for Examinations) Dec 2004, Ethiopian Second National Learning assessments of grade 4 students and grade 8 students. ESDP I to IV, 2000-2011, MOE, Addis Ababa.

Mutasa, D. (Ed.). (2006). *African languages in 21st century*: The main challenges. South Africa: Simbagoru Publishers.

Ogutu, A. (2006). *Mother tongue amidst other languages: Playing roles in the classroom and outside*. (Ed.). African languages in 21st century: The main challenges. South Africa: Simba goru Publishers.

Ramachandran, R. & Rauh, C. (2016). Discriminatory attitudes and indigenous language promotion: Challenges and solutions. United Nations University World Institute for Development Economics Research.

Seyoum. H. (2009). *Language policy and access to education*. In Seyoum Hameso, Trueman, T., and Temesgen Muleta-Erena (Eds.). *Ethiopia: Conquest and the quest for freedom and democracy* (pp. 153-166). London: TSC Publishers.

UNESCO (2005). *Mother tongue matters*; local language as a key to effective learning Paris: UNESCO.

Wells, G. (1994). The Complementary Contributions of Halliday and Vygotsky to a "Language-Based Theory of Learning" Australian Journal of Lingustics and Education.

Young. C. (2009). *Good practices in mother tongue-first multilingual education*. In: M. Redmond, ed. *Mother Tongue as Bridge Language of Instruction: Policies and Experiences in Southeast Asia*. Bangkok: The Southeast Asian Ministers of Education Organization (SEAMEO) Secretariat.

# አባሪዎች

## ቅጽ ሀ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የአማርኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል

## ለተማሪዎች የቀረበ መጠይቅ

*ውድ የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች!*

*ይህ መጠይቅ የቀረበላችሁ በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በተመለከተ ለጥናት የሚውሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከስር በሰንጠረዥ ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች 5 /አምስት/ አማራጭ መልሶች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ መጠይቅ በጣም እስማማለሁ (በ.እ)፣ እስማማለሁ (እ)፣ መልስ ከመስጠት እታቀባለሁ (እ)፣ አልስማማም (አል) ወይም ፈጽሞ አልስማማም (ፈ.አ) ከሚሉ ምላሾች ለእናንተ ተጨባጭ የአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ተሞክሮ ተስማሚ የሆነውን አንድ መልስ በመምረጥ በየጥያቄዎቹ ትይዩ በመልስ መስጫ ሳጥን ውስጥ የ ‹‹X›› ምልክት በማስቀመጥ ሞልታችሁ እንድታጠናቅቁ ትጠየቃላችሁ፡፡ የሚሰበሰበው መረጃ ሙሉ በሙሉ ለትምህርታዊ ጥናት አላማ ብቻ የሚውል መሆኑን እየገለጽኩላችሁ፣ የምትሰጡት ምላሽ በእውነተኛ የመማሪያ ክፍል ልምዳችሁ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ይህን ጥናት በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንዳለው አስቀድሜ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡ ስለትብብራችሁ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡*

## ክፍል 1፡- የተጠኚዎች ግላዊ መረጃዎች

1.እድሜ፡- ______

2. ጾታ፡- ወንድ______ ሴት ______

3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ችሎታ ደረጃ

| ተ.ቁ | የቋንቋ ክሂል | እጅግ በጣም ጥሩ | በጣም ጥሩ | ጥሩ | ደህና | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መናገር | | | | | |
| 2 | ማዳመጥ | | | | | |
| 3 | ማንበብ | | | | | |
| 4 | መጻፍ | | | | | |

4. የወላጅ /አሳዳጊ/ የትምህርት ሁኔታ፡-

ሀ) አባትና እናት ማንበብና መጻፍ የተማሩ፡-_______

ለ) ከሁለቱ አንዳቸው ማንበብና መጻፍ የተማሩ፡-________

ሐ) ሁለቱም ቢያንስ ማንበብና መጻፍ ያልተማሩ፡-________

መ) ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው 8ኛ ክፍል የጨረሱ፡- ________

ሠ) ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው 10ኛ ክፍል የጨረሱ፡- ________

ረ) ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው ኮሌጅ ዲፕሎማ የጨረሱ፡- ________

ሰ) ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው ከዲፕሎማ በላይ የጨረሱ፡-________

5. በመኖሪያ አካባቢያችሁ በስፋት የሚነገረው መግባቢያ ቋንቋ፡-

ሀ) አፋን ኦሮሞ፡- ________ ለ) አማርኛ፡- ________ ሐ) ሌላ፡-________

5. በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መጻፊያ (ቁቤ) መጻፍ ላንተ/ቺ/ እንዴት ነው?

ሀ) በጣም ቀላል______ ለ) ቀላል______ ሐ) ምንም አይልም_____ መ) ከባድ______ ሠ) በጣም ከባድ______

## ክፍል 2፡- የጥናቱ መረጃዎች

**ማሳሰቢያ፡-** በሰንጠረዡ ውስጥ፡-

*በ.እ. (በጣምእስማማለሁ)፣ 5*

*እስ. (እስማማለሁ)፣ 4*

*እ.ታ. (መልስ ከመስጠት እታቀባለሁ)፣ 3*

*አል. (አልስማማም)፣ 2*

*ፈ.አ. (ፈጽሞ‹‹አልስማማም) 1 ነጥብ የመልስ አማራጮችን ይወክላሉ፡፡*

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ.እ. | እስ. | እ.ታ. | አል. | ፈ.አ. |
| 1 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ለይቼ አውቃለሁ፡፡ | | | | | |
| 2 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ለኔ የትምህርት ቤት ቆይታ በጣም አስደሳች ክንዋኔ ነው፡፡ | | | | | |
| 3 | ሁሉንም የትምህርት አይነቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመማር አጥጋቢ ውጤት ለማምጣት እተጋለሁ፡፡ | | | | | |
| 4 | በትምህርት ቤት ቆይታዬ ከመምህራንና ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመግባባት ትኩረት [illegible] | | | | | |
| 5 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ እወዳለሁ፡፡ | | | | | |
| 6 | የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ በሚገባ በማውቀው ቋንቋ የሚሰጥ በመሆኑ የምማራቸውን ትምህርቶች ሁሉ በደበልጥ ለመረዳት ጠቀሜ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቱ ባህልን ለማወቅ፣ ሰብዕና ለመገንባትና ለስነልቦና እድገት ጠቅሞኛል፡፡ | | | | | |
| 8 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመማር ያገኘሁት እድል ሌሎች ሁለተኛ ቋንቋዎችን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት አስተዋጽኦ አድርጓልኛል፡፡ | | | | | |
| 9 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር በምኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ጥሩ የተግባቦት ችሎታ እንዳዳብር ረድቶኛል፡፡ | | | | | |
| 10 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ የምንማር ተማሪዎች በሌሎች ቋንቋዎች (ለምሳሌ፡- አማርኛ፣ እንግሊዝኛ) እንደሚማሩት ተማሪዎች እኩል ላናውቅ ወይም በስራ እኩል መወዳደር አንችል ይሆናል የሚል ስሜት በበኩሌ | | | | | |
| 11 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስለመማር ያለኝ አመለካከት አዎንታዊ ነው፡፡ | | | | | |
| 12 | በክፍል ውስጥ እውቀት የሚተላለፍበት መንገድ ከቋንቋ ግንዘቤዬ ጋር የተገናዘበ በመሆኑ ለኔ የመማር ሂደት [illegible] | | | | | |
| 13 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደር በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርን በሚገባ ያበረታታል፡፡ | | | | | |
| 14 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የቋንቋና የባህል ክበባት በማደራጀት ተማሪዎች ተሳትፎ እንድናደርግ ያበረታታል፡፡ | | | | | |
| 15 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደርና መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ አጠቃቀም አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖረን በየጊዜው ግንዛቤ ይሰጡናል፡፡ | | | | | |
| 16 | ወላጆቼ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ይገልጹልኛል፡፡ | | | | | |
| 17 | ወላጆቼ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በቤት ውስጥ በአብዛኛው በቤት ውስጥ መጠቀማቸው በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ለመማር መነሳሳት ፈጥሮልኛል፡፡ | | | | | |
| 18 | በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የተሻልኩ ሁኜ ለመገኘት የሚያስችሉ አጋዥ የንባብ መጻህፍትን ወላጆቼ እያመጡ እንዳነብ ያደርጉኛል፡፡ | | | | | |
| 19 | በትምህርት ቤታችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ ባህላዊ ጠቀሜታ ያላቸው መጻህፍት በበቂ ሁኔታ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ በሁሉም የትምህርት አይነቶች የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት በየግላችን ይደርሱናል፡፡ | | | | | |
| 21 | በቂ የሆኑ የመማሪያ መጻህፍት በትምህርት ቤታችን ቤተመጻህፍት ይገኛሉ፡፡ | | | | | |
| 22 | የመማሪያ ክፍሎቻችን ዴስኮችና ጥቁር ሰሌዳ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ተስማሚ ሁነው የተሰናዱ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 23 | በትምህርት ቤታችን ለምንማራቸው የትምህርት አይነቶች ሁሉ በቂ መምህራን ተመድበውልናል፡፡ | | | | | |
| 24 | መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ችሎታ የመማር ማስተማሩን ሂደት ተስማሚ [illegible] | | | | | |
| 25 | ሁሉንም የትምህርት አይነቶች የሚያስተምሩ መምህራን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ በሚገባ መናገርና መጻፍ እንዲሁም የማስተማር ችሎታ ያላቸው በመሆኑ በትምህርቱ ሂደት [illegible] | | | | | |
| 26 | እኔ በምማርበት ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት እንድበረታታ ተከታታይ በሆነ መልኩ እገዛ ይደርጉልኛል፡፡ | | | | | |
| 27 | መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የሚያጋጥሙኝን ችግሮች በማቃለል ሁሌም ድጋፍ [illegible] | | | | | |
| 28 | የተለያዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላትን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ አቻ ትርጉም አሟልቶ የያዘ መዝገበ ቃላት [illegible] | | | | | |
| 29 | ለተማሪዎች ባህላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ትምህርታዊ ፍላጎቶች የሚመጥኑ የመማሪያ ቁሳቁሶች በትምህርት ቤታችን ተማልተው ይገኛሉ፡፡ | | | | | |
| 30 | የአፍ መፍቻ ቋንቋን መሰረት ባደረገው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የእስካሁኑ ተከታታይ ቆይታዬ ያገኘሁት ግንዛቤና ተሞክሮዬ በበኩሌ አበረታች እንደሆነ [illegible] | | | | | |
| 31 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ የጽሁፍ ቋንቋ ከመሆኑ ጋር ሰዋስዋዊ ስርዓቱን መለየት ትምህርቱን ከባድ እየርጎብኛል፡፡ | | | | | |
| 32 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ለጽሁፍ የሚያገለግሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቃላት ስያሜዎች ለመረዳት ይከብዳሉ፡፡ | | | | | |
| 33 | ወላጆቼ በትምህርት ጉዳይ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ሲጠሩ ለመገኘት አያመነቱም፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 34 | በቤተሰባችን ውስጥ ካሉ ታላላቆቼ ወይም ዘመዶች ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርቴ መጠናከር የሚረዳ [illegible] | | | | | |

# ቅጽ ለ

## ከመምህራን ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ ማተኮሪያ ነጥቦች

### ውድ መምህር!

በቅድሚያ በዚህ ቃለመጠይቅ በመሳተፍ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛነትዎን ስላሳዩኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ የዚህ ቃለመጠይቅ አላማ በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በተመለከተ ለጥናት የሚውሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡ የሚሰበሰበው መረጃ ሙሉ በሙሉ ለትምህርታዊ ጥናት አላማ ብቻ የሚውል መሆኑን እየገለጽኩልዎት፣ የሚሰጡት ምላሽ በእውነተኛ የመማር ማስተማር ተሞክሮዎ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ይህን ጥናት በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንዳለው አስቀድሜ ልገልጽልዎት እወዳለሁ፡፡ ስለትብብርዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

1. በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መምህርነት ያለዎት ስልጠና እንዴት ነው? በቋንቋው በማስተማር ያለዎት ልምድስ ምን ይመስላል? በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ በማስተማር ላይ እያሉ ያገኙት የስራ ላይ ስልጠና ካለ አያይዘው ቢገልጹልኝ?
2. በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፖሊሲና አተገባበር ዙሪያ ያለዎት አመለካከት ምን እንደሚመስል ቢገልጹልኝ?
3. እርስዎ በሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ከማቅረብ ጋር ተያይዘው የሚስተዋሉ ችግሮች ምን ምንድናቸው?
4. በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ ዙሪያ ለሚስተዋሉ አበይት ችግሮች መንስኤ ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ቢገልጹልኝ?
5. በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎችዎ ያላቸው አመለካከት፣ ተነሳሽነትና የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ቢገልጹልኝ?

ስለትብብርዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# ቅጽ ሐ

# ከትምህርት ቤት ርእሳነ-መምህራን ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ ማተኮሪያ ነጥቦች

## ውድ ርእሰ-መምህር!

በቅድሚያ በዚህ ቃለመጠይቅ በመሳተፍ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛነትዎን ስላሳዩኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ የዚህ ቃለመጠይቅ አላማ በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በተመለከተ ለጥናት የሚውሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡ የሚሰበሰበው መረጃ ሙሉ በሙሉ ለትምህርታዊ ጥናት አላማ ብቻ የሚውል መሆኑን እየገለጽኩልዎት፤ የሚሰጡት ምላሽ በእውነተኛ የትምህርት ቤትዎ ተሞክሮ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ይህን ጥናት በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንዳለው አስቀድሜ ልገልጽልዎት እወዳለሁ፡፡ ስለትብብርዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

1. በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፖሊሲና አተገባበር ዙሪያ ያለዎት አመለካከት ምን እንደሚመስል ቢገልጹልኝ?
2. በትምህርት ቤትዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራን ለማጎልበት በትምህርት ቤቱ፣ በወላጆች፣ በመንግስትና በትምህርት ባለድርሻዎች የሚደረጉ ድጋፎች ምን ይመስላሉ?
3. እርስዎ በሚመሩት ትምህርት ቤት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ከማቅረብ ጋር ተያይዘው የሚስተዋሉ ዋንኛ ችግሮች ምን ምንድናቸው?
4. በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ ዙሪያ ለሚስተዋሉ አበይት ችግሮች መንስኤ ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ቢገልጹልኝ?
5. በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ወላጆችና ማህበረሰቡ ያላቸው አጠቃላይ አመለካከትና ተነሳሽነት ምን እንደሚመስል ቢገልጹልኝ?

ስለትብብርዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# ቅጽ መ

# ከወላጅ-መምህራን ሕብረት (ወመህ) ተወካዮች ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ ማተኮሪያ ነጥቦች

ውድ የወላጅ መምህር ህብረት ተወካይ!

በቅድሚያ በዚህ ቃለመጠይቅ በመሳተፍ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛነትዎን ስላሳዩኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ የዚህ ቃለመጠይቅ አላማ በአፋን ኦሮሞ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በተመለከተ ለጥናት የሚውሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡ እርስዎ በሚያስተዳድሩት ትምህርት ቤት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ስለሚታዩት አጠቃላይ ሁኔታዎች እውነተኛ የሚሉዋቸውን መረጃዎች እንደሚሰጡኝ እምነት አለኝ፡፡ ስለትብብርዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

1. በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ወላጆችና ህብረተሰቡ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

2. በሚመሩት ትምህርት ቤት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራን ለማጎልበት በወላጅ መምህራን ህብረት፣ በወላጆች፣ በመንግስትና በሌሎች የትምህርት ባለድርሻዎች የሚደረጉ ድጋፎች ምን ይመስላሉ?

3. በዚህ ትምህርት ቤት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ከማቅረብ ጋር ተያይዘው የሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ምንድናቸው ብለው ያምናሉ?

4. በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ትግበራ ዙሪያ ለሚስተዋሉ አበይት ችግሮች መንስኤ ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ቢገልጹልኝ?

# ቅጽ ሠ

# የክፍል ምልከታ መቃኛ ነጥቦች

1. የትምህርት ቤት ስም፡----------------------------------
2. የምልከታ ዙር ፡- 1ኛ ------- 2ኛ -------
3. የምልከታ ቀን ----------------------------------

| ተ.ቁ | የምልከታ መቃኛ ነጥቦች | የምልከታ ውጤት | |
|---|---|---|---|
| | | አጥጋቢ ነው | አጥጋቢ አይደለም |
| 1 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቹ ተደሳችነት፡- | | |
| 2 | ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያሳዩት ተሳትፎ፡- | | |
| 3 | መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ አቅደውና አደራጅተው ማቅረባቸው፡- | | |
| 4 | መምህሩ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተግባቦት እንዲያካሂዱ የሚያደርጉት ጥረት፡- | | |
| 5 | ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል መምህሩ የሚያደርጉት ጥረት ተደራሽነት፡- | | |
| 6 | ተማሪዎቹ በሚማሩት ይዘት ዙሪያ የእርስ በርስ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ እንዲያበለጽጉ የሚያደርጉት ግፊት ጉልህነት፡- | | |
| 7 | በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የትምህርቱ ማእከል አድርገው ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት አነቃቂነት፡- | | |
| 8 | በቀረበው ትምህርት ላይ ግብረ-መልስ በማቅረብ ትምህርቱን ለማስረጽ የሰጡት ትኩረት፡- | | |
| 9 | ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚነት፡- | | |
| 10 | በትምህርት ቤቱ ቤተመጻህፍት በቂ የተጨማሪ ንባብ አጋዥ መጻህፍት ተሟልተው መገኘት፡- | | |